# ሕብረተሰብ ትምህርት

## የመምህራን መጽሐፍ

## የስምንተኛ ክፍል

**አዘጋጆች :**

በላቸዉ አበራ (M.A)

ግርማ ፀጋየ (M.Ed.)

ነጌሶ እስሞ (M.Sc.)

**አርታኢዎች:**

ጀማል ሙስጠፋ (M.Ed.)

ነጋሽ ሄቦ (M.A.)

**ገምጋሚዎች:**

በቀለ ቀነአ (M.A)

አበራ ከበበዉ (B.A)

ፍቃዱ ከበደ (M.A)

ቤኪ ቶለሣ (M.A)

**ተርጓሚዎች:**

በቀለ ቀነአ (M.A)

ቤኪ ቶለሣ (M.A)

አበራ ከበበዉ (B.A)

ከተማ ፀጋ (M.A)

ዘዉዴ ረጋሣ (M.A)

**ግራፊክስ:**

ታደሰ ድንቁ (M.A)

© የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ፣ 2014/2021

ይህ መጽሐፍ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮና በሮቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ትብብር በ2014/2021 ተዘጋጀ፡፡

የዚህ መጽሐፍ የባለቤትነት መብት በህግ የተጠበቀ ነው፡፡ ከኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ፈቃድ ውጪ በሙሉም ሆነ በከፊል ማሳተምም ሆነ አባዝተው ማሰራጨት በህግ ያስጠይቃል፡፡

## መዉጫ


ይዘት ገፅ

ምዕራፍ አንድ 1

1. ተፈጥሮኣዊ የመሬት ባህሪያት ..... 1

1.1 የመሬት ገፅታን የሚቀይሩ ኃይሎች ..... 2

1.2. በከባቢ አየር ውስጥ የሚገኙ ይዘቶች ..... 8

1.3. የአየር ንብረትና የአየር ሁኔታን የሚቆጣጠሩ ነገሮች ..... 12

ምዕራፍ ሁለት ..... 17

ህዝብ ፤ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ..... 17

2.1. የባህል ልዩነትና ለውጦች ..... 18

2.3 ንግድና ገበያ ..... 30

2.4 የመንግስት ገቢና ግብር ..... 31

ምዕራፍ ሦስት ..... 35

ተፈጥሮ ሀብት ፤ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች እድገት ..... 35

3.1 የተፈጥሮ ሀብት፤ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ..... 35

3.2. በተፈጥሮ ሀብት ያለእንክብካቤ መጠቀም የሚመጡ ጉዳቶች ..... 42

ምዕራፍ 4 ዘመናዊው የአለም ታሪክና አጀማመሩ ..... 46

4.1. ጂኦግራፊያዊ የባህርና ውቅያኖስ ላይ አሰሳ ..... 47

4.2 የአዳዲስ ጽንሰ ሃሰቦች መፍለቅ (Renaissance) ፣ የተሓድሶ እንቅስቃሴ (Reformation) እና የተሓድሶ እንቅስቃሴ ተቃውሞ (Counter-Reformation) ..... 50

4.3 የኢንዱስትሪ አብዮት ..... 54

4.4. አንደኛው ናሁለተኛው የአለምጦርነቶች ..... 57

4.5. ቀዝቃዛው የአለም ጦርነት ..... 60

ምዕራፍ 5 የአፍሪካ ታሪክ ከ15ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ..... 66

5.1. የባርያ ንግድ ስርዓት ........ 66

5.2 የቅኝ አገዛዝ ስርዓት በአፍሪካ ........ 69

5.3. የአፍሪካ ህዝቦች ከነፃነትበኋላ ያጎለበቱት ፖሊቲካዊና ምጣኔ ሀብታዊ ትስስር ........ 72

ምዕራፍ 6 ዘመናዊው የኢትዮጵያ ታሪክ ........ 76

6.1. ዘመናዊዉ የኢትዮጵያመንግስት አመሰራረት ........ 76

6.2. የረጅም ርቀት የንግድ መስመር ........ 79

6.3. ዘመናዊዉ የኢትዮጵያ መንግስት ከዉጭ ሀገራት ጋር ያለው ግንኙነት ........ 82

6.4. የኢትዮጵያ ህዝቦች በአንድነት ዳር ድንበርና ሉዓላዊነትን ለማስከበር ያደረጉት ትግል. 86

ምዕራፍ ሰባት፡ ትኩረት የሚሹ ዋና ዋና የአለም ጉዳዮች ለዚህ ምዕራፍ የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት ……………………………12 ........ 91

7.1. በአሁኑ ጊዜ ትኩረት የሚሹ ዋና ዋና የአለም ጉዳዮች ........ 91

ሕብረተሰብ ትምህርት ሲለበስ ……………………………………………………107

# ምዕራፍ አንድ

## 1. ተፈጥሮኣዊ የመሬት ባህሪያት

### ለዚህ ምዕራፍ የተሰጠው የክፍል ጊዜ ብዛት …………………20

የምዕራፉ የመማር ውጤቶች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፤

- ተፈጥሮኣዊ የመሬት አቀማመጥ ባህሪያትን ይለያሉ።
- የመሬት ገፅታን የሚቀይሩ የመሬት ዉስጣዊና ውጫዊ ሃይሎችን ይለያሉ።
- በመሬት ዉስጣዊና ውጫዊ ሃይሎች ምክንያት የሚፈጠሩ የተለያዩ የመሬት ውጫዊ ገፅታን ይለያሉ።
- የመሬት ዉስጣዊና ውጫዊ ሃይሎች በሰዉ ልጅ ኑሮ ላይ ተፅዕኖ እንዴት እንደሚያደርሱ ይገነዘባሉ።
- በአየር ንብረትና የአየር ፀባይ መካከል ያለዉን ልዩነትን ይለያሉ።
- የአየር ፀባይን የሚቆጣጠሩ ነገሮችና ይዘቶችን ይዘረዝራሉ።
- በደጋ፤ በወይና ደጋና በቆላ አከባቢዎች የሙቀትና የዝናብ መጠን መለያየት ምክንያቶችን ይገልፃሉ።

### መግቢያ

በሰባተኛ ክፍል ትምህርት ውስጥ ስለመሬት ክፍሎችና ይዘቶች አስመልክቶ ተማሪዎች በቂ ግንዛቤ ማግኘታቸዉ ይታወቃል። በዘህ ስምንተኛ ክፍል ምዕራፍ አንድ የህብረተሰብ ትምህርት ውስጥ ደግሞ የመሬት ውጫዊ ገፅታን ለመቀየር ምክንያት የሆኑ የመሬት ዉስጣዊና ውጫዊ ሃይሎችን ይማራሉ። የመሬት ገፅታን የሚቀይሩ የመሬት ዉስጣዊ ሃይሎች እንደ የመሬት መንቀጥቀጥ፤ የመሬት መታጣጠፍ፤ የመሬት መንሸራተትና እሳተ ገሞራ ፍንዳታ ናቸዉ።እነዚህ ኃይሎች በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚቀይሩ ሲሆኑ የመሬት ውጫዊ ኃይሎች

የሚባሉት ደግሞ እንደ የውሃ ጎርፍ፤ ንፋስና የበረዶ መንሸራተት ናቸዉ። እነዚህ ኃይሎች የመሬት ገጽታን ለመቀየር ረጅም ጊዜ ይወስባቸዋል።

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ተማሪዎች ማግኘት የሚገባቸዉ እዉቀት ስለ የአየር ንብረትና የአየር ሁኔታ ምንነት ነዉ። የአየር ንብረት ማለት በኣንድ አከባቢ የሙቀትና የዝናብ መጠን ሳይለወጥ ለረጅም ጊዜ መቆየትን የሚገልፅ ሲሆን የአየር ሁኔታ ማለት በደቂቃ፤ በሰዓት፤ በቀን፤ በሳምንት፤ በወርና በዓመት ውስጥ የሚቀያየር የከባቢ አየር ይዘቶች ፀባይ ነው።

## 1.1 የመሬት ገፅታን የሚቀይሩ ኃይሎች

ለዚህ ርዕስ ትምህርት የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት.............................. (2)

ተማሪዎች ቢያንስ ለደርሱበት የሚገባ የመማር ብቃት

ከዚህ የርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፤

- የመሬት ገፅታን የሚቀይሩ የመሬት ዉስጣዊና ውጫዊ ሃይሎችን ይለያሉ።
- በመሬት ዉስጣዊና ውጫዊ ሃይሎች ምክንያቶች የሚፈጠሩ የተለያዩ የመሬት ውጫዊ ገፅታን ይናገራሉ።
- የመሬት ዉስጣዊና ውጫዊ ሃይሎች በሰዉ ልጅ ኑሮ ላይ ምን ዓይነት ተፅዕኖ እንደሚያደርሱ ይገነዘባሉ።

## ቅድመ ዝግጅት

የዚህን ርዕስ ትምህርት ለማስተማር ከተማሪዎች መጽሐፍ ውጪ ሌሎች የተለያዩ ማጣቀሻ መጻፍሕት ለምሳሌ ከፊዝካል ጅኦግራፊ ስለመሬት አፈጣጠርና ገፀ መሬት አቀማመጥ ላይ የተሰጡ መብራሪያዎችን በሚገበባ በማንበብ ግንዛቤያቸዉን ማዳበር ያስፈልጋል። አጫጭር ማስታወሻዎችን፤ የልምምድ፤ለውይይት የሚሆኑ ጥያቄዎችን ማዘጋጀት ያስፈሌጋል። በተጨማሪም ትምህርቱን ሊረዱ የሚችሉ የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ማዘጋጀት አስፈላጊ ነዉ።

# የመማር ማስተማር ዘዴዎች

የዚህን ርእስ ትምህርት የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ማስተማር ይቻላል፡፡ እነሱም በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ አማካይነት፣ በውይይትና የመሳሳሉት ናቸው፡፡ በመቀጠልም የተማሪዎችን ግንዛቤ ለመጨመር እና የመማር ማስተማር ሁኔታን ተጨባጭ ለማድረግ የምዕራፉን መልመጃ ስራዎችን በተሰጠው ጊዜ ውስጥ እንዲሰሩ ማበረታታት የበለጠ ውጤት ሊያመጣ ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ ቢያንስ ተማሪዎች ሊደርሱበት የሚገባ የመማር ብቃት ለማሳካት ተማሪዎችን ያማከለ የመማር ማስተማር ዘዴ መምረጥ ያስፈልጋል፡፡ በተማሪዎች መካከል ያለውን ልዩነት በማጥበብ ቁጥጥር እና ክትትል በማድረግ በቂ ድጋፍ እና ገለጻን በመስጠት ተመሳሳይ ግንዛቤ አንዲያገኙ ማድረግ ነው፡፡

## ልዩ ተሠጥዖ እና ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

ልዩ ችሎታ እና ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማበረታታት አስፈላጊ ነው፡፡ ውይይቱን ከሌሎች ተማሪዎች ቀድሞ ቶሎ መጨረስ ስለሚችሉ ርእሱን የበለጠ ሊያስገነዝባቸው የሚያስችል የተለየ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት መስጠት ያስፈልጋል ፡፡ በክፍል ውስጥ ያሉ በትምህርት አቀባበላቸው ፈጣን ያልሆኑ እና ሴት ተማሪዎችን ደግሞ ተጨማሪ ሥራን እንዲሰሩ ማድረግና ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት እንድያገኙ ማድረግ መረሳት የሌለበት ጉዳይ ነዉ፡፡

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ ለማወቅ ተከታታይነት ያለው ክትትል ማድረግ ነው፡፡ የተማሪዎችን ችሎታ በመለየት የሚያስፈልጋቸውን እገዛ ማድረግ ነው፡፡ ለምሳሌ የመሬትን ገፅታ የሚቀይሩ የመሬት ውስጣዊና ውጫዊ ሃይሎች ምን ምን ናቸዉ? እንዴትስ ይቀይራሉ እና የመሳሰሉት ጥያቄዎችን በመጠየቅ ግንዛቤያቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ሁሉም ተማሪዎች ቢያንስ ሊደርሱበት የሚገባቸው የብቃት ደረጃ ላይ መድረስ አለባቸው፡፡

የመማር ደረጃ ላይ ሊደርሱ ያልቻሉ ተማሪዎችን ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ተመሳሳይ ብቃት እንዲኖራቸው የተለየ ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል። ስለዚህ ለነዚህ ተማሪዎች የተለየ የትምህርት ክፍለ ጊዜ በማዘጋጀት በእረፍት ሰዓታቸው የሚሰሩትን ሥራ በመስጠት እንዲሰሩ በማገዝ የተለየ ድጋፍ ማድረግ አስፈላጊ ነው። የተሻለ ውጤት ያገኙ ተማሪዎች ባገኙት ውጤት በመኩራራት ወደኂላ እንዳይመልሱ ማበረታታት እና መከታተል አስፈላጊ ነው።

## የመልመጃ 1.1 ጥያቄዎች መልስ

1. የመሬት ገፅታን የሚቀይሩ ሀይሎች በሁለት ይከፈላሉ። እነሱም ውስጣዊ የመሬት ሀይሎችና ውጫዊ የመሬት ሀይሎች ናቸዉ።

2. የመሬት አቀማመጥ ስንል ተራራ፤ ሜዳ፤ ሸለቆና የመሳሰሉት ናቸው ይችላሉ።

3. የመሬት ገፅታን የሚቀይሩ የመሬት ዉስጣዊና ውጫዊ ሃይሎች ልዩነት የመሬት ዉስጣዊ ሃይሎች የሚባሉት የመሬት መንቀጥቀጥ፤ የመሬት መተጣጠፍ፤ የመሬት መንሸራተትና የእሳተ ገሞራ ፍንዳታ ሲሆኑ የመሬት ውጫዊ ኃይሎች የሚባሉት ደግሞ እንደ የውሃ ኅርፍ፤ ንፋስና የበረዶ መንሸራተት ናቸዉ።

### 1.1.1 የመሬት ገፅታን የሚቀይሩ የመሬት ዉስጣዊ ሃይሎች

ለዚህ ርዕስ ትምህርት የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት............................ (5)

ተማሪዎች ቢያንስ ሊደርሱበት የሚገባ የመማር ብቃት

ከዚህ ርዕሱ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች፤

- በመሬት ዉስጣዊ ሃይሎች ምክኒያት የሚፈጠሩ የመሬት ውጫዊ ገፅታን ይለያሉ፡
- በአከባቢያቸዉ የሚገኙ የመሬት አቀማመጦችን ያደንቃሉ።
- የመሬት ዉስጣዊና ውጫዊ ሃይሎች በሰዉ ልጅ ኑሮ ላይ የሚያደርሱትን ተፅዕኖዎችን ይገልፃሉ።

## ዋና ዋና ነጥቦች

የመሬት አቀማመጥ በሁሉም ቦታዎች ተመሳሳይ አይደለም። አንድ አንድ ቦታዎች ተራራማ ሲሆን ሌላዉ ደግሞ ሜዳማ እንዲሁም ሸለቋማ ሊሆኑ ይችላሉ።ተማሪዎችይህንን የመሬት አቀማመጥ በተጨባጭ እንዲማሩ ወደ መስክ በመዉሰድ አከባቢያቸዉን እንዲመለከቱና ያዩትን ደግሞ እንዲናገሩ ማድረግ ያስፈልጋል። ይህ ዓይነት አካሄድ በክፍል ውስጥ የተማሩትን ትምህርት በትክክል እንዲረዱ ያግዛቸዋል።

ከመስክ ምልከታ ውጪ ተማሪዎች የተለያዩ ስዕሎችንና ሞዴሎችን እንዲመለከቱ በማድረግ ግንዛቤያቸዉን እንድያዳብሩ ማድረግ ነዉ። የዚህ ትምህርት ዋና ዓላማዉ ግብ መምታቱን ለማረጋገጥ የተማሪዎችን ርፖርት መመልከትና የተለያዩ የቃል ጥያቄዎችን መጠየቅ አስፈላጊ ነዉ። በተጨማሪም መምህራን ከግል ግንዛቤያቸዉ በመነሳት የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የትምህርቱን ዓላማ ከግብ ማድረስ ይችላሉ።

## ቅድመ ዝግጅት

ይህንን ርዕስ ለማስተማር የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን እንደ ሥዕል፤ የመሬት ውስጣዊ ሀይሎችን የሚያሳዩ ፎቶ ግራፎችን በማዘጋጀት፤ እንዲሁም ከተለያዩ ምንጮች በማግኘና ተጨማሪ መፅሓፎችን በማንበብ በቂ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልግል። የመሬት አቀማመጥ(ተራራዎችን፤ ሸለቆዎችን፤ ሜዳዎችን፤ ፕላቶዎችን) የሚያሳዩ የዓለም ካርታን መጠቀም አስፈላጊ ነዉ።

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

የዚህን ርእስ ትምህርት የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ማስተማር ነው። እነሱም በገለፃ፤ በጥያቄና መልስ፤ በውይይትና በመሳሳሉት ዘዴዎች ማስተማር ነው። በመቀጠልም የተማሪዎችን የመገንዘብ ችሎታን ለመጨመር እና የመማር ማስተማር ሁኔታን ተጨባጭ ለማድረግ የምዕራፉን የመልመጃ ስራዎችን በተሰጠው ጊዜ ውስጥ እንዲሰሩ ማበረታታት የበለጠ ውጤት ሊያመጣ ይችላል።

ይሁን እንጂ ተማሪዎች ቢያንስ ሊደርሱበት የሚገባ የመማር ብቃት ለማሳካት ሁሉንም ተማሪዎች ያማከለ የመማር ማስተማር ዘዴ መምረጥ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ርዕስ ውስጥ ሊማሩ የሚገባቸው ዋና ዋና ነጥቦች የመሬት ውስጣዊ ሀይሎችን ነዉ፡፡

## ልዩ ተሠጥዖ እና ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

ልዩ ችሎታ እና ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማበረታታት አስፈላጊ ነው፡፡ ውይይቱን ከሌሎች ተማሪዎች ቀድሞ ቶሎ መጨረስ ስለሚችሉ ርእሱን የበለጠ ሊያስገነዝባቸው የሚያስችል ተጨማሪ ጥያቄዎችን ማዘጋጀትና መስጠት ያስፈልጋል ፡፡ በክፍል ውስጥ ያሉ በትምህርት አቀባበላቸው ፈጣን ያልሆኑ እና ሴት ተማሪዎችን ደግሞ ተጨማሪ ሥራን እንዲሰሩ ማድረግና ሊደርሱበት የሚገባቸዉን የመማር ብቃት እንዲያገኙ ማድረግ መረሳት የሌለበት ጉዳይ ነዉ፡፡

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች የመሬት ገፅታን የሚቀይሩ ሀይሎች ላይ ሰፊ ውይይት እንድያደርጉ ፤ በክፍል ውስጥ በመዘዋወር መከታተልና በመጨረሻም ግብረ መልስ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ የመሬት ገፅታን የሚቀይሩ ሀይሎች ምንነት መረዳታቸዉን ጥያቄ በመጠየቅ መረዳታቸዉን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በአብዛኛው የመሬት ገፅታን የሚቀይሩ ኃይሎች በመሬት ውስጥ በሚፈጠሩ ሀይሎች አማካይነት መሆኑን እንዲረዱ ማድረግ ነዉ፡፡ በዚህ ምክንያት በመሬት ውጫዊ ገፅታ ላይ የሚታዩ እንደ ተራሮች፤ ሸለቆዎች፤ ሜዳዎችና ፐላቶዎች ናቸዉ፡፡
ለተማሪዎች የቃል ጥያቄ፤ የቤት ሥራዎች፤ የክፍል ሥራዎችና የመሳሰሉትን በመስጠት እዲሳተፉ ማድረግ ነው፡፡

## 1.1.2 የመሬትን ገፅታን የሚቀይሩ የመሬት ውጫዊ ኃይሎች

**ለዚህ ርዕስ ትምህርት የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት………… (3)**

ተማሪዎች ቢያንስ ሊደርሱበት የሚገባ የመማር ብቃት

ከዚህርዕስትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡

- በመሬት ውጫዊ ኃይሎች ምክንያት የተፈጠሩ የመሬት ገፅታዎችን ይናገራሉ፡፡
- በመሬት ውጫዊ ሀይሎች የተፈጠሩ የመሬት ገፅታን የት የት እንደሚገኙ ይናገራሉ፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

ይህንን ርዕስ ማስተማር ከመጀመረዎ በፊት ለትምህርቱ መርጃ መሳሪያነት የሚያገለግሉ እንደ ካርታና የመሬትን ገፅታ የሚያሳዩ ስዕሎችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ ለትምህርቱ አጋዥ የሆኑ የተለያዩ መፅሓፍትን በማንበብ በመሬት ውጫዊ ኃይሎች የተፈጠሩ የመሬት ገፅታዎችን የት እንደሚገኙ የሚያሳይ ካርታዎችን በማዘጋጀት ማስተማር ያስፈልግል፡፡ በተጨማሪም ለተማሪዎች የመስክ ጉብኝት በማዘጋጀት ትምህርቱን ይበልጥ እንዲገነዘቡ ማድረግ ነዉ፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

የዚህን ርዕስ ትምህርት የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን መጠቀም ይቻላል፡፡ እነዚህም ዘዴዎች የመስክ ጉብኝት፤ በገለፃ፤ በጥያቄና መልስ እንድሁም በውይይት መልክ ሊሆን ይችላል፡፡ መምህራን ተማሪዎች ሊደርሱበት የሚገባቸዉን የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ ለማድረግ ተማሪዎችን የሚያነቃቃ ዘዴን መምረጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በዚህ ትምህርት ውስጥ ተማሪዎች እንዲገነዘቡ የሚፈለገዉ ስለ የመሬትን ገፅታ የሚቀይሩ የመሬት ውጫዊ ኃይሎች ነዉ፡፡

## ልዩ ተሠጥዖ እና ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

ልዩ ችሎታ እና ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማበረታታት አስፈላጊ ነው፡፡ ውይይቱን ከሌሎች ተማሪዎች ቀድሞ ቶሎ መጨረስ ስለሚችሉ ርእሱን የበለጠ ሊያስገነዝባቸው የሚያስችል ጥያቄዎችን በማዘጋጀትና መስጠት ነው ፡፡ በክፍል ውስጥ ያሉ በትምህርት አቀባበላቸው ፈጣን ያልሆኑ እና ሴት ተማሪዎችን ደግሞ ተጨማሪ ሥራን እንዲሰሩ ማድረግና ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት እንድያገኙ ማድረግ መረሳት የለበትም ነዉ፡፡

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ ለማወቅ ተከታታይነት ያለው ክትትል ማድረግ አስፈላጊ ነው፤፡ የተማሪዎችን ችሎታ በመለየት የሚያስፈልጋቸውን እገዛ ማድረግ ነው። ለምሳሌ የመሬትን ገፅታ የሚቀይሩ የመሬት ውስጣዊና ውጫዊ ሃይሎች ምን ምን ናቸዉ? እና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅ ግንዛቤያቸውን ማረጋገጥ ይጠበቅቦታል። ሁሉም ተማሪዎች ቢያንስ ሊደርሱበት የሚገባቸው የብቃት ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ለማድረግ ጥያቄዎችን መጠየቅ። ለምሳሌ የመሬት ገፅታን የሚቀይሩ የመሬት ውጫዊ ሓይሎች ምን ምን ነቸዉ? የመማር ደረጃ ላይ ሊደርሱ ያልቻሉ ተማሪዎችን ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ተመሳሳይ ብቃት እንዲኖራቸው ደገሞ የተለየ ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል። ስለዚህ ተማሪዎች የተለየ የትምህርት ክፍለ ጊዜ በማዘጋጀት በእረፍት ሰዓታቸው የሚሰሩትን ሥራ በመስጠት እንዲሰሩ በማገዝ የተለየ ድጋፍ ማድረግ ነው። የተሻለ ውጤት ያገኙ ተማሪዎች ባገኙት ውጤት በመኩራራት ወደኋላ እንዳይመልሱ ማበረታታት እና መከታተል አስፈላጊ ነው።

## የመልመጃ 1.1.2 ጥያቄዎች መልስ

1. የመሬትን ገፅታ የሚቀይሩ የመሬት ውጫዊ ኃይሎች የሚባሉት እንደ አዉሎ ንፋስ፤ የውሃ ጎርፍና የበረዶ መንሸራተት ነቸዉ።

2. በመሬት ገፅታ ላይ የሚታዩ ለዉጦች እንደ ሸለቆ ፤ዴልታ፤ባርኬን፤ የመሬት መቦርቦርና የመሳሰሉት ናቸው።

# 1.2. በከባቢ አየር ውስጥ የሚገኙ ይዘቶች

## 1.2.1 የከባቢ አየር ይዘቶች

**ለዚህ ርዕስ ትምህርት የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት**……………………..…2

ተማሪዎች ቢያንስ ሊደርሱበት የሚገባ የመማር ብቃት

ከዚህ ርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡

- የከባቢ አየር ይዘቶች ባህሪያትን ይገልፃሉ።
- የከባቢ አየር ባህሪያትን ያደንቃሉ።
- ከባቢ አየር የሚቀየርባቸዉ ምክንያቶችን ይለያሉ።

## ቅድመ ዝግጅት

ይህንን ርዕስ ለማስተማር ከመጀመሪያ በፊት ስለከባቢ አየር ይዘቶች የሚያሳይ ሠንጠረዥ ማዘጋጀት ያስፈልጋል። ይህ ትምህርት ለተማሪዎች ሊከብዳቸዉ ስለሚችል የተለያዩ አጋዥ መፅሃፍትን በማንበብ በቂ ዝግጅት ማድረግና አዳዲስ ቃላት ፍቺ ቀድሞ ማዘጋጀት ነው። የተለያዩ የከባቢ አየር ይዘቶችን የሚያሳይ ሠንጠረዥ ፤ጥያቄዎችንና አጫጭር ማስተወሻዎችን ማዘጋጀት ጥሩ ነዉ።

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

የዚህን ርዕስ ትምህርት የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን በመጠቀም ማስተማር ይቻላል። እነዚህም ዘዴዎች በገለፃ፤ በጥያቄና መልስ እንዲሁም በውይይት መልክ ሊሆን ይችላል። መምህራን ተማሪዎች ሊደርሱበት የሚገባቸዉን የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ ለማድረግ ተማሪዎችን የሚያነቃቃ ዘዴዎችን መምረጥ ይጠበቅቦታል። በዚህ ትምህርት ውስጥ ተማሪዎች እንዲገነዘቡ የሚፈለገዉ ስለ ከባቢ አየርና በውስጣቸዉ የሚገኙ ይዘቶች ነዉ።

## ልዩ ተሠጥዖ እና ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

ልዩ ችሎታ እና ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማበረታታት አስፈላጊ ነው። ውይይቱን ከሌሎች ተማሪዎች ቀድሞ ቶሎ መጨረስ ስለሚችሉ ርእሱን የበለጠ ሊያስገነዝባቸው የሚያስችል ጥያቄዎችን በማዘጋጀትና መስጠት ያስፈልጋል ። በክፍል ውስጥ ያሉ በትምህርት አቀባበላቸው ፈጣን ያልሆኑ እና ሴት ተማሪዎችን ደግሞ ተጨማሪ ሥራን እንዲሰሩ ማድረግና ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት እንዲደርሱ ማድረግ መረሳት የለለበት ጉዳይ ነዉ።

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ ለማወቅ ተከታታይነት ያለው ክትትል ማድረግ አስፈላጊ ነው፤፡ የተማሪዎችን ችሎታ በመለየት የሚያስፈልጋቸውን እገዛ ማድረግ ነው። ለምሳሌ በከባቢ አየር ውስጥ የሚገኙ ይዘቶች ምን ምን እንደሆኑ እንዲናገሩ ማድረግና የመሳሰሉት ጥያቄዎችን በመጠየቅ ግንዛቤያቸውን ማረጋገጥ ይጠበቅቦታል።

ሁሉም ተማሪዎች ቢያንስ ሊደርሱበት የሚገባቸው የብቃት ደረጃ ላይ እንድ,ዲደርሱ ለማድረግ ጥያቄዎችን መጠየቅ በክፍል ውስጥ ባላቸዉ ተሳትፎ፣ በውይይት ጊዜ ለክፍላቸው ጓደኞች በሚያቀርቡት ሪፖርት፣ የቤት ስራን ሰርተዉ እንዲመጡ በማድረግ፣የቃል ጥያቄዎችን በመጠቀም ችሎታቸዉን መገምገም ያስፈልጋል፡፡

## የመልመጃ 2.1 ጥያቄዎች መልስ

1. ከባቢ አየር ይዘቶች የተለያዩ ጋሶች፣ የዉሃ ትነትና የአቧር ቅይጥ ናቸዉ፡፡

2. ከባቢ አየር ባላቸዉ ሙቀትና ይዘቶች ላይ በመመርኮዝ በተለያዩ ንብርብሮች ይከፈላል፡፡ እነሱም ትሮፐስፌር፣ እስትራቶስፌር፣ ሜሶስፌርና ቴርሞስፌር ናቸዉ፡፡ከባቢ አየር ብዙ ጠቀሜታ አለዉ፡፡ ለምሳሌ በእስትራቶስፌር ውስጥ የኦዞን በውስጡ ውጦ ስለሚያስቀር ከፀሓይ የሚመጣዉ አልተራቫዮሌት ጨረር ህይወት ያላቸዉን እንዳይጎዳ ያደርጋል፡፡ ትሮፖስፌር ዝናብና እርጥበትን በውስጡ ስለሚይዝ ጠቀሜታ አለዉ፡፤

## 1.2.2 የከባቢ አየር ንብርብሮች

**ለዚህ ርዕስ ትምህርት የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛ…………… ………2**

ተማሪዎች ቢያንስ ሊደርሱበት የሚገባ የመማር ብቃት


ከዚህ ርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡

- የከባቢ አየር ንብርብሮችና ባህሪያቸዉ ምንነት ይገልፃሉ፡፡
- የከባቢ አየር ንብርብሮች ጥቅምን ይናገራሉ፡፡
- በከባቢ አየር ንብርብሮች ውስጥ ያለውን የሙቀት ልዩነት ይናገራሉ፡፡

### ቅድመ ዝግጅት

የዚህን ርዕስ ትምህርት ለማስተማር በመጀመርያ የሚያስፈልጉ ቅድመ ዝግጅቶችን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ትምህርቱን ተጨባጭ ለማድረግ ይህንን ትምህርት የሚገልጹ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ከዚህ በታች ያለዉን ግራፍ በትልቅ ወረቀት ላይ በማዘጋጀት መጠቀም

ነዉ። በተጨማሪም ይህንን ርዕስ ለማስተማር ከዚህ ርዕስ ጋር የሚያያዙ የተለያዩ መፅሃፍቶችን በማንበብ በቂ የሆነ እዉቀት መያዝ ይጠበቅቦታል።




## ሥዕል 1.1 የከባቢ አየር ንብርብሮች

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

የዚህን ርዕስ ትምህርት የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን በመጠቀም ማስተማር ይቻላል። እነዚህም ዘዴዎች በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ እንዲሁም በውይይት መልክ ሊሆን ይችላል። መምህራን ተማሪዎች ሊደርሱበት የሚገባቸዉን የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ ለማድረግ ተማሪዎችን የሚያነቃቃ ዘዴዎችን መምረጥ ይጠበቅባቸዋል። በዚህ ትምህርት ውስጥ ተማሪዎች እንዲገነዘቡ የሚፈለገዉ የከባቢ አየር ንብርብሮች ምን እንደሆኑና የክፍፍላቸው መሠረት ምን እንደሆነ እንዲሁም ባህርያቸውን እንዲያውቁ ነዉ።

## ልዩ ተሠጥዖ እና ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

ልዩ ችሎታ እና ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማበረታታት አስፈላጊ ነው። ውይይቱን ከሌሎች ተማሪዎች ቀድሞ ቶሎ መጨረስ ስለሚችሉ ርእሱን የበለጠ ሊያስገነዝባቸው የሚያስችል ጥያቄዎችን በማዘጋጀትና መስጠት ያስፈልጋል ። በክፍል ውስጥ ያሉ በትምህርት

አቀባበላቸው ፈጣን ያልሆኑ እና ሴት ተማሪዎችን ደግሞ ተጨማሪ ሥራን እንዲሰሩ ማድረግና ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት እንዲኖራቸው ማድረግ ነዉ፡፡

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ ለማወቅ ተከታታይነት ያለው ክትትል ማድረግ አስፈላጊ ነው፤፡ የተማሪዎችን ችሎታ በመለየት የሚያስፈልጋቸውን እገዛ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ለምሳሌ የተለያዩ ጥያቄዎችን ፤ ከባቢ አየር ንብርብሮች የሚባሉት ምን ምን ናቸዉ? እና መገኛቸው፤ እንዲሁም ያላቸው የሙቀት ሁኔታ እና የመሳሰሉትን በመጠየቅ ግንዛቤያቸዉን መረዳት ይቻላል፡፡

## የመልመጃ 1.1.2 ጥያቄዎች መልስ

1. የከባቢ አየር ንብርብሮች በአራት ይከፈላሉ፡፡ ትሮፖስፌር፤ እስትራቶስፌር፤ ሜሶስፌርና ቴርሞስፌር ናቸዉ፡፡
2. ከባቢ አየር ብዙ ጥቅሞች አሉት፡፡ ከነዚህም ውስጥ ዳመናና ዝናብ የሚፈጠርበት ቦታ፤ለመኖር የሚያግዙ አየር ምንጭ፤ ለአየር ማጓጓዣና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡

## 1.3. የአየር ንብረትና የአየር ሁኔታን የሚቆጣጠሩ ነገሮች

**ለዚህ ርዕስ ትምህርት የተሰጠው የክፍል ጊዜ ብዛት…………… ………2**

ተማሪዎች ቢያንስ ሊደርሱበት የሚገባ የመማር ብቃት

ከዚህ ርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡

- የአየር ንብረትና የአየር ሁኔታን ልዩነት ይለያሉ፡፡
- አየር ንብረትን የሚቆጠጠሩ ነገሮችን ይለያሉ፡፡
- በደጋ፤ በወይና ደጋና በቆላማ አከባቢ የዝናብና ሙቀት ልዩነትን በማወዳደር የገልፃሉ፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

የዚህን ርዕስ ትምህርት ለማስተማር በመጀመርያ የሚያስፈልጉ ቅድመ ዝግጅቶችን በማድረግ ትምህርቱን ተጨባጭ ለማድረግ ከዚህ ርዕስ ጋር የሚሄዱ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

እንደ ካርታና ሠንጠረዥ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ የአከባቢያቸውን ተጨባጭ ሁኔታን መሰረት በማድረግ ስለ አየር ንብረትና የአየር ሁኔታን ማስተማር ይቻላል፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

የዚህን ርዕስ ትምህርት የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን በመጠቀም ማስተማር ይቻላል፡፡ እነዚህም ዘዴዎች በፕሮጀክት፤ በገለፃ፤ በጥያቄና መልስ እንዲሁም በውይይት መልክ ሊሆን ይችላል፡፡ መምህራን ተማሪዎች ሊደርሱበት የሚገባቸዉን የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ ለማድረግ ተማሪዎችን የሚያነቃቃ ዘዴዎችን መምረጥ ይጠበቅቦታል፡፡ በዚህ ትምህርት ውስጥ ተማሪዎች እንዲገነዘቡ የሚፈለገዉ የአየር ንብረትና የአየር ሁኔታን መለየት ነዉ፡፡

## ልዩ ተሠጥዖ እና ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

ልዩ ችሎታ እና ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማበረታታት አስፈላጊ ነው፡፡ ውይይቱን ከሌሎች ተማሪዎች ቀድሞ ቶሎ መጨረስ ስለሚችሉ ርእሱን የበለጠ ሊያስገነዝባቸው የሚያስችል ጥያቄዎችን በማዘጋጀትና መስጠት ያስፈልጋል ፡፡ በክፍል ውስጥ ያሉ በትምህርት አቀባበላቸው ፈጣን ያልሆኑ እና ሴት ተማሪዎችን ደግሞ ተጨማሪ ሥራን እንዲሰሩ ማድረግና ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት እንድዲደርሱ ማድረግ መረሳት የሌለበት ጉዳይ ነዉ፡፡

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ ለማወቅ ተከታታይነት ያለው ክትትል ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ የተማሪዎችን ችሎታ በመለየት የሚያስፈልጋቸውን እገዛ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ለምሳሌ የተለያዩ ጥያቄዎችን እንደ የአየር ንብረትና የአየር ሁኔታ ልዩነት ምንድነዉ?የአየር ንብረት በተፈጥሮአዊ አከባቢ ላይ የሚያመጠዉ ተፅእኖ ምንድነዉ? የአየር ንብረትና የአየር ሁኔታን የሚቆጣጠሩ ነገሮች ምንድናቸዉ? የሚሉትን በመጠየቅ ግንዛቤያቸዉን መሻሻል ይገባል፡፡ ተማሪዎች ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ማግኘት ያልቻሉትን የተለየ እገዛ በማድረግ ግንዛቤያቸዉን እንድያሻሽሉ ማድረግ ነው፡፡

## 1.3.3 የአየር ንብረትና የአየር ሁኔታን የሚቆጣጠሩ ነገሮች

**ለዚህ ርዕስ ትምርት የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት**..............................2

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊደርሱበት የሚገባ የመማር ብቃት**

ከዚህ የርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡

- በደጋ፤ በወይና ደጋና በቆላማ አከባቢዎች የዝናብና ሙቀት ልዩነት በምን ምክንያት እንደሚፈጠር ይረዳሉ።
- የአከባቢያቸዉን የአየር ሁኔታን ለይተዉ ይናገራሉ።
- የአየር ንብረትና የአየር ሁኔታን የሚቆጣጠሩ ነገሮችን ይዘረዝራሉ።

## ቅድመ ዝግጅት

የዚህን ትምህርት ርዕስ ለማስተማር ከመጀመርዎ በፊት ለዚህ ርዕስ የሚስማሙ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን፤ የዓለም የከባቢ አየር ስርጭት የሚያሳይ ካርታን ማዘጋጀትና በቂ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል።

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

የዚህን ርዕስ ትምህርት የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን በመጠቀም ማስተማር ይቻላል። እነዚህም ዘዴዎች በፕሮጀክት፤ በገለፃ፤ በጥያቄና መልስ እንዲሁም በውይይት መልክ ሊሆን ይችላል። መምህራን ተማሪዎች ሊደርሱበት የሚገባቸዉን የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ ለማድረግ ተማሪዎችን የሚያነቃቃ ዘዴዎችን መምረጥ ይጠበቅባቸዋል። በዚህ ትምህርት ውስጥ ተማሪዎች እንዲገነዘቡ የሚፈለገዉ የአየር ንብረትና የአየር ሁኔታን የሚቆጣጠሩ ነገሮችን መረዳት ነዉ።

## ልዩ ተሠጥዖ እና ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

ልዩ ችሎታ እና ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማበረታታት አስፈላጊ ነው። ውይይቱን ከሌሎች ተማሪዎች ቀድሞ ቶሎ መጨረስ ስለሚችሉ ርእሱን የበለጠ ሊያስገነዝባቸው የሚያስችል ጥያቄዎችን በማዘጋጀት መስጠት ያስፈልጋል ። በክፍል ውስጥ ያሉ በትምህርት አቀባበላቸው ፈጣን ያልሆኑ እና ሴት ተማሪዎችን ደግሞ ተጨማሪ ሥራን እንዲሰሩ ማድረግና ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ።

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ ለማወቅ ተከታታይነት ያለው ክትትል ማድረግ አስፈላጊ ነው። የተማሪዎችን ችሎታ በመለየት የሚያስፈልጋቸውን እገዛ ማድረግ ነው።ለምሳሌ የተለያዩ ጥያቄዎችን እንደ የአየር ንብረትና የአየር ሁኔታ የሚቆጣጠሩ ነገሮች ምን ምን ናቸዉ?የአየር ንብረት ተፈጠጥረሮ አከባቢ ላይ የሚያመጠዉ ተፅእኖ ምንድነዉ? የሚሉትን በመጠየቅ ግንዛቤያቸዉን መሻሻል ይገባል። ሁሉም ተማሪዎች የሚጠበቅባቸዉን የመማር ብቃት ላይ መድረስ አለባቸዉ። ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ማግኘት ያልቻሉትን የተለየ እገዛ በማድረግና ግንዛቤያቸዉን እንድያሻሽሉ ማድረግ ያስፈልጋል።

## 1.3.4. የአየር ንብረትና የአለም ሙቀት

**ለዚህ ርዕስ ትምህርት የተሰጠው የክፍል ጊዜ ብዛት**.................. .........2

ተማሪዎች ቢያንስ ሊደርሱበት የሚገባ የመማር ብቃት

ከዚህ ርዕስ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች፡

- በትምህርት ቤታቸዉ አከባቢ የዕለት ተዕለት የአየር ሁኔታን በመከታተል ይገልፃሉ።
- በመምህራን የሚሰጡ ዓመታዊ የሙቀት መጠን በግረፍ ማሳየት ይችላሉ።

## ቅድመ ዝግጅት

የዚህን ትምህርት ርዕስ ለማስተማር ከመጀመርዎ በፊት ለዚህ ርዕስ የሚስማሙ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን፤ የዓለም የአየር ስርጭትን የሚያሳይ ሠንጠረዥና ካርታን ማዘጋጀት እንዲሁም ከዚህ ርዕስ ጋር የሚያያዙ የተለያዩ መፅሓፍትን በማንበብ በቂ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል።

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

የዚህን ርዕስ ትምህርት የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን በመጠቀም ማስተማር ይቻላል። እነዚህም ዘዴዎች በፕሮጀክት፤ በገለፃ፤ በጥያቄና መልስ እንዲሁም የቡድን በውይይት መልክ ሊሆን ይችላል። መምህር ተማሪዎች ሊደርሱበት የሚገባቸዉን የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ ለማድረግ ተማሪዎችን የሚያነቃቃ ዘዴዎችን መምረጥ ይጠበቅቦታል። በዚህ ትምህርት ውስጥ ተማሪዎች እንዲገነዘቡ የሚፈለገዉ የአየር ንብረትና የአለም ሙቀት ላይ በቂ እዉቀት እንዲያገኙ ማድረግ ነዉ።

## ልዩ ተሠጥዖ እና ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

ልዩ ችሎታ እና ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማበረታታት አስፈላጊ ነው፡፡ ውይይቱን ከሌሎች ተማሪዎች ቀድሞ ቶሎ መጨረስ ስለሚችሉ ርእሱን የበለጠ ሊያስገነዝባቸው የሚያስችል ጥያቄዎችን በማዘጋጀትና መስጠት ያስፈልጋል ፡፡ በክፍል ውስጥ ያሉ በትምህርት አቀባበላቸው ፈጣን ያልሆኑ እና ሴት ተማሪዎችን ደግሞ ተጨማሪ ሥራን እንዲሰሩ ማድረግና ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ፡፡

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ ለማወቅ ተከታታይነት ያለው ክትትል ማድረግ አስፈላጊ ነው፤፡ የተማሪዎችን ችሎታ በመለየት የሚያስፈልጋቸውን እገዛ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ለምሳሌ የተለያዩ ጥያቄዎችን እንደ የአየር ንብረትና የአለም ሙቀትእንዴት ይፈጠራል? የሚሉትን በመጠየቅ ግንዛቤያቸዉን መሻሻል ይገባል፡፡ ሁሉም ተማሪዎች የሚጠበቅባቸው የመማር ብቃት ላይ መድረስ አለባቸዉ፡፡ ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ማግኘት ያልቻሉትን የተለየ እገዛ በማድረግ፤ ቲቶሪያል በማዘጋጀት ማስተማርና ግንዛቤያቸዉን እንድያሻሽሉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## የምዕራፍ አንድ የማጠቃለያ ጥያቄዎች

### I. የምርጫ ጥያቄዎች መልስ

1. ሐ 2. ሐ 3. መ

### II. አዛምድ ጥያቄዎች መልስ

1. መ 2. ሰ 3. ሠ 4. ረ 5. ቀ 6. ሀ 7. ለ

# ምዕራፍ ሁለት

## ህዝብ ፡ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች

**ለዚህ ምዕራፍ የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት** ……..………….27

### የምዕራፉ የመማር ውጤቶች

### ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች፣

ከጊዜ ወደ ጊዜ ያለዉን የህብረተሰቡን የባህል እድገትና ለውጥ ይገልፃሉ።

- የባህል መገለጫ የሆኑትን እንደ ቋንቋና ሀይማኖት ይገልፃሉ።
- ግሎባላይዜሽን በኅብረተሰቡ ባህል ለውጥ ላይ ያለውን ጠፅዕኖ ይገነዘባሉ።
- ለአካባቢያዊ እውቀት እውቅና ይሰጣሉ።
- የተለያዩ ሀገሮች ኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችና የእድገት ደረጃቸዉን በማወዳደር ይገልፃሉ።
- ያደጉና በማደግ ላይ ያሉ አገሮችን የእርሻ እድገት ደረጃ በማወዳደር ይገልፃሉ።
- የምርት፣ የመረጃ ስርጭትና ማህበራዊ አገልግሎቶችን ይገልፃሉ።
- የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች በአገር እድገት ላይ ያለዉን ተፅዕኖ ይገነዘባሉ።
- ግብርና ታክስ ያላቸዉን ጠቀሜታ ይገልፃሉ።
- የመንግስት ታክስና ግብር ምንነት ይገልፃሉ።

## መግቢያ

በምዕራፍ አንድ ትምህርት ውስጥ ተማሪዎች የመሬት ገፅታን የሚቀይሩ ሀይሎችን፣ ስለከባቢ አየር፣ የአየር ንብረትና የአየር ሁኔታን የሚቆጣጠሩ ነገሮችን መማራቸዉ ይታወቃ።በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ደግሞ የባህል ልዩነቶችና ለውጦች፣ የኅህበረሰቡን የባህል የዕድገት ደረጃ፣ የባህል መገለጫዎች፣ የአለም የሙቀት መጨመር፣ ዋና ዋና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች፣ ገበያ፣የመነንግስት ግብር፣ የምርት አቅርቦትና ፍላጎት በኢኮኖሚ ላይ ያለዉ ተፅዕኖ፣ የገበያ ውድድር፣ ታክስና ግብር ለአገር  እድገት ያለዉ ጠቀሜታን ይማራሉ።

## 2.1. የባህል ልዩነትና ለውጦች

**ለዚህ ርዕስ የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት**.............................. .........4

ተማሪዎች ቢያንስ ሊደርሱበት የሚገባ የመማር ብቃት

ከዚህ ርዕስ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች፡

- ለባህል እድገት ምክንያት የሆኑትን ይገልፃሉ፡፡
- ቋንቋ፤ ሀይማኖትና የኅህበረተሰብ ማንነትና የባህል መገለጫዎች መሆናቸዉን ይገልፃሉ፡፡
- ግሎባላይዜሽን በባህል መቀየር ላይ ያለዉን ተፅዕኖ ይናገራሉ፡፡

### ቅድመ ዝግጅት

ይህንን ርዕስ ለማስተማር መደረግ ያለበት ቅድመ ዝግጅት በመጀመሪያ መስፈርቱን ያሟላ የትምህርት እቅድ ማዘጋጀት ነዉ፡፡ የተማሪዎች መፅሓፍና ከትምህርቱ ጋር የሚያያዙ የተለያዩ ማጣሻ መፅሓፍትን በማንበብ በቂ ግንዛቤ መያዝ ይጠበቅቦታል፡፡ በተጨማሪም ትምህርቱን ተጨባጭ ለማድረግ የሚያስፈልጉ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ለምሳሌ እንደ ፎቶዎች፤ ሥዕሎችና ሰንጠረዥዎችን ማዘጋጀትና መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

### የመማር ማስተማር ዘዴዎች

የዚህን ርዕስ ትምህርት ለማስተማር ከመጀመዎ በፊትት የተማሪዎችን ግንዛቤ መፈተሽ ያስፈልጋል፡፡ ተማሪዎች የሚያዉቁትን ነገር እንዲናገሩ በጥያቄና መልስ መጀመር፡፡ ለምሳሌ ባህል ማለት ምን ማለት ነዉ? የምታዉቁትን የባህል ዓይነቶች ተናገሩ? የሰዉ ልጅ ባህልን የሚያሳድገዉ እንዴትነዉ? ሀይማኖትና ቋንቋ እንዴት ለባህል ልዩነት ምክንያት ይሆናሉ?**እና** የመሳሰሉትን ጥያቄዎችን መጠቀም ነው፡፡

የተማሪዎችን ግንዛቤ ላመጨመር የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን በመጠቀም ማስተማር ይቻላል፡፡ እነዚህም ዘዴዎች በገለፃ፤ በጥያቄና መልስ እንዲሁም የቡድን ውይይት ሊሆን ይችላል፡፡ መምህር ተማሪዎች ሊደርሱበት የሚገባቸዉን የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ ለማድረግ ተማሪዎችን የሚያነቃቃ ዘዴን መምረጥ ይጠበቅቦታል፡፡ በዚህ ትምህርት ውስጥ ተማሪዎች እንዲገነዘቡ የሚፈለገዉ በአየር ንብረትና የአለም ሙቀት ላይ በቂ እዉቀት እንዲይዙ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## ልዩ ተሠጥያና ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

ልዩ ችሎታ እና ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማበረታታት አስፈላጊ ነው። ውይይቱን ከሌሎች ተማሪዎች ቀድሞ ቶሎ መጨረስ ስለሚችሉ ርእሱን የበለጠ ሊያስገነዝባቸው የሚያስችል ጥያቄዎችን በማዘጋጀት መስጠት ያስፈልጋል ። ለምሳሌ በግሎባላይዜሽን ምክንያት የህብረተሰባችን ባህል ወዴት ሊቀየር ይችላል? በባህል፣ በቋንቋና በሀይማኖት መካከል ያለዉ ግንኙነት ምንድነዉ? የሚሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ተማሪዎች በጥልቀት የማሰብና ችግር የመፍታት ችሎታቸዉን እንድያሳድጉ ማድረግ ይቻላል።

በክፍል ውስጥ ያሉ በትምህርት አቀባበላቸው ፈጣን ያልሆኑ እና ሴት ተማሪዎችን ደግሞ ተጨማሪ ሥራን እንዲሰሩ ማድረግና ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ።

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ ለማወቅ ተከታታይነት ያለው ክትትል ማድረግ አስፈላጊ ነው። የተማሪዎችን ችሎታ በመለየት የሚያስፈልጋቸውን እገዛ ማድረግ ነው።ለምሳሌ የተለያዩ ጥያቄዎችን እንደ ባህል ምንደነዉ? ባህል ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የሚሰራጨዉ እንዴት ነዉ? ግሎባላይዜሽን ለባህል ለውጥ እንዴት ምክንያት ይሆናል? የሚሉትን በመጠየቅ ግንዛቤያቸዉን መሻሻል ይገባል። ሁሉም ተማሪዎች ሊደርሱበት የሚገባቸዉን የመማር ብቃት ላይ መድረስ አለባቸዉ። ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ማግኘት ያልቻሉትን የተለየ እገዛ በማድረግ፣ ቲቶሪያል በማዘጋጀት ማስተማርና ግንዛቤያቸዉን እንድያሻሽሉ ማድረግ መርዳት ነው።

## የመልመጃ 2.1 ጥያቄዎች መልስ

1. ባህል የህብረተሰብ የአኗኗር ዘይቤ ወይም አንድ ማህበረሰብ ያለዉ የእዉቀት ደረጃ ነዉ።
2. በሀገራችን ባህል እንደ ብሔር ብሔረሰባችን ብዛት የአመጋገብ፣ የአለባበስ፣ የጋብቻ ሥርዓት፣ የደስታና ሀዘን መግለጫ ልዩነት አለዉ።
3. በማህበረሰባችን ውስጥ ጠቃሚ ባህሎች እንዳሉ ሁሉ ጎጂ ልምዶችም አሉ። ለምሳሌ የሴት ልጅ ግርዛት፣ ያለእድሜ ጋብቻ፣ ግግ ማዉጣት፣ ድድ መፈልፈልና የመሳሰሉት ናቸዉ።
4. ባህል ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በንግድ፣ በትምህርት፣ ወይም በቴክኖሎጂ ምክንያት ልሰራጭ ይችላል።

5. በግሎባላይዜሽን ምክንያት የአለም ህዝብ መረጃን በመለዋወጥ፤ በተለያዩ ምክንያት ግንኙነት በመፍጠር የቴክኖሎጂና የባህል ልውውጥ ያደርጋሉ፡፡ በዚህ ምክንያት በማህበረሰብ ባህል ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ይደርሳል፡፡ ይህ ማለት ቀስ በቀስ አንዱ ሌላውን ሊያጠፈው ይችላል፡፡

## 2.2 ዋና ዋና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች

**ለዚህ ርዕስ ትምህርት የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት……….. ……….14**

## 2.2.1. አንደኛ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ

**ለዚህ ርዕስ ትምህርት የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት…………… ………5**

ተማሪዎች ቢያንስ ሊደርሱበት የሚገባ የመማር ብቃት

ከዚህ ርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡

- የመጀመሪያ ደረጃ የኢኮኖሜ እንቅስቃሴ ምንነት ይገልፃሉ፡፡
- የመጀመሪያ ደረጃ የኢኮኖሜ እንቅስቃሴ ባህሪያትን ይዘረዝራሉ፡፡
- የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታን መሰረት በማድረግ የመጀመሪያ ደረጃ የአኮኖሜ እንቅስቃሴን ይገልፃሉ፡፡
- እርሻ ባደጉና በማደግ ላይ ባሉ አገሮች መካከል ያለዉን ልዩነት ይገልፃሉ፡፡
- በአከባቢያቸዉ የሚከናወኑ ሥራዎች በየትኛዉ ደረጃ የኢኮኖሜ እንቅስቃሴ ውስጥ እንደሚመደብ ይለያሉ፡፡

### ዋና ዋና ነጥቦች

የዚህ ርዕስ ዋና ትኩረት የሰዉ ልጅ ከጥንት ጀምሮ ሲያካሄዱ የነበረና በአሁኑ ጊዜም የራሳቸዉን ፍላጎት ለሟሟላት እያከናወኑ ያሉትን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ ተማሪዎች የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች በተለያየ መንገድ ሊከፈል እንደሚችል፤ እነሱም በዚህ ትምህርት ውስጥ የመጀመሪያ ደረጃ፤ ሁለተኛ ደረጃና ሶስተኛ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ተብለዉ እንደሚከፈሉ እንዲረዱ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ሌላዉ ነጥብ እርሻ በማደግ ላይ ላሉ ሀገሮች ዋና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ መሆኑን መረዳት አለባቸዉ፡፡በዝሁ መሳረት ተማሪዎች በአከባቢያቸዉ የሚገኙ ኅብረተሰብ በምን ዓይነት ሥራ ላይ እንደተሰማራ እንዲናገሩ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

የዚህን ርዕስ ትምህርት ለማስተማር የኢኮኖሚ እንቅስቃሴን የሚያሳዩ የተለያዩ መርጃ መሳሪያዎችን እንደ የአለም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ሥርጭትን የሚያሳይ ካርታ፤ ቻርቶችና ሥዕሎች ማዘጋጀት ያስፈልጋል። የእርሻ፤ የደን ሥራ፡ ከተቻለ ዓሳን መስገርና ሌሎችንም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን የሚያሳይ ቪድዮዎችን በማዘጋጀት ታማሪዎቹ ትምህርቱን በደንብ እንዲገነዘቡ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ።

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

ይህንን ርዕስ ለማስተማር ከመጀመረዎ በፊት ተማሪዎች ያለቸዉን ግንዛቤ ምን እንደሆነ መጠየቅ ያስፈልጋል። ከተማሪዎች መፅሓፍና ከሌሎች ማጣቀሻ መፅሓፍት በማንበብ በቂ እዉቀት መያዝ ያስፈልጎታል። ተማሪዎች የሚያዉቁትን እንዲናገሩ በጥያቄና መልስ መጀመር ነው። ለምሳሌ የመጀመሪያ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ማለት ምን ማለት ነዉ? ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ የሚባሉ ሌሎች ሥራዎች ምን ምን ናቸዉ? የእርሻ ሥራ ባደጉና በማደግ ላይ ባሉት ሀገሮች ምን ይመስላል? ዓሳን ማስገርና ማዕድናትን ማዉጣት ምን ዓይነት ሥራ እንደሆነ ተማሪዎችን መጠየቅ ይቻላል። ለዚህ ርዕስ ምቹ የሆነ የመማር ዘዴን በመምረጥ ከአከባቢያቸዉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማያያዝ ተማሪዎች ትምህርታቸዉን በትክክል እንዲከታተሉ ማበረታታት አስፈላጊ ነዉ።

## ልዩ ተሠጥዖ እና ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

ልዩ ችሎታ እና ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማበረታታት አስፈላጊ ነው። ውይይቱን ከሌሎች ተማሪዎች ቀድሞ ቶሎ መጨረስ ስለሚችሉ ርእሱን የበለጠ ሊያስገነዝባቸው የሚያስችል ጥያቄዎችን በማዘጋጀትና መስጠት ያስፈልጋል ።በክፍል ውስጥ ያሉ በትምህርት አቀባበላቸው ፈጣን ያልሆኑና ሴት ተማሪዎችን ደግሞ ተጨማሪ ሥራን እንዲሰሩ ማድረግና ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ።

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች የዚህን ርዕስ ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ ለማወቅ የተለያዩ ጥያቄዎችን ላምሳሌ የመጀመሪያ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ማለት ምን ማለት ነዉ? በአገራችን በብዛት ህዝቡ የተሰማራበት የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የትኛዉ ነዉ? የደን ሥራ፤ ማዕድን ማዉጣትንና፤ የእርሻ ሥራ በየትኛው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ ይመደባሉ ? ምክንያቱስ ? የሚሉትን መጠየቅ፡፡ ሁሉም ተማሪዎች የሚጠበቅባቸዉን የመማር ብቃት ላይ መድረስ አለባቸዉ፡፡ ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ማግኘት ያልቻሉትን የተለየ እገዛ በማድረግ፤ ቲቶሪያል በማዘጋጀት ማስተማርና ግንዛቤያቸዉን እንድያሻሽሉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## የመልመጃ 2.2 ጥያቄዎች መልስ

1. የመጀመሪያ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የሚባሉት እንደ እርሻ፤ ዓሳ ማስገር፤ ማዕድናትን ማዉጣት፤ የደን ሥራዎችና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡
2. ከመጀመሪያ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ሰዎች በብዛት የተሰማሩበት የእርሻ ሥራ ነዉ፡፡
3. እርሻ በማደግ በሉ አገሮች ውስጥ ዋነኛዉ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ነዉ፡፡ የምግብ እህልና ለውጪ ምንዛሬ  የሚሆኑ ወይንም ገበያ እህሎችን ያመርታሉ፡፡
4. እርሻ በደጉት ሀገራት የሚከናወነዉ በቴክኖሎጂ በመታገዝ ሲሆን በማደግ ላይ ባሉት ሀገራት ግን በሰዉ ጉልበትና በባህላዊ መልክ ነዉ፡፡
5. የደን ሥራ እንደ ጣዉላ ማምረት፤ ከሰልና የማገዶ እንጨትን ለማግኘት ይጠቅማል፡፡ ዓሳን ማስገር ማለት ደግሞ በሐይቆች፤ በወንዞችና በባህሮች ላይ በባህላዊም ሆነ በዘመናዊ መልክ የሚከናወን ነዉ፡፡ ማዕድናትን ማዉጣት ማለት ደግሞ የተለያዩ ማዕድናትን እንደ የድንጋይ ከሰል፤ ወርቅ፤ መዳብና የመሳሰሉትን ከመሬት ውስጥ ማዉጣት ነዉ፡፡

## 2.2.2 ሁለተኛ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ዎች

**ለዚህ ርዕስ ትምህርት የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት**.......................... 2

ተማሪዎች ቢያንስ ሊደርሱበት የሚገባ የመማር ብቃት

- የሁለተኛ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ምንነት ይገልፃሉ፡፡
- የሁለተኛ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ባህሪያትን ይናገራሉ፡፡

- በሀገራችን ውስጥ ሁለተኛ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ምን እንደሚመስል ይገልፃሉ።
- በኢትየጵያ የእንድስትሪ ስርጭት ምን እንደሚመስል ይገልፃሉ።
- ባደጉትና በማደግ ላይ ባሉት አገሮች መካከል የሁለተኛ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ያሉትን ልዩነቶችን ይገልፃሉ።

## ዋና ዋና ነጥቦች

የመጀመሪያ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንደ እርሻ ሥራ፤ የደን ሥራ፤ ዓሳ ማስገርና ማዕድናትን ማዉጣትን መማራችዉ ይታወቃል። በዚህ ትምህርት ውስጥ ደግሞ የሁለተኛ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴን ይማራሉ። ሁለተኛ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የምንለዉ ደግሞ እንዱስትሪ ምርት ነዉ።እንዱስትሪ የተለያዩ ጥሬ ዕቃን በመጠቀም በተለያየ መጠንና ጥራት ለሰዎች አገልግሎት በሚሰጥ መልኩ ምርት ማምረት ነዉ። እንዱስትሪ ምርት (Manufuturing industries) በእድገት ደረጃቸው በሁለት የከፈላሉ። እነሱም የጎጆ እንዱስትሪና ዘመናዊ እንዱስትሪ ናቸዉ። ዘመናዊ እንዱስትሪ በሚያመርቱት ምርት ጥራት፤ዋጋና ዘመናዊነት እንደገና ለሁለት ይከፈላል። እነሱም ከባድ እንዱስትሪዎችና አነስተኛ እንዱስትሪዎች ናቸዉ። ከባድ እንዱስትሪዎች በብዛት የሚገኙት ባደጉ አገሮች መሆኑን በትክክል ማስረዳት ያስፈልጋል።

## ቅድመ ዝግጅት

የዚህን ትምህርት ርዕስ ለማስተማር ከመጀመረዎ በፊት ለዚህ ርዕስ የሚስማሙ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን የዓለም ካርታን፤ ሰንጠረዥና ሥዕሎችን ማዘጋጀትና በተጨማሪም ከዚህ ርዕስ ትምህርት ጋር ግንኙነት ያላቸውን የተለያዩ መፅሓፍትን በማንበብ በቂ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልግል።

# የመማር ማስተማር ዘዴዎች

የዚህን ትምህርት ርዕስ ለማስተማር ከመጀመርዎ በፊት በመጀመሪያ ለዚህ ርዕስ የሚስማሙ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን መምረጥ፤ የተማሪዎችን መፅሓፍና ሌሎች የተለያዩ ፅሑፎችን በማንበብ፤ ከኢንተርኔትና በመፈለግ ስለ ሁለተኛ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን በማንበብ

በቂ እዉቀት መያዝና ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል። ተማሪዎች የሚያዉቁትን እንዲገልፁ በጥያቄና መልስ መጀመር አስፈላጊ ነዉ። ለምሳሌ የሁለተኛ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የሆኑትን ተናገር? ባደጉትና በማደግ ላይ ያሉት ሀገሮች መካከል የእንዱስትሪ እድገትና ስርጭት ምን ይመስላል? በሁለተኛ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች የተለያዩ አገሮች መካከል ያለዉ ልዩነት ምን ይመስላል? በማለት መጠየቅ ይቻላል። ሁሉም ተማሪዎች እንድሳተፉ ማበረታተትና መከታተል ያስፈልጋል።

## ልዩ ተሠጥዖ እና ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

ልዩ ችሎታና ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማበረታታት አስፈላጊ ነው። ውይይቱን ከሌሎች ተማሪዎች ቀድሞ ቶሎ መጨረስ ስለሚችሉ ርእሱን የበለጠ ሊያስገነዝባቸው የሚያስችል ጥያቄዎችን በማዘጋጀት መስጠት ያስፈልጋል ። በክፍል ውስጥ ያሉ በትምህርት አቀባበላቸው ፈጣን ያልሆኑ እና ሴት ተማሪዎችን ደግሞ ተጨማሪ ሥራን እንዲሰሩ ማድረግና ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ።

**ተከታታይ ምዘና**

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ ለማወቅ ተከታታይነት ያለው ክትትል ማድረግ አስፈላጊ ነው። የተማሪዎችን ችሎታ በመለየት የሚያስፈልጋቸውን እገዛ ማድረግ አስፈላጊ ነው።ለምሳሌ የተለያዩ ጥያቄዎችን ለምሳሌ፤ የፋብሪካ ዓይነቶች ተናገሩ፤ በሁለተኛ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ አብዘኛዉ ህዝብ ምን ያህል ይሳተፋሉ? በአደጉና በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮች መካከል ያለዉ ልዩነት ምንድነዉ? የሚሉትን በመጠየቅ ግንዛቤያቸዉን መሻሻል ይገባል። ሁሉም ተማሪዎች የሚጠበቅባቸው የመማር ብቃት ላይ መድረስ አለባቸዉ። ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ማግኘት ያልቻሉትን የተለየ እገዛ በማድረግ ግንዛቤያቸዉን እንድያሻሽሉ ማድረግ ያስፈልጋል።መሻሻል ያሳዩ ተማሪዎችን በማድነቅና በመሸለም ማበረታታት ነው።

## የመልመጃ 2.2.2 ጥያቄዎች መልስ

1. ሁለተኛ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች የሚባሉት እንደ መጠገን፤ ማምረት፤ መገንባትና መቀየርን ያጠቃልላል። በሌላ አባባል ከጥሬ ዕቃ ምርትና ለአገልግሎት በሚዉል ምረቶችን ማምረት ማለት ነዉ።

2. የእንዱስትሪ ዓይነቶች ሁለት ሲሆኑ እነሱም ባህላዊና ዘመናዊ እንዱስትሪዎች ናቸዉ።

3. የሁለተኛ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ባህሪያት የተማረ የሰዉ ኃይል ይፈልጋሉ። የሚቋቋሙበት ቦታ ለገበያና ጥሬ ዕቃን ለማግኘት ምቹ መሆን አለበት።

4. የእንዱስትሪ ስርጭትን የሚወስኑ ነገሮች የጥሬ ዕቃ መገኘት፤ የመጓጓዥ መስፋፋት፤ የገበያ መኖር፤ የውሃ መኖር፤ ምቹ የመሬት አቀማመጥና የመሳሰሉት ናቸዉ።

5. በአደጉ አገሮች የእንዱስትሪዎች ባህሪያት ትላልቅ እንዱስትሪዎች በብዛት ተስፋፍተዉ ይገኛሉ፤ ኢኮኖሚያቸዉ በእንዱስትሪ ላይ የተመሰረተ ነዉ። በማደግ ላይ ያሉ አገሮች ደግሞ አነስተኛ እንዱስትሪዎች በብዛት ይገኛሉ፤ ኢኮኖሚያቸዉ በእርሻ ላይ የተመሰረተ ነዉ።

## 2.2.3 ሦስተኛ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች

ለዚህ ርዕስ የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት.............................. .........5

ተማሪዎች ቢያንስ ሊደርሱበት የሚገባ የመማር ብቃት

ከዚህ የርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡

- የሦስተኛ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ምንነት ይገልፃሉ።
- ሦስተኛ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ይዘረዝራሉ።
- የሦስተኛ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ባህሪያትን ይገልፃሉ።
- የንግድ ምንነትና ዓይነቶችን የገልፃሉ።
- ንግድና ትራንስፖርት በኢኮኖሚ ውስጥ ያላቸዉን ጠቀሜታ ይገልፃሉ።
- የትራንስፖርት ዓይነቶችንና ባህሪያቸዉን ይለያሉ።
- የኢትዮጵያ የንግድ ሁኔታ ምን እንደሚመስል ይገልፃሉ።
- ከቱሪዝም ጋረ ተያይዘዉ ሀገራችን ያላት እድል ምን እንደሆነ ይናገራሉ።
- ሦስተኛ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን ባደጉትና በማደግ ላይ ባሉት ሀገሮች መካከል ያለዉን ልዩነት ይገነዝባሉ።

**ዋና ዋና ነጥቦች**

ሦስተኛ ደረጃ የኢኮኖሚ  እንቅስቃሴዎች የሚባሉት የተለያየ አገልግሎት የሚሰጡ እንደ ንግድ፤ ቱሪዝም፤ ትርንስፖርትና የመሳሰሉት ናቸዉ። በሦስተኛ ደረጃ የኢኮኖሚ  እንቅስቃሴ ውስጥ የተለያዩ አገልግሎቶች ይሰጣል እንጂ ምንም ዓይነት ምርት አይመረትም። ንግድ ምርት ከሚመረትበት ቦታ ምርት ወደ ማይገኝበት ቦታ ማድረስ ማለት ነዉ። ንግድ የተጀመረዉ ሰዎች ተመሳሳይ ዕቃዎችን በመቀያየር ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በገንዘብ አገልግሎቶችን በመግዛት ነዉ። ንግድ በአገር  ውስጥ ወይም ከአገር  ውጪ ሊካሄድ ይችላል። ትራንስፖርት፤ ንግድና ቱሪዝም እንድካሄድ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። ቱሪዝም የተለያዩ ታዋቂና ታሪካዊ ቦታዎችን የመጎብኘት ስራ ሲሆን ጭስ አልባ እንዱስትሪ ተብለዉ ይጠራል። በቱሪዝም የሚታዩ የተፈጥሮና ሰዉ ሰራሽ ነገሮች ናቸዉ። በምስራቅ አፍሪካ ኢትዮጵያ፤ ኬኒያና ታንዛኒያ በተፈጥሮ የቱሪዝም መስብ የታደሉ ሀገሮች ናቸዉ።

## ቅድመ ዝግጅት

ይህንን ርዕስ ለማስተማር የሚያስፈልጉ የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን እንደ የዓለም ሀገራትን የሚያሳይ ካርታ ማዘጋጀት ያስፈልጋል። በዚህ ካርታ ላይ ከተቻለ የዓለም የቱሪስት ቦታዎችን ፤ የንግድ መስመሮችን በአህጉራትና በውሃዎች ላይ የሚያሳይ ማዘጋጀት ያስፈልጋል።በተጨማሪም  ትምህርቱን ለማስተማር ተስማሚ የሆነ የመማር ዘዴን መምረጥ ያስፈልጋል።

# የመማር ማስተማር ዘዴዎች

የዚህን ትምህርት ርዕስ ለማስተማር ከመጀመዎ በፊት በመጀመሪያ ለዚህ ርዕስ የሚስማሙ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን መምረጥ፤ የተማሪዎችን መፅሓፍና ሌሎች የተለያዩ ፅሑፎችን በማንበብና ከኢንተርኔት መረጃን መሰብሰብ አስፈላጊ ነዉ።  በተጨማሪም ከአከባቢዉ ቱሪዝምና ትራንስፖርት ፅህፈት ቤት መረጃን በመሰብሰብ ማስተማር ይቻላል። በአከባቢያቸዉ የሚታይ የቱሪዝም መስብ ከለ እንዲመለከቱ ማድረግና ተማሪዎች ከሚየዉቁት እንዲነሱ ለማድረግ ትምህርቱን በጥያቄ መጀመር። ለምሳሌ ንግድና የንግድ ዓይነቶች ምን ምን ናቸዉ? በሦስተኛ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የሚባሉት ምን ምን ናቸዉ?  የትራንስፖርት ዓይነቶች  ምን ምን ናቸዉ?, ሰዎች በብዛት የሚጠቀሙት የትራንስፖርት ዓይነቶች   የትኞቹ ናቸዉ? ቱሪዝም

ምንድነዉ? በማለት መጀመር፡፡ ተማሪዎች ትምህርታቸዉን በትኩረት እንድከታተሉ ማድረግ ማበረታታትና መከታተል አስፈላጊ ነዉ፡፡

## ልዩ ተሠጥዖ እና ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

ልዩ ችሎታ እና ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማበረታታት አስፈላጊ ነው፡፡ ውይይቱን ከሌሎች ተማሪዎች ቀድሞ ቶሎ መጨረስ ስለሚችሉ ርእሱን የበለጠ ሊያስገነዝባቸው የሚያስችል ጥያቄዎችን በማዘጋጀት መስጠት ያስፈልጋል ፡፡ በክፍል ውስጥ ያሉ በትምህርት አቀባበላቸው ፈጣን ያልሆኑ እና ሴት ተማሪዎችን ደግሞ ተጨማሪ ሥራን እንዲሰሩ ማድረግና ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ፡፡

.

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ ለማወቅ ተከታታይነት ያለው ክትትል ማድረግ አስፈላጊ ነው፤፡ የተማሪዎችን ችሎታ በመለየት የሚያስፈልጋቸውን እገዛ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ለምሳሌ የተለያዩ ጥያቄዎችን እንደ የንግድ ዓይነቶች፤ ንግድ በሀገራችን ኢኮኖሚ ውስጥ ያለዉ ድርሻ ምን እንደሆነ፤ መገናኛ ብዙሃን በኢኮኖሚ ውስጥ ያለዉ ጠቀሜታ፤ ባደጉና በማደግ ላይ ያሉት ሀገሮች መካከል ያለዉ የመገናኛ ብዙሃን ልዩነት የሚሉትን በመጠየቅ ግንዛቤያቸዉን መሻሻል ይገባል፡፡ ሁሉም ተማሪዎች የሚጠበቅባቸው የመማር ብቃት ላይ መድረስ አለባቸዉ፡፡ ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ማግኘት ያልቻሉትን የተለየ እገዛ በማድረግ ግንዛቤያቸዉን እንድያሻሽሉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡መሻሻል ያሳዩ ተማሪዎችን በማድነቅና በመሸለም ማበረታታት ነው፡፡

## የመልመጃ 2.2.3 ጥያቄዎች መልስ

1. የሦስተኛ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች የተለያዩ አገልግሎቶችን የሚያጠቃልል ሲሆን እነሱም እንደ ንግድ፤ ቱሪዝም፤ እንሹራንስ፤ ባንክ ፤ሆቴልና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡
2. ንግድ ማለት በሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎችና አገሮች መካከል ዕቃዎችን መሸጥና መግዛትን ማለት ነው፡
3. የአገር ውስጥና ወጪ ንግድ ነዉ፡፡
4. የየብስ ፤ የአየርና የውሃ ትራንስፖርት ናቸዉ፡፡ በሀገራችን ሰዎች በብዛት የሚጠቀሙት የትራንስፖርት ዓይነት የየብስ ላይ ትራንስፖርት ነዉ፡፡

5. የአገራችን የባቡር መንገድ በተወሰነ መስመር ላይ ብቻ የሚደረግ ሲሆን ዕቃን መጫንና ማዉረድ የሚካሄደዉ በመነሻና በመድረሻ ላይ ብቻ ነዉ፡፡

6. የትራንስፖርት ጥቅም ሰዎችንና ዕቃን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ማጓጓዝ ነዉ፡፡

7. አንደኛ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች

8. በማደግ ላይ ያሉ አገሮች የኢኮኖሚ እንቅስቃሴያቸዉ አንደኛ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴና ሁለተኛ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የተመሰረተ ሲሆን ያደጉ ሀገሮች ደግሞ በሁለተኛ ደረጃ ላይ ነዉ፡፡

## 2.2.4. የተለያዩ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ለሃገር እድገት ያላቸዉ ጠቀሜታ

**ለዚህ ርዕስ የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት**…………………… ………2

ተማሪዎች ቢያንስ ሊደርሱበት የሚገባ የመማር ብቃት

ከዚህ ርዕስትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡

- የኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ለአገር እድገት ያለዉ ጠቀሜታን ይናገርሉ፡፡
- ንግድ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ ያለዉ ጠቀሜታን ይገልፃሉ፡፡
- ወደ ውጪ የሚደረግ ንግድ ላይ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ያለዉ ጠቀሜታን ይዘረዝራሉ፡፡
- ትራንስፖርት በአንድ አገር ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ላይ ያለዉ ጠቀሜን ይገልፃሉ፡፡
- ቱሪዝም ለአንድ አገር ያለዉ ጠቀሜታን ይዘረዝራሉ፡፡
- በባደጉና በማደግ ላይ ላሉ ሀገሮች የኢኮኖሚያቸዉ መስረት ምን እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡

# ቅድመ ዝግጅት

ይህንን ርዕስ ለማስተማር የሚያስፈልጉ የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን እንደ የዓለም ሀገራትን የሚያሳይ ካርታ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ የአንድን አገር የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ መሰረት የሆኑትን እንደ ማዕድናት፤ የገበያ እህሎች፤ ቡና፤ የደን ውጤቶችና የመሳሰሉትን የሚያሳይ ቻርት ወይም ሥዕል ማዘጋጀት አስፈላጊ ነዉ፡፡ የተለያዩ እንዱስትሪዎች፤ የቱሪዝም መስቦችና የተለያዩ የመጓጓዣ ዓይነቶችን የሚያሳይ ሥዕሎችን ማዘጋጀት አስፈላጊ ነዉ፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

ይህንን ትምህርት ማስተማር ከመጀመርዎበፊትበተማሪዎች መማሪያ መፅሐፍ ላይ ያለዉን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የሚለዉን በደንብ ማንበብና ከሌሎች ምንጮችም ተጨማሪ መረጃ በመፈለግ መረዳት ያስፈልጋል። ተማሪዎች ከሚያዉቁት እንድነሱ ለማድረግ ስለ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ በቡድን እንድወያዩና የሚዉቁትን እንድናገሩ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ። እርሻ፤ እንዱስትሪ፤ ንግድ፤ መጓጓዣ፤ መገናኛ ብዙሀንና ቱሪዝም በአገር እድገት ላይ ያለዉን ጠቀሜታ እንድናገሩ ማድረግያስፈልጋል። ለዚህ ርዕስ ተስማሚ የሆነ የመማር ማስተማር ዘዴን መከተል ያስፈልጋል።

## ልዩ ተሠጥዖ እና ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

ልዩ ችሎታ እና ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማበረታታት አስፈላጊ ነው። ውይይቱን ከሌሎች ተማሪዎች ቀድሞ ቶሎ መጨረስ ስለሚችሉ ርእሱን የበለጠ ሊያስገነዝባቸው የሚያስችል ጥያቄዎችን በማዘጋጀት መስጠት ያስፈልጋል ። በክፍል ውስጥ ያሉ በዝግታ የሚማሩ እና ሴት ተማሪዎችን ደግሞ ተጨማሪ ሥራን እንዲሰሩ ማድረግና ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ። ተማሪዎች ስለገበያ አቅርቦትና ፍላጎት መካከል ያለዉን ግንኙነት በደንብ እንዲገነዘቡ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ።

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ ለማወቅ ተከታታይነት ያለው ክትትል ማድረግ አስፈላጊ ነው፤፡ የተማሪዎችን ችሎታ በመለየት የሚያስፈልጋቸውን እገዛ ማድረግ አስፈላጊ ነው።ለምሳሌ የተለያዩ ጥያቄዎችን እንደ የንግድ እንዴት ተጀመረ፤ በንግድ ዘርፍ ፍላጎትና አቅርቦት እንዴት ተፅዕኖ ያደርስል፤ የሚሉትን በመጠየቅ ግንዛቤያቸዉን መሻሻል ይገባል። ሁሉም ተማሪዎች የሚጠበቅባቸው የመማር ብቃት ላይ መድረስ አለባቸዉ። ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ማግኘት ያልቻሉትን የተለየ እገዛ በማድረግና በእረፍት ጊዜያቸዉ የሚሰሩትን ሥራዎችን በመስጠት ግንዛቤያቸዉን እንድያሻሽሉ ማድረግ ያስፈልጋል።መሻሻል ያሳዩ ተማሪዎችን በማድነቅና በመሸለም ማበረታታት ያስፈልጋል።

.

## 2.3 ንግድና ገበያ

**ለዚህ ርዕስ የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት........................ .........7**

ተማሪዎች ቢያንስ ሊደርሱበት የሚገባ የመማር ብቃት

ከዚህ ርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡

- የንግድና የገበያ ምንነትና ትርጉም ይገልፃሉ።
- የንግድ አጀማመር እንዴት እንደሆነ ይናገራሉ።
- ንግድ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ ያለዉ ጠቀሜታ ምን እንደሆነ ይለያሉ።
- የንግድ ዓይነቶች ምን እንደሆኑ ይገልፃሉ።
- ንግድን የሚወስኑ ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ይዘረዝራሉ።
- የምርት አቅርቦትና ፍላጎት በገበያ ላይ ያለዉን ተፅዕኖ፤ የንግድ መመጣጠንና የንግድ ውድድር ምንነት ይዘረዝራሉ።

## ቅድመ ዝግጅት

ይህንን ርዕስ ለማስተማር የሚያግዙ የመማር ዘዴዎችንና የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች እንደ ስዕል፤ ግራፍ፤ ቻርትና ሠንጠረዥ ያሉ ስለ ንግድ፤ ገበያን ግብርን ማሳየት የሚችሉትን ማዘጋጀት አስፈላጊ ነዉ። በተጨማሪም ስለገበያ ፍላጎትና አቅርቦት የተለያዩ መፅሕፍትን በማንበብ በቂ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል።

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

ይህንን ትምህርት ማስተማር ከመጀመርዎ በፊት በተማሪዎች መማሪያ መፅሐፍ ላይ ያለዉን ንግድ፤ ገበያ፤ ግብር፤ፍላጎትና አቅርቦት የሚለዉን በደንብ ማንበብና ከሌሎች ምንጮችም ተጨማሪ መረጃ በመፈለግ መረዳት ያስፈልጋል። ተማሪዎች ከሚያዉቁት እንዲነሱ ለማድረግ ስለ ንግድ፤ ገበያ፤ ግብር፤ፍላጎትና አቅርቦት በአከባቢያቸዉ ወይም በአገር ደረጃ ምን እንደሆነ በቡድን በመወያየትና የሚዉቁትን እንዲናገሩ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ። በተጨማሪም ንግድ፤ ገበያ፤ ግብር፤ፍላጎትና አቅርቦት በአገር እድገት ላይ ያለዉን ጠቀሜታና የሚወስኑ ነገሮችን እንዲለዩ ማድረግ አስፈላግ ነዉ።

## ልዩ ተሠጥዖ እና ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

ልዩ ችሎታ እና ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማበረታታት አስፈላጊ ነው። ውይይቱን ከሌሎች ተማሪዎች ቀድሞ ቶሎ መጨረስ ስለሚችሉ ርእሱን የበለጠ ሊያስገነዝባቸው የሚያስችል ጥያቄዎችን በማዘጋጀት መስጠት ያስፈልጋል ። በክፍል ውስጥ ያሉ በትምህርት አቀባበላቸው ፈጣን ያልሆኑ እና ሴት ተማሪዎችን ደግሞ ተጨማሪ ሥራን እንዲሰሩ ማድረግና ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ ነዉ። ተማሪዎች ስለገበያ አቅርቦትና ፍላጎት መካከል ያለዉን ግንኙነት በደንብ እንዲገነዘቡ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ።

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ ለማወቅ የተለያዩ ጥያቄዎችን ለምሳሌ ንግድ፤ ገበያና የመንግስት ግብር እንዲሁም ጥቅማቸዉ በአከባቢያቸዉ ምን እንደሚመስል፤ አቅርቦትና ፍላጎት በገበያ ላይ ምን ዓይነት ተፅዕኖ እንደሚያመጡ መጠየቅ። ተማሪዎች የአቅርቦትና የፍላጎት ተመጣጣኝ መሆንና አለመመጣጠንን የሚያሳይ ግራፍ በመስራት ለጓደኞቻቸዉ እንደያሳዩ በማድረግ ተከታታይነት ያለው ክትትል ማድረግ አስፈላጊ ነው፤፡ የተማሪዎችን ችሎታ በመለየት የሚያስፈልጋቸውን እገዛ ማድረግ ነው።ለምሳሌ እንደ ንግድ ፍላጎትና አቅርቦት ላይ እንዴት ተፅዕኖ ያደርሰል፤ የሚሉትን በመጠየቅ ግንዛቤያቸዉን መሻሻል ይገባል። ሁሉም ተማሪዎች የሚጠበቅባቸው የመማር ብቃት ላይ መድረስ አለባቸዉ። ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ማግኘት ያልቻሉትን የተለየ እገዛ በማድረግና በእረፍት ጊዜያቸዉ የሚሰሩትን ሥራዎችን በመስጠት ግንዛቤያቸዉን እንድያሻሽሉ ማድረግ ያስፈልጋል።መሻሻል ያሳዩ ተማሪዎችን በማድነቅና በመሸለም ማበረታታት ያስፈልጋል።

## 2.4 የመንግስት ገቢና ግብር

**ለዚህ ርዕስ የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት**……………………………………2

ተማሪዎች ቢያንስ ሊደርሱበት የሚገባ የመማር ብቃት

ከዚህ ርዕስ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች፡

- የመንግስት ግብር እና ታክስ ምንነት ይገልፃሉ።
- ስለ ኢትዮጵያ የታክስና ግብር አመጣጥ ዕድገት ይገልፃሉ።
- የመንግስት ግብር እና ታክስ ያለዉ ጠቀሜታ ምን እንደሆነ ይገልፃሉ።

## ቅደመ ዝግጅት

ይህንን ርዕስ ለማስተማር ስለገቢ ምንነት፤ የገቢ ምንጭ፤ ገቢ ለአንድ አከባቢ ወይም አገር ያለዉ ጠቀሜታ ምን እንደሆነና በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ በቂ ግንዛቤ መያዝ ይኖርቦታል፡፡ገቢ ወይም ግብር እንዴት እንደሚሰበሰብና የግብር መሰብሰቢያ ህጎችን በተመለከተ በአከባቢያችዉ የሚገኙ የገቢዎች ፅህፈት ቤት በመሄድ በቂ እዉቀትና ልምድ መዉሰድ አስፈላጊ ነዉ፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

ይህንን ትምህርት ለማስተማር ከመጀመርዎ በፊት ከተማሪዎች መፅሐፍ ስለገቢና ግብር በማንበብ በደንብ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም ከሌሎች ምንጮች ከኢንተርኔትና ከመሳሰሉት በማንበብ በቂ እዉቀት መያዝ አስፈላጊ ነዉ፡፡ ተማሪዎች ስለ ገቢና ግብር የሚያዉቁትን እንድናገሩ ለማድረግ ትምህርቱን በጥያቄና መልስ መጀመር አለባችዉ፡፡ ተማሪዎች በአከባቢያቸዉ ግብርን እንዴት እንደሚሰበሰብና የገቢ ጥቅም በቡድን በመወያየት ያለቸዉን እዉቀት እንዲለዋወጡ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ፡፡

## ልዩ ተሠጥዖ እና ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

ልዩ ችሎታ እና ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማበረታታት አስፈላጊ ነው፡፡ በውይይት ወቅት የገቢና የግብር ምንነትና ለአገር እድገት ያለዉ ጠቀሜታ ምን እንደሆነ በደንብ እርስ በርስ ልምዳቸዉን እንንዲከፋፈሉ ማድረግ ያስፈልጋል ፡፡ በክፍል ውስጥ ያሉ በትምህርት አቀባበላቸው ፈጣን ያልሆኑ እና ሴት ተማሪዎችን ደግሞ ተጨማሪ ሥራን እንዲሰሩ ማድረግና ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ፡፡ ተማሪዎች ስለገበያ አቅርቦትና ፍላጎት መካከል ያለዉን ግንኙነት በደንብ እንዲገነዘቡ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ፡፡

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ ለማወቅ ተከታታይነት ያለው ክትትል ማድረግ አስፈላጊ ነው፤፡ የተማሪዎችን ችሎታ በመለየት የሚያስፈልጋቸውን እገዛ ማድረግ ጥሩ ነው፡፡ለምሳሌ የተለያዩ ጥያቄዎችን እንደ የመንግስት ገቢና ግብር ምንድነዉ? የመንግስት

ገቢና ግብር እንዴት ተጀመረ? የሚሉትን በመጠየቅ ግንዛቤያቸዉን መሻሻል ይገባል። ሁሉም ተማሪዎች የሚጠበቅባቸው የመማር ብቃት ላይ መድረስ አለባቸዉ። ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ማግኘት ያልቻሉትን የተለየ እገዛ በማድረግና በእረፍት ጊዜያቸዉ የሚሰሩትን ሥራዎችን በመስጠት ግንዛቤያቸዉን እንድያሻሽሉ ማድረግ ያስፈልጋል።መሻሻል ያሳዩ ተማሪዎችን በማድነቅና በመሸለም ማበረታታት ያስፈልጋል።

## የምዕራፍ ሁለት ጥያቄዎች መልስ

| እዉነት ሀሰትጥ ያቄዎች | | | | አዛምድ ያቄዎች | ምርጫዎች ያቄዎች |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | እዉነት | 7 | ሀሰት | 1 ሐ | 1 ሠ |
| 2 | እዉነት | 8 | እዉነት | 2 ሀ | 2 መ |
| 3 | ሀሰት | 9 | እዉነት | 3 መ | 3 ሀ |
| 4 | እዉነት | 10 | ሀሰት | 4 ሠ | 4 ሐ |
| 5 | ሀሰት | | | 5 ረ | 5 ሐ |
| 6 | እዉነት | | | 6 ለ | 6 መ |

## IV አጭር መልስ የሚፈልጉ ጥያቄዎች መልስ

1. አንደኛ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች
2. ጥሬ ዕቃን ለሰዉ አገልግሎት በሚሰጥ መልኩ ማዘጋጀት
3. በሁለት
4. እንደኛ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ከሌሎች የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የሚለየዉ የሰለጠነ የሰዉ ኃይልና ትላልቅ ቴክኖሎጂን ስለማይፈልግ ነዉ።
5. ሦስተኛ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ሲሆን ከፍተኛ የሆነ ገቢ ማስገኘትና ለብዙ ሰዎች የሥራ ዕድል የሚፈጥር ነዉ።

6. የአደጉ ሀገሮች የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያለዉ ሁለተኛና ሦስተኛ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ሲሆኑ በማደግ ላይ ያሉ ሀገሮች ደግሞ አንደኛ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ነዉ።

7. በምርት አቅርቦት ላይ ተፅዕኖ የሚያመጡ ነገሮች የምርት መሸጫ ዋጋ፤ የአምራች ብዛት፤ የተክኖሎጂ መስፋፋት፤ የመንግስት ግብር እና ድጋፍ ናቸዉ።

8. በምርት ፍላጎት ላይ ተፅዕና የሚያመጡ ነገሮች የግል ምርጫዎች፤ የተጠቃሚዎች ብዛት፡ የምርቱ ዋጋና የግል ገቢ ናቸዉ።

9. ኢትዮጵያ ለዓለም ገበያ የምታቀርበዉ ምርቶች ለምሳሌ ቡናና ወርቅ ሲሆኑ ወደአገር ውስጥ የምታስገባው ደግሞ ነዳጅና ኤሌክትሮኒክስ ምርቶች ናቸዉ።

## ማብራሪያ የሚፈልጉ ጥያቄዎች መልስ

1. ሦስተኛ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ከሌሎች የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ልዩ የሚያደርገዉ. የሦስተኛ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የተለያዩ አገልግሎቶችን የሚያጠቃልል ሲሆን እነሱም እንደ ንግድ፤ ቱሪዝም፤ እንሹራንስ፤ ባንክ ሆቴልና የመሳሰሉት ናቸዉ። ዘህ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ምንም ዓይነት ምርት የማይመረትና የተመረተውን ምርት ማቅረብ ወይንም መጠቀም ፤ አገልግሎት መስጠት ብቻ ነው።

2. ግብር ለአገራችን ከሚሰጠዉ ጠቀሜታ ውስጥ የኢኮኖሚ እድገት ይጨምራል። ገቢን ያሳድጋል። የአገር እንቨስትመንትን ያሳድጋል።

# ምዕራፍ ሦስት

# ተፈጥሮ ሀብት ፤ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች እድገት

**ለዚህ ምዕራፍ የተሰጠው የክፍል ጊዜ ብዛት** ………………………….27

**የምዕራፉ የመማር ውጤቶች**

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፤

የተፈጥሮ ሀብት፤ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ላይ ያለዉ ጠቀሜታ ይናገራሉ፡፡

- የተፈጥሮ ሀብት ምንነትና አጠቃቀም ለአገር  እድገት ያለዉን ጠቀሜታ ይገልፃሉ፡፡
- በአከባቢያቸዉ ህብረተሰቡ በተፈጥሮ ሀብት እንዴት እንደሚጠቀሙ ይናገራሉ፡፡
- በተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ምክንያት የሚፈጠሩ ግጭቶች እንዴት እንደሚፈቱ ይናገራሉ፡፡

**ዋና ዋና ነጥቦች**

በዚህ ርዕስ ትምህርት ውስጥ ተማሪዎች እንዲያዉቁ የሚጠበቀዉ የተፈጥሮ ሀብት በማህበራዊና በኢኮኖሚያዊ እድገት ውስጥ ያለዉ ጠቀሜታ ምን እንደሆነ የተፈጥሮ ሀብት ዓይነቶችን የማራሉ፡፡

## 3.1 የተፈጥሮ ሀብት፤ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ  እድገት

ለዚህ ርዕስ ትምህርት የተሰጠው የክፍል ጊዜ ብዛት…………… ………1

ተማሪዎች ቢያንስ ሊደርሱበት የሚገባ የመማር ብቃት

ከዚህ ርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡

- በኢትዮጵያ ውስጥ በሰዉ ልጅ ተግባር በተፈጥሮ ሀብት ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን ይናገራሉ፡፡
- የተፈጥሮ ሀብት በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ያለዉ ጠቀሜታ ምን እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡
- በተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ላይ ጉዳት ሊያመጡ የሚችሉ ነገሮችን ይለያሉ፡፡

- በአከባቢያቸዉ በተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ከጊዜ ወደ ጊዜ ለምን እየተቀየረ እንደሚሄድ ይገነዘባሉ፡፡
- በአከባቢያቸዉ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶችን ይንከባከባሉ፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

የዚህን ርዕስ ትምህርት ለማስተማር ከመጀመርዎ በፊት ለዚህ ርዕስ የሚስማሙ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች እንደ ሰንጠረዥና ሥዕሎችን ማዘጋጀት እንዲሁም ከዚህ ርዕስ ጋር የሚያያዙ የተለያዩ መፅሓፍትን በማንበብ በቂ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

ይህንን ትምህርት ለማስተማር ከመጀመርዎ በፊት ተማሪዎችን ማዕከል ያደረገ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ ተማሪዎች እንደየአከባቢያቸዉ ተጨባጭ ሁኔታ በቡድን ሆነው በአከባቢያቸዉ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶችን በመመልከት ትምህርቱን ተጨባጭ ማድረግ ይቻላል፡፡ በተጨማሪም ከሌሎች መፅሐፍት ያነበቡዋቸዉን በማካተት የትምህርቱን ማጠቃሊያ መስጠት አስፈላጊ ነዉ፡፡

## ልዩ ተሠጥዖ እና ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

ልዩ ችሎታ እና ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማበረታታት አስፈላጊ ነው፡፡ በውይይት ወቅት የገቢና የግብር ምንነት እንዲሁም ለአገር እድገት ያለዉ ጠቀሜታ ምን እንደሆን በደንብ እርስ በርስ ልምዳቸዉን እንድያካፍሉ ማድረግ ያስፈልጋል ፡፡ በክፍል ውስጥ ያሉ በትምህርት አቀባበላቸው ፈጣን ያልሆኑ እና ሴት ተማሪዎችን ደግሞ ተጨማሪ ሥራን እንዲሰሩ ማድረግና ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ፡፡ ተማሪዎች ስለገበያ አቅርቦትና ፍላጎት መካከል ያለዉን ግንኙነት በደንብ እንዲገነዘቡ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ፡፡

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ ለማወቅ ተከታታይነት ያለው ክትትል ማድረግ አስፈላጊ ነው፤፡ የተማሪዎችን ችሎታ በመለየት የሚያስፈልጋቸውን እገዛ ማድረግ ነው።ለምሳሌ የተለያዩ ጥያቄዎችን ፤ የሰዉ ልጅና የተፈጥሮ ሀብት መካከል ያለዉ ግንኙነት ምን ይመስላል፤በተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀም ላይ የሚከሰቱ ግጭቶች እንዴት ይፈታሉ? የሚሉትን በመጠየቅ ግንዛቤያቸዉን መሻሻል ይገባል። ሁሉም ተማሪዎች የሚጠበቅባቸው የመማር ብቃት ላይ መድረስ አለባቸዉ። ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ማግኘት ያልቻሉትን የተለየ እገዛ በማድረግና በእረፍት ጊዜያቸዉ የሚሰሩትን ተጨማሪ ሥራዎች በመስጠት ግንዛቤያቸዉን እንድያሻሽሉ ማድረግ ያስፈልጋል።መሻሻል ያሳዩ ተማሪዎችን በማድነቅና በመሸለም ማበረታታት ጥሩ ነው።

## 3.1.1. ተከታታይነት ያለዉ እድገት ለማምጣት የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምና እንክብካቤ

ለዚህ ርዕስ የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት……………………… ………2

ተማሪዎች ቢያንስ ሊደርሱበት የሚገባ የመማር ብቃት

ከዚህ ርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡

- የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤና አጠቃቀም ምንነት ይገልፃሉ።
- በተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ምክንያት የሚፈጠሩ ግጭቶች እንዴት እንደሚፈቱ ይናገራሉ።
- በተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ላይ ከህብረተሰቡ ጋር የድርሻቸዉን ይወጣሉ።
- የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ውስጥ ያለዉ ጠቀሜታ ይገለፃሉ።

## ቅድመ ዝግጅት

ይህንን ርዕስ ለማስተማር ከመጀመርዎ በፊት ለትምህርቱ የሚያስፈልጉትን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች እንደ የኢትዮጵያን ለተፈጥሮ ሀብቶች የሚደረጉ እንክብካቤዎችን የሚያሳይ የፊዝካል ካርታና የተለያዩ ስዕሎችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል።

## የመማር ማስተማር ዘዴ

የዚህን ርዕስ ትምህርት ለማስተማር የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን መቅረብ ይቻላል፡፡ለምሳሌ ፤ገለፃ፤ ጥያቄና መልስ፤ ማሳየትና በመሳሰሉት ሊሆን ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ ለዚህ ርዕስ ይበልጥ የሚስማማዉና ተማሪዎችን የሚያነቃቃ የተለየ ዘዴን መምረጥ ይቻላል፡፡

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ ለማወቅ ተከታታይነት ያለው ክትትል ማድረግ አስፈላጊ ነው፤፡ የተማሪዎችን ችሎታ በመለየት የሚያስፈልጋቸውን እገዛ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ለምሳሌ የተለያዩ ጥያቄዎች፤ በተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤና ተከታተይነት ያለዉ እድገት መካከል ያለዉ ግንኙነት ምን ይመስላል?እና የመሳሰሉትን በመጠየቅ ግንዛቤያቸዉን መሻሻል ይገባል፡፡ ሁሉም ተማሪዎች የሚጠበቅባቸው የመማር ብቃት ላይ መድረስ አለባቸዉ፡፡ ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ማግኘት ያልቻሉትን ደግሞ የተለየ እገዛ በማድረግና በእረፍት ጊዜያቸዉ የሚሰሩትን ሥራዎች በመስጠት ግንዛቤያቸዉን እንድያሻሽሉ ማድረግ ነው፡፡

## የመልመጃ 3.1. ጥያቄዎች መልስ

1. ተፈጥሮ ሀብቶች ውስን ስለሆኑ ሁሉም የማህበረሰብ ክፍል በጥንቃቄና በቁጠባ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡
2. የተፈጥሮ ሀብቶችን ለተተኪዉ ተውልድ ለማቆየት በቁጠባ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡
3. ተተኪዉን ተውልድ የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤና አጠባበቅን ማስተማር ያስፈልጋል፡፡

## 3.1.2. በተከታታይ ተፈጥሮ ሀብትን መጠቀም ለኢኮኖሚ እድገትያለዉ ጠቀሜታ

ለዚህ ርዕስ የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት……………………… ………2

ተማሪዎች ቢያንስ ሊደርሱበት የሚገባ የመማር ብቃት

ከዚህ ርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፤

- በተፈጥሮ ሀብት በቀጣይነት መጠቀም በኢኮኖሚ ላይ ያለዉን ጠቀሜታ ይገነዘባሉ፡፡
- በአከባቢያቸዉ ያለዉን የተፈጥሮ ሀብት በመንከባከብና በጥንቃቄ ይጠቀማሉ፡፡
- የተፈጥሮ ሀብትን ያለእንክብካቤ መጠቀም የሚያመጣዉን ጉዳት ይለያሉ፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

ይህንን ርዕስ ለማስተማር ከመጀመርዎ በፊት ለትምህርቱ የሚያስፈልጉ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፤ የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሀብቶች ዓይነቶችና እንክብካቤያቸዉን የሚያሳይ የፊዝካል ካርታና የተለያዩ ስዕሎችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴ

የዚህን ርዕስ ትምህርት ከመጀመርዎ በፊት በተማሪዎች መፅሐፍ ላይ የቀረበዉን ሀሳብና ከዚህ ርዕስ ጋር ተያያዥነት ያለቸዉ ሌሎች ፅሁፎችን በማንበብ በቂ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ተማሪዎች ስለ የተፈጥሮ ሀብት ዓይነቶችና የሚደረግላቸው እንክብካቤዎች ከሚያዉቁት በመነሣት እንዲናገሩ ትምህርቱን በጥያቄ መጀመር ነው፡፡

## ተከታታይ ምዘና

የዚህን ርዕስ ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ ለማረጋገጥ ተማሪዎችን በተፈጥሮ ሀብት መመንጠር ምክንያት ሊመጡ የሚችሉ ችግሮች ምን እንደሆኑ በመጠየቅ ግንዛቤያቸዉን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነዉ፡፡ ተማሪዎች የሚጠበቅባቸው የመማር ብቃት ላይ መድረስ አለባቸዉ፡፡ ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ማግኘት ያልቻሉትን የተለየ እገዛ በማድረግና በእረፍት ጊዜያቸዉ የሚሰሩትን ሥራዎች በመስጠት ግንዛቤያቸዉን እንዲያሻሽሉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡መሻሻል ያሳዩ ተማሪዎችን በማድነቅ በራስ መተማመን እንድያዳብሩ ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡

## 3.1.3. በተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ላይ ተፅዕኖ ሊያደርሱ የሚችሉ ነገሮች

ለዚህ ርዕስ የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት……………………… ………2

ተማሪዎች ቢያንስ ሊደርሱበት የሚገባ የመማር ብቃት

ከዚህ ርዕስትምህርት በኂላ ተማሪዎች፡

- በተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ላይ ተፅዕኖ ሊያደርሱ የሚችሉ ነገሮችን ይለያሉ፡፡
- በአከባቢያቸው የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶችን የሚያሳይ ካርታ በማዘጋጀት ያሳያሉ፡፡
- የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤና በቀጣይነት የመጠቀም ፅንሰ ሀሳብ ይገልፃሉ፡፡
- በተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ላይ የሚነሱ ግጭቶችን እንዴት እንደሚፈቱ ይገነዘባሉ፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

የዚህን ርዕስ ትምህርት ማስተማር ከመጀመርዎ በፊት የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን፤ በተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ላይ ተፅዕኖ ሊያደርሱ የሚችሉ ነገሮችን የሚያሳይ ስዕል ማዘጋጀት አስፈላጊ ነዉ፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

ይህንን ርዕስ ለማስተማር ተማሪዎችን ማዕከል ያደረገ የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን በመጠቀም ማስተማር ይቻላል፡፡ መምህራን የትምህርት ቤታቸዉን ተጨባጭ ሁኔታን መሠረት በማድረግ ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት የመስክ ጉብኝት እንድያደርጉ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ትምህርቱን ይበልጥ እንድረዱ ማድረግ ያስፈልግል፡፡ በተጨማሪም ሌሎች የተለያዩ ምንጮችን በማንበብና ያገኙትን እዉቀት መሰረት በማድረግ የትምህርቱን ማጠቃለያ መስጠት አስፈላጊ ነዉ፡፡

## ልዩ ተሠጥዖ እና ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

ልዩ ችሎታ እና ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማበረታታት አስፈላጊ ነው፡፡ በውይይት ጊዜ በሌሎች ተማሪዎች ላይ ተፅዕኖ እንዳያደርሱ ክትትል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በክፍል ውስጥ ያሉ በትምህርት አቀባበላቸው ፈጣን ያልሆኑ እና ሴት ተማሪዎችን ደግሞ ተጨማሪ ሥራን እንዲሰሩ ማድረግና ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ፡፡

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች ትምህርቱን ምን ያህል እንደተገነዘቡ ለማረጋገጥ የማያቋርጥ ክትትል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ክትትሉ በሚደረግበት ጊዜ በክፍል ውስጥ የተለያዩ ዓይነት ተማሪዎች መኖራቸዉን መረሳት የለበትም፡፡ ስለዚህም የሚዘገጀዉ ጥያቄ ሁሉም ተማሪዎችን ማዕከል ያደረገ መሆን አለበት፡፡ ተማሪዎችን ከለየን በኂላ እገዛ ለሚያስፈልጋቸዉ ተከታታይነት ያለዉ እገዛ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## 3.1.4. የተፈጥሮ ሀብት ከጊዜ ወደ ጊዜ ያለዉ ጠቀሜታ

ለዚህ ርዕስ የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት............................... .........1

ተማሪዎች ቢያንስ ሊደርሱበት የሚገባ የመማር ብቃት

ከዚህ ርዕስትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡

- የተፈጥሮ ሀብት ከጊዜ ወደ ጊዜ ያለዉን ጠቀሜታ ይለያሉ፡፡
- የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ህጎችና ደንቦችን ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡
- ለግልና ለአገር ሀብቶች ጥበቃ ያደርጋሉ፡፡

### ቅድመ ዝግጅት

የዚህን ርዕስ ትምህርት ማስተማር ከመጀመርዎ በፊት ይህንን ርዕስ ለማስተማር የሚያግዙ የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን እንደ ስዕልና ፖስተሮች ማዘጋጀት አስፈላጊ ነዉ፡፡

### የመማር ማስተማር ዘዴዎች

ይህንን ርዕስ ለማስተማር ተማሪዎችን ማዕከል ያደረገ የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን መጠቀም ይቻላል፡፡ መምህራን የትምህርት ቤታቸዉን ተጨባጭ ሁኔታን መሠረት በማድረግ ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት የመስክ ጉብኝት እንድያደርጉ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ትምህርቱን ይበልጥ እንዲረዱ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም ሌሎች የተለያዩ ምንጮችን በማንበብና ያገኙትን እዉቀት መሰረት በማድረግ የትምህርቱን ማጠቃለያ መስጠት አስፈላጊ ነዉ፡፡

### ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች ትምህርቱን ምን ያህል እንደተገነዘቡ ለማረጋገጥ የማያቋርጥ ክትትል ማድረግ ነው፡፡ ክትትሉ በሚደረግበት ጊዜ በክፍል ውስጥ የተለያዩ ዓይነት ተማሪዎች መኖራቸዉን መረሳት የለበትም፡፡ ስለዚህም የሚዘጋጁ ጥያቄዎች ሁሉን ተማሪዎች ማዕከል ያደረገ መሆን አለበት፡፡ ተማሪዎችን ከለየን በኋላ እገዛ ለሚያስፈልጋቸዉ ተከታታይነት ያለዉ እገዛ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## 3.2. በተፈጥሮ ሀብት ያለእንክብካቤ መጠቀም የሚመጡ ጉዳቶች

ለዚህ ርዕስ የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት……………………… ………2

ተማሪዎች ቢያንስ ሊደርሱበት የሚገባ የመማር ብቃት

ከዚህ ርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡

- የተፈጥሮ ሀብት መመንጠር ምክንያትን ይገልፃሉ፡፡
- በተፈጥሮ ሀብት ያለእንክብካቤ መጠቀም የሚመጡ ጉዳቶችን ይናገራሉ፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

የዚህን ርዕስ ትምህርት ማስተማር ከመጀመርዎ በፊት ይህንን ርዕስ ለማስተማር የሚያግዙ የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፤ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃን የሚያሳዩ ስዕል በማዘጋጀት ወይም ቪዲዮ በመጠቀም ማስተማር ይቻላል፡፡ሌሎች የተለያዩ መፅሐፎችን በማንበብ በቂ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

ይህንን ርዕስ ለማስተማር ተማሪዎችን ማዕከል ያደረገ የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን እንደ ጠያቄና መልስ፤ የቡድን ውይይት በመጠቀም ማስተማር ይቻላል፡፡ ተማሪዎች ያለጥንቃቄ በተፈጥሮ ሀብት መጠቀም የሚያመጡትን ችግሮችና ለተፈጥሮ ሀብት የሚደረጉ ጥንቃቄዎቸ ምን ምን እንደሆኑ ከሚያዉቁት በመነሳት እንዲናገሩ ለማድረግ ጥያቄዎችን በማዘጋጀትና መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም ሌሎች የተለያዩ ምንጮችን በማንበብና ያገኙትን እዉቀት መሰረት በማድረግ የትምህርቱን ማጠቃለያ መስጠት አስፈላጊ ነዉ፡፡

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ ለማወቅ ተከታታይነት ያለው ክትትል ማድረግ አስፈላጊ ነው፤፡ የተማሪዎችን ችሎታ በመለየት የሚያስፈልጋቸውን እገዛ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ለምሳሌ የተለያዩ ጥያቄዎች፤ የተፈጥሮ ሀብት ምንድናቸው? የተፈጥሮ ሀብት ጥቅሞች ምን ምን ናቸው? የሚሉትን በመጠየቅ ግንዛቤያቸዉን መሻሻል ይገባል፡፡ ሁሉም ተማሪዎች የሚጠበቅባቸዉን የመማር ብቃት ላይ መድረስ አለባቸዉ፡፡ ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ማግኘት ያልቻሉትን የተለየ እገዛ በማድረግና በእረፍት ጊዜያቸዉ የሚሰሩትን

ሥራዎችን በመስጠት ግንዛቤያቸዉን እንድያሻሽሉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡መሻሻል ያሳዩ ተማሪዎችን በማድነቅና በመሸለም ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡

**የመልመጃ 3.1.3. ጥያቄዎች መልስ**

1. የተፈጥሮ ሀብቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ የተለያዩ ጥቅሞች አላቸዉ፡፡ ምክንያቱም የተፈጥሮ ሀብቶች የአንድን አገር ደንብና ህግን መስረት በማድረግ በአገር እድገት ላይ ከፍተኛ ሚና አላቸዉ፡፡

2. የህዝብና የተፈጥሮ ሀብቶች ግንኙነት መጣጣም አለበት፡፡ ምክንያቱም የተፈጥሮ ሀብትና የህዝብ ብዛት ከልተጣጣመ በተፈጥሮ ሀብት ላይ ከፍተኛ የሆነ መመንጠር ይደርሳል፡፡

3. የህዝብና የተፈጥሮ ሀብቶች ግንኙነት በሦስት ይከፈላል፡፡ እነሱም ከአቅም በላይ የሆነ የህዝብ ሥርጭት፤ተመጣጣኝ የሆነ የህዝብ ሥርጭትና ከአቅም በታች የሆነ የህዝብ ስርጭት ናቸዉ፡፡

## 3.2.1.የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤና አጠቃቀም

ለዚህ ርዕስ የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት………………………… ………1

ተማሪዎች ቢያንስ ሊደርሱበት የሚገባ የመማር ብቃት

ከዚህ ርዕስ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች፡

- የተፈጥሮ ሀብቶች የሚባክኑበትን መንገዶች ይዘረዝራሉ፡፡
- የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ሣይቋረጥ እንዴት መንከባከብ እንደሚቻል ይዘረዝራሉ፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

የዚህን ርዕስ ትምህርት ማስተማር ከመጀመርዎ በፊት ይህንን ርዕስ ለማስተማር የሚያግዙ የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃን የሚያሳይ ስዕል በማዘጋጀት ማስተማር ይቻላል፡፡ሌሎች የተለያዩ መፅሐፎችን በማንበብ በቂ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

ይህንን ርዕስ ለማስተማር ተማሪዎችን ማዕከል ያደረገ የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን

እንደ ጠያቂና መልስ፤ የቡድን ውይይትና የመስክ ጉብኝት በመጠቀም ማስተማር ይቻላል። ተማሪዎች ለተፈጥሮ ሀብት የሚደረጉት ጥንቃቄዎች ምን ምን እነደሆኑ ከሚያዉቁት ተነስተዉ እንዲናገሩ ለማድረግ ጥያቄዎችን አዘጋጅቶ መጠየቅ ያስፈልጋል። በተጨማሪም ሌሎች የተለያዩ ምንጮችን በማንበብና ያገኙትን እዉቀት መሰረት በማድረግ የትምህርቱን ማጠቃለያ መስጠት አስፈላጊ ነዉ።

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ ለማወቅ ተከታታይነት ያለው ክትትል ማድረግ አስፈላጊ ነው፤፡ የተማሪዎችን ችሎታ በመለየት የሚያስፈልጋቸውን እገዛ ማድረግ አስፈላጊ ነው።ለምሳሌ የተፈጥሮ ሀብትን እንዴት መጠበቅ ይቻላል? የተፈጥሮ ሃብቶች የሚባክኑበት መንገዶች ምንድናቸው ? የሚሉትን በመጠየቅ ግንዛቤያቸዉን መሻሻል ይገባል። ሁሉም ተማሪዎች የሚጠበቅባቸው የመማር ብቃት ላይ መድረስ አለባቸዉ። ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ማግኘት ያልቻሉትን የተለየ እገዛ በማድረግና በእረፍት ጊዜያቸዉ የሚሰሩትን ሥራዎችን በመስጠት ግንዛቤያቸዉን እንድያሻሽሉ ማድረግ ያስፈልጋል።

### የመልመጃ 3.1.4. ጥያቄዎች መልስ

1. የተፈጥሮ ሀብት ለአንድ አገር ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት ውስጥ ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ አለዉ። በተለይም የተፈጥሮ ሚዛን ለመጠበቅና ለእንዱስትሪ ጥሬ ዕቃነት ያገለግላል።
2. የተፈጥሮ ሀብት ውስን በመሆኑ ለቀጣይ ትውልድ ለማስተላለፍ በጥንቃቄና በቁጠባ መጠቀም ያስፈልጋል።
3. ያለ እንክብካቤ በተፈጥሮ ሀብት የምንጠቀም ከሆነ አንዳንድ የተፈጥሮ ሀብቶች ልያልቁ ስለሚችሉና ራሳቸዉን የማይተኩ ስለሆነ እንደገና ልናገኛቸዉ አንችልም።

## የምዕራፍ 3 የመልመጃ ጥያቄዎች መልስ

**I.** እዉነት ወይም ሀሰት ጥያቄዎች

1. ሀሰት 2. ሀሰት 3. እዉነት 4. ሀሰት

**II.** አዘምድ ጥያቄዎች

1. ሐ 2. ሀ 3. ሀ 4. ሐ 5. ለ

## III. አጭር መልስ ጥያቄዎች

1. የተፈጥሮ ሀብትን ሳያባክኑ ለቀጣይ ትውልድ እንዲተላለፍ በቁጠባና በጥንቃቄ መጠቀም ማለት ነዉ፡፡
2. በቀጣይነት በተፈጥሮ ሀብት መጠቀም በአንድ አገር ኢኮኖሚ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ አለዉ፡፡
3. በተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ላይ ተፅዕኖ የሚያመጡ ነገሮች ብዙ ሲሆኑ፤ ከእነዚህም ውስጥ የማህበረሰቡ የአጠቃቀም ባህል፤ ሀገሪቱ የእድገት ደረጃና የተክኖሎጂ ግኝት ናቸዉ፡፡
4. አፈርን መንከባከብና በቀጣይነት መጠቀም ወሳኝ ነዉ፡፡ ምክንያቱም በማህበረሰብ ውስጥ የምርት መጨመር ስለሚያስገኝ ነዉ፡፡
5. ውሃ በኢኮኖሚ ውስጥ ያለዉ ጠቀሜታ ለንፅህና፤ ለመጓጓዣነት፤ የኤለክትሪክ ሃይል ለማመንጨት፤ ለእርሻና ለመሳሰሉት ይዉላል፡፡
6. የደኖች መጥፋት የተለያዩ ችግሮችን ያስከትላል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ የውሃ ምንጮች መድረቅ፤ የእንስሳት መሰደድ፤ ድርቅና የመሳሰሉት ናቸው፡፡
7. በህዝብ ቁጥር መጨመርና በተፈጥሮ ሀብት መመንጠር መካከል ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት አለ፡፡ ምክንያቱም የህዝብ ቁጥር መጨመር የምግብ እህልና የሌሎች መሰረታዊ ነገሮች ፍላጎት ይጨምራል፡፡ ይህ ደግሞ የደኖች መጨፍጨፍ፤ የሌሎች የተፈጥሮ ሀብቶች መጥፋትና የመሳሰሉትን ያመጣል፡፡ ይህ ደግሞ የአየር ንብረት መቀየር ያስከትላል፡፡

# ምዕራፍ 4 ዘመናዊው የአለም ታሪክና አጀማመሩ

**የክፍል ጊዜ ብዛት......... 24**

**ከዚህ ምዕራፍ የሚጠበቁ ውጤቶች፡**

***ይህ ምዕራፍ ከተጠናቀቀ በኋላ ተማሪዎች፤***

- ጂኦግራፊያዊ የባህርና ውቅያኖስ ላይ አሰሳ ሂደት ትገልጻለህ/ሽ
- የአዳዲስ ጽንሰ ሃሰቦች መፍለቅ (Renaissance)፣ የተሓድሶ እንቅስቃሴ (Reformation) እና የተሓድሶ እንቅስቃሴ ተቃውሞ (Counter - Reformation) በማነጻጸር ታገናዝባለህ/ሽ
- ስለ ኢንዱስትሪ አብዩት ጽንሰ ሀሳብ በስፋት ትገልጻለህ/ሽ
- የሁለቱን የአለም ጦርነቶች ምክንያትና ባህሪያትታገናዝባለህ/ሽ
- ቀዝቃዛው የአለም ጦርነት ባህሪያት ትገልጻለህ/ሽ፡፡

## መግቢያ

በሰባተኛ ክፍል ትምህርት ውስጥ ስለ ቀደምት አውሮፓ፣ ኤሺያ እና የአፍሪካ ስልጣኔዎች ተምረዋል፡፡ በተጨማሪም ስለ ክርስትና ሀይማኖትና የእስልምና ሀይማኖት አመጣጥ እና መስፋፋትን ተረድተዋል። እንዲሁም ስለ ባዛንታየን ኢምፓየር ባህሪያት ለይተዋል።

በ8ኛ ክፍል ትምህርት ውስጥ ደግሞ በዘመናዊው የአለም ታሪክ ውስጥ ጂኦግራፊያዊ የባህርና ውቅያኖስ ላይ አሰሳ ይማራሉ፡፡ እንዲሁም ስለ የአዳዲስ ጽንሰ ሃሰቦች መፍለቅ (Renaissance)፣ የተሓድሶ እንቅስቃሴ እና የተሓድሶ እንቅስቃሴ ተቃውሞ (Counter-Reformation)ይማራሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ስለ ኢንዱስትሪው አብዩት ውጤቶች፣ ሁለቱ የአለም ጦርነቶች እና ቀዝቃዛውን የአለም ጦርነት ይማራሉ።

# 4.1. ጂኦግራፊያዊ የባህርና ውቅያኖስ ላይ አሰሳ

**የክፍለ ጊዜ ብዛት………3**

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባቸው የትምህርት ብቃት፤**

- የባህርና ውቅያኖስ ላይ አሳሾች ሲጠቀሙበት የነበረውን የአሰሳ መስመሮችን በካርታ ላይ ያሳያሉ
- በጂኦግራፊያዊ የባህርና ውቅያኖስ ላይ አሰሳ ሲሳተፉ የነበሩትን ሀገራትና ሰዎችን ይለያሉ፡፡

## ዋና ዋና ነጥቦች

መምህር/ት! የሰው ልጅ ከመጀመሪያው ጀምሮ እንዴት ከሀገር ወደ ሀገር ሲጓዝ እንደ ነበርና በጥንት የአለም ስልጣኔ ጊዜም በውሃ ላይ ሲጓዝ እንደ ነበር መገንዘብ አሰረላጊ ነው ። በዚህ መሰረት የአሰሳ ዘመን የጀመረው በ15ኛው ክፍለ ዘመን አከባቢ ነው ።

ይህ አሰሳ የተጀመረበት ምክንያቶችም ብዙ ናቸው ። ለንግድ ስራ በማሰብ አውሮፓውያን እስከ መካከለኛው ምስራቅ፣ ደቡብ ምዕራብና መካከለኛው ኤሽያ በአድካሚ ሁኔታ በመሬት ላይ ሲጓዙ ነበር።ይሁን እንጂ ከ11ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በኦትማን ቱርክና በአውሮፓውያን መካከል በተፈጠረው ግጭት የተነሳ ወደ መካከለኛው ኤሽያ የሚወስደው መንገድ ሊዘጋ ችሏል። ይህ አለመግባባት ከ1090 እስከ 1270ዎቹ ኢ.አ.አ የመስቀል ጦርነት ሊያስከትል ችሏል፡፡

ወደ ምስራቅ የሚወስደው መንገድ በመዘጋቱ የተነሳ አው ሮፓው ያኖች የንግድ፣ የፖለቲካና የጆግራፋዊ ፍላጎታቸው ን ለሚሟላት ሌላ አማራጭ መፈለግ ግድ ነበር። በዚሁም መሰረት ወደ ምስራቅ የሚወስደው ን መንገድ በመተው አቅጣቻቸው ን በመቀየር ወደ ምዕራብ አሰሳ ጀመሩ።
በዚህ ሁኔታ አውሮፓኖች በንፋስ የሚገፉ ጀልባዎችን በመጠቀምእስከ ሰሜን አፍሪካ ተጉዘዋል። ቀስ በቀስም ወደ ምዕራብ አፍሪካ በመጓዝ በ1488 ባርቶሎሚየው ዴየዝ የደቡብ

አፍሪካ ጫፍ ሲደርስ፣ በ1498 ቫስኮ ዳጋማ ደግሞ ህንድ ሀገር ደርሷል። በ1492 ክርስቶፈር ኮሎምቦስ አዲስ አህጉር (አሜሪካን) ሲያገኝ፣በ1519-1522 ደግሞ ፈርዲናንድ ማጅላን አለምን ለመጀመሪያ ጊዜ ዞሯል። ከዚህም ውጭ የተለያዩ አሳሾች በባህርና በውቅያኖሶች ላይ ከቦታ ቦታ በመዟዟር አዳዲስ አከባቢዎችንና የአየር ሁኔታዎች ሲያስሱ ቆይተዋል። በዚህም የተነሳ ለሀገራቸውና ለአለም ብዙ ጥቅሞችን አስገኝተዋል።

## ቅድመ ዝግጅት

መምህር/ት! ተማሪዎችን ይህንን ንዑስ ርዕስ ማስተማር ከመጀመርህ/ሽ በፊት ሰፊ የሆነ ዝግጅት ይጠበቅብሀል/ሻል። በዚህ መሰረትም ጠለቅ ያለ እውቀት እንዲኖርህ/ሽ ከጥንታዊው የአለም ስልጣኔ ዘመን ጀምሮ እስከ የአሰሳው ዘመን ያሉትን ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች ተገንዘብ/ቢ። በውቅያኖሶች ላይ አሰሳ መጀመር ምክንያቶች መለየት ይጠበቅብሀል/ሻል። ለዚህ ስራ አስተዋፅኦ ያደረጉትን ሀገራትና ነገሥታት አገናዝብ/ቢ። በመጨረሻም የአሰሳ አቅጣጫዎችን(መንገዶችን) ሊያሳይ የሚችል የአለም ካርታ አዘጋጅ/ጂ።ከዚህ በኋላ ጥራት ያለውና የተማሪውንና የመምህሩን/ሯን ተግባር የለየ የትምህርት ዕቅድ አዘጋጅ/ጂ።. ይህንን የትምህርት ይዜት ለማስተማርም ሶስት ክፍለ ጊዜ ተሰቷል።በመሆኑም የትምህርት ይዘቱ በተሰጠው ክፍለ ጊዜ ሊጠናቀቅ በሚችል መልኩ በተቀመጠው ዓላማ መሰረት ቅደም ተከተሉን ጠብቀህ/ሽ ማስገንዘብ አስፈላጊ ነው ።

## የመማር ማስተማር ዘዴ

እንደሚታወቀው ተማሪዎችን ለማስተማር አንድ ዘዴ ብቻ መጠቀም በቂ አይደለም።ስለዚህም ይህንን ንዑስ ርዕስ ለማስተማር የተሻለው ዘዴ የቱ ነው? በማለት ልዩ የሆነ የመማር ማስተማሩ ዘዴ ለመነሻ ያህል እንደ ምልከታ፣ ድራማ፣ ክርክር፣ መዘገብና ማወዳደር ዘዴዎች መጠቀም ይችላሉ። የአለም ፊዚካል ካርታን በመጠቀም ተማሪዎች አሳሾች ሲጠቀሙበት የነበረውን መንግድና የአሰሳ ሁኔታ በሚያሳይ ሁኔታ ማስገንዘብ አስፈላጊ ነው ። የመለማመጃ ጥያቄዎችን በስፋት እንዲመካከሩበት፣ እንዲከራከሩበትና መልሳቸውንም በማወዳደር እንዲወያዩበት ማድረግ ተገቢ ነው። አሳታፊ የሆነና ሁሉን ያማከለ የማስተማር ዘዴ መጠቀምም በጣም አስፈላጊ ነው ።.

## ተማሪዎች የፈጠራችሎታቸውን እንዲያጎለብቱ ማድረግ

ልዩ ተሰጥዖና ከፍተኛ ግንዛቤ ያላቸውን ተማሪዎች በመደገፍ የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ማበረታታት አስፈላጊ ነው ።ለምሳሌ የጀልባ ሥዕል በመሳል፣ ካርታ ማንሳትና ሥዕል የማንሳትን መለማመድ የሚፈልጉ ተማሪዎች ካሉ ማበረታታት አስፈላጊ ነው። በቡድናቸው ውስጥ የተሰጣቸውን ስራ ቀድመው የጨረሱ ተማሪዎች በተጨማሪ ሊሰሩ የሚችሉትን ጥያቄ መስጠት ተገቢ ነው ።እነዚህም ጥያቄዎች እየተማሩት ካለው ርዕስ ውስጥ ሳይወጣ በተቀራርቢ ይዜት በማዘጋጀት ሊሰጣቸው ይገባል። ነገር ግን ልዩ ተሰጥዖ ያላቸውን ተማሪዎች በምትረዱበት ጊዜ በክፍሉ ውስጥ ካሉት የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችም የተሻለ አማራጭ ሊዘጋጅላቸው ይገባል። በዚህ መሰረትም በክፍሉ ውስጥ ያሉትን ተማሪዎች ሁሉ ያማከለ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ መጠቀም ተገቢ ነው።

### ተከታታይ ምዘና

እንደ መማር ማስተማሩ ዘዴ የተከታታይ ምዘናና ግምገማ ዘዴዎችም ብዙ ናቸው ። ስለዚህ በቡድን ምክክር ጊዜ ያላቸውን ተሳትፎ በማየት፣ አሳቦች ሲያቋርጡበት የነበረውን መስመሮች እንዲያሳዩ በማድረግ መመዘን ይቻላል። እንዲሁም ካርታ ሰርተው እንዲያቀርቡ በማድረግ፣ አሰሳውን ሲያደርጉ የነበሩትን ሀገራትና የአሰሳ መስመሮችን እንዲያሳዩ በማድረግ መመዘን አስፈላጊ ነው ፣ ከዚህም ውጭ ተከታታይ የምዘና ዘዴን በመጠቀም በዚህ ንዑስ ርዕስ መጨረሻ ላይ የተሰጠውን መልመጃ ሰርተው እንዲያሳዩ ማድረግ፡፡እንዲሁም ተማሪዎቹ የትምህርት ዓላማ መረዳታቸውን ማረጋገጥና ማስተካከያ መስጠትይገባል።

# 4.2 የአዳዲስ ጽንሰ ሃሰቦች መፍለቅ (Renaissance) ፣ የተሓድሶ እንቅስቃሴ (Reformation) እና የተሓድሶ እንቅስቃሴ ተቃውሞ (Counter-Reformation)

## 4.2.1. የአዳዲስ ጽንሰ ሃሰቦች መፍለቅ (Renaissance)

**የክፍለ ጊዜው ብዛት—9**

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባቸው የትምህርት ብቃት፤**

- የአዳዲስ ጽንሰ ሃሰቦች መፍለቅ ፣ የተሓድሶ እንቅስቃሴ እና የተሓድሶ እንቅስቃሴ ተቃውሞ ያላቸውን ጥቅም ይለያሉ፡
- በቀደምት የአለም ስልጣኔ ዘመን የተገኙት አዳዲስ ጽንሰ ሀሳቦች
- የአዳዲስ ጽንሰ ሃሰቦች መፍለቅ፣ ተሓድሶና የተሓድሶ እንቅስቃሴን ይገነዘባሉ።

### ዋና ዋና ነጥቦች

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ሶስት ዋና ዋና ነጥቦች ተካተዋል። እነሱም የአዳዲስ ጽንሰ ሃሰቦች መፍለቅ፣ ተሓድሶና የተሓድሶ እንቅስቃሴን ናቸው። በዚህ ሁኔትም ለሶስቱም ይዘቶች ሀሳቦች ጠቅለል ተደርገው በአንድ ላይ ቀለልባለ መንገድ ቀርበዋል። በጥንት ዘመን ስልጣኔ ጊዜ የሰው ልጅ እንደ ዴሞክራሲ፣ ሪፓብሊክ፣ ህግ፣ አስተዳደርና የመሳሰሉ ሀሳቦችን በመፍጠር ሲያስፋፉ ነበር።

ቀስ በቀስም ከ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ እስከ 17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በጥንት ዘመን የነበሩና ደግሞ የተረሱትን የተለያዩ ሀሳቦችና ሙያ ዎችን እንደ አዲስ መጠናት ተጀመሩ። በተለይም የጥንት ግሪኮ-ሮማ ስልጣኔ እንደ አዲስ በጥንቃቄ ተጠንተዋል። በአጠቃላይ ይህ እንቅስቃሴ የተለያዩ ሙያዎች፣ሳይንሳዊ ሐሳቦችና ፈጠራዎች አብዮት የተካሄደበት ዘመን ነው ።

አዲሱ ፅንሰ ሀሳብ እንቅስቃሴ (Renaissance) የአለምን ማህበረሰብ በተለይም የአውሮፓን ማህበረሰብ የነበራቸውን ፖለቲካ፣ ማህበራዊ ጉዳዮች፣ ሀይማኖት እና ባህልን በማነቃቃት ግንዛቤያቸውን እንዲያሰፉ አድርጓል። ይህም የተስፋፋው ግንዛቤ በሀይማኖት በኩል

ማህበረሰቡን ጥልቅ እንቅስቃሴ ውስጥ አስግብቷቸዋል። በዚህ መሰረትም ከ14ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በጣም በመጠናከር ከ15ኛው ክፍለ ዘመን እስከ 16ኛው ክፍለ ዘመን ይበልጥ በመጎልበት በካቶሊክ ሀይማኖት ላይ ጥያቄ አስነስቷል።

በዚህም መሰረት በ1517 ዓ.ም ማርቲን ሉተር በግልፅ የክርስትና ሀይማኖት ቅርንጫፍ የሆነውን የሉተራን ፕሮቴስታንት እምነት በመባል የሚታወቀውን ሀይማኖት መስርቷል። መፅሀፍ ቅስንም ወደ ጀርመን ቋንቋ በመቶርጎም ትልቅ የሚባል እንቅስቃሴ አድርጓል።እንዲሁም ጆን ካልቪን 'ካልቪኒስት' የተባለውን ቤተክርስቲያን በመመስረት ካልቪኒዝም በመባል የሚታወቀውን የሀይማኖት አስተምህሮ አስፋፍቷል።በአጠቃላይ እነዚህ አዳዲስ የተመሰረቱት የክርስትና ሀይማኖት ቅርንጫፎች በወል ስማቸው የፕሮቴስታንት ክርስቲያኖች (Protestant Christian Religion) በመባል ይታወቃሉ።

የሀይማኖት ተሓድሶ ቡድን እንቅስቃሴ በካቶሊክ ሀይማኖት ላይ የተለያየ እርምጃ መውሰድ ጀመሩ።በተቃራኒው ደግሞ ይህንን ለውጥ የማይፈልጉ የካቶሊክ ቡድኖች የተሓድሶ ተቃውሞ እንቅስቃሴ(Counter- Reformation) መመስረት ጀመሩ። ይህ እንቅስቃሴም የካቶሊኮች እንቅስቃሴ ሲሆን ሁለት ዋና ዋና እንቅስቃሴዎችን ያቀፈ ነው። እነሱም ውስጥን የማጥራት እንቅስቃሴና የተሓድሶ ቡድኖችን የማዳከምና የማጥፋት እንቅስቃሴዎች ላይ ያተኮረ ነው። በዚህ መሰረት በ1534 የእየሱስ ቤተሰቦች በመባል የሚታወቀውን ድርጅት በእስፔን ውስጥ በኢግናተስ ሎዮላ በመመስርት እንቅስቃሴውን ጀምሯል።

የእየሱሳዊያን መመስረት ዋናው አላማ በአለም ሀገራት ላይ በመዞር የካቶሊክ ሀይማኖት ጥንካሬን ማስተማርና የተሓድሶ ቡድኖችን ማዳከምና ማጥፋት ነው።እነዚህ እየሱሳዊያን የሚታወቁበት ሌላው ስማቸው የካቶሊክ ሚሽነሮች (ሚሲዮኖች) የሚል ነው ።እነዚህ ቡድኖች ከ16ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ እንደ ኤሽያ፣ አውሮፓ፣ አሜሪካና አፍሪካ አህጉራት ውስጥ ተሰራጭተው ያስተማሩ ናቸው ።

ከነዚህም ውስጥ አንዱ ቅርንጫፍ በ1557-1625 ዓመታት አከባቢ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ንጉሥ ሱስንዮስ የካቶሊክ እምነትን እንዲቀበል አድርገው ነበር። በዚህም

የተነሳ ጎንደር ውስጥ ትልቅ የእርስ በርስ ግጭት ተነስቶ ነበር። ይህንን መሰረት በማድረግ ንጉሥ ፋሲሊደስ የውጭ ሀገራትን ዜጎች ሁሉ (የአው ሮፓ ሚስዮኖችን) ከኢትዮጵያ በማባረር በርን የመዝጋት ፖሊሲ (Close Door Policy) አውጇል። የዚህን ፖሊሲ ጥቅምና ጉዳት መገንዘብ ከዋና ዋና ነጥቦች ውስጥ አንዱ ነው ።

## ቅድምመ ዝግጅት

በቂ የሆኑ እውቀት ለማግኘት የተለያዩ የዋቢ መጽሐፍትን ማንበብ አስፈላጊ ነው።በተለየም ከ14ኛው ክፍለ ዘመን እስከ 17ኛው ክፍለ ዘመን በአውሮፓ ውስጥ የአዲሱ ፅንሰ ሀሳብ መፍለቅ (Renaissance) በተመለከተ በደንብ መገንዘብ አስፈላጊ ነው ።

በተጨማሪም ስለ ካቶሊክ እምነት አካሄድና እንቅስቃሴ ከተሓድሶ እንቅስቃሴ ቡድኖች ጋር ያላቸውን አለመግባባትና የወሰዱትን እርምጃዎች ማገናዘብ ያስፈልጋል። ከተቻለም የእነዚህን እንቅስቃሴዎች አከባቢ የሚያሳይ ካርታ፣ ስዕላስዕሎችና ፖስተሮችን አደራጅቶ መያዝ ያስፈልጋል። በመጨረም የዕለቱን የትምህርት ዕቅድ ጥራት ባለው ሁኔታ መዘጋጀት አለበት። ይህ ዕቅድም ከተሰጠው ክፍለ ጊዜ ጋር ሊሄድ የሚችል የትምህርት ይዜት ብቻ እንዲያቅፍ ሊደረግ ይገባል። እንዲሁም ተማሪዎች ይህን ይዜት ከተማሩ በኋላ ሊጎናፀፉት የሚገባቸውን ብቃት ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው። ከዚህም ውጭ የተማሪውንና የመምህሩን/ሯን ተግባር ግልፅ በሆነ አገላለፅ በዕቅዱ ውስጥ ሊካተት ይገባል።

እነዚህን ንዑሳን ርዕሶች ለማስተማር የተስጡጥ ክፍለ ጊዜዎችም ዘጠኝ ናቸው።በዚህም መሰረት የአዲሱን ጽንሰ ሀሳብ መፍለቅ ዘመን ለማስተማር ሶስት ክፍለ ጊዜዎች፣ የተሓድሶን እንቅስቃሴም በሶስት ክፍለ ጊዜዎችና የተሓድሶ ተቃውሞ ደግሞ ሶስት ክፍለጊዜዎች ተሰጥተዋል። እነዚህ ርዕሶች ከተሰጠው ሰዓት ጋር በማመጣጠን መጠቀም አስፋላጊ ነው።

## የመማር ማስተማር ዘዴ

እነዚህ ሶስቱ ንዑስ ርዕሶች (የአዲሱ ፅንሰ ሀሳብ፣ ተሓድሶና የተሓድሶ ተቃውሞ) ማስተማር ሊከብድ ይችላል። ምክንያቱም ስለ አመለካከትና ሀይማኖት ተማሪዎችን አሳምኖ ማስተማር የመምህሩን/ሯን ብቃት የሚጠይቅ ነው ። በተለይም (የአዲሱ ፅንሰ ሀሳብ

ዘመንና የተሓድሶ ተቃውሞ ከሀይማኖት ጋር የሚያያዙ ጉዳዮች ስለሆኑ መምህሩ/ሯ በከፍተኛ ጥንቃቄ ማስተማር አለብህ/ሽ።

እንዲሁም በጣም ተመራጭ የሆኑ የመማር ማስተማር ዘዴን መምረት ይገባሀል/ሻል። በተለይም ተማርዎች በክፍላቸው ውስጥ በፒራሚድ ዘዴ በመጠቀም የአዲሱ ፅንሰ ሀሳብ ዘመን አጀማመር ጋር የሚያያዙ ጉዳዮች ላይ እንዲመካከሩ አቅጣጫ ማሳየት አስፈላጊ ነው ። በተጨማሪም የክፍሉን ተማሪዎች በሁለት ቦታ በመክፈል የአዲሱ ዘመን ፅንሰ ሀሳብ መጀመርና የተሃድሶ እንቅስቃሴ ለአለም ማህበረሰብ ያበረከተውን አስተዋፆ ላይ ክርክር እንዲያካሂዱ ማድረግ ወሳኝ ነው ።

እንደ ድራማ ያሉትን በመጠቀም የመካከለኛው ዘመን የአለም ሁኔታ እንዲገልፁ ማድረግ ተገቢ ነው ።የፕሮጀክት ስራ በመስጠት በመካከለኛው ዘመን ውስጥ አዳዲስ ፅንሰ ሀሳቦች፡ሥዕል የመሳል ሙያ፣ቀለም መቀባት፣ግጥም መፃፍ እና የመሳሉትን በማስመሰል እንዲሰሩ ማድረግ አስፈላጊ ነው ።

## ተማሪዎች የፈጠራችሎታቸውን እንዲያጎለብቱ ማድረግ

ልዩ ተሰጥዖ ያላቸውን ተማሪዎች በመደገፍ የማገናዘብና የመገምገም ችሎታ እንዲያዳብሩ ማበረታታት አስፈላጊ ነው ። በዚህ መሰረትም የተለያዩ ቅርፃ ቅርፆን የመስራት ፍላጎት እና ችሎታ ያላቸውን ማበረታታት፡፡እንዲሁም ካርታን በማንሳትና ግጥም በመግጠም ለክፍሉ የሚመጥን አዲስ አስተሳሰብ የሚያመነጩት ተማሪዎችን ማበረታታት አስፈላጊ ነው ።

በቡድናቸው ውስጥ ለምክክር የተሰጣቸውን ቀድመው የጨረሱትን ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ይበልት ሊያስገነዝባቸው የሚችሉትን ጥያቄዎች ተጨማሪ መስጠት ያስፈልጋል። በክፍሉ ውስጥ ያሉትን ልዩ ተሰጥዖ ያላቸውን ተማሪዎች ደግሞ የተለየ አማራጭና ዘዴ በመጠም በክፍሉ ውስጥ ያሉትን ተማሪዎች ችሎታ ማቀራረብ አስፈላጊ ይሆናል።

## ተከታታይ ምዘና

የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠቀም በካርታ ላይ ሀገራትንና አዲሱን ፅንሰ ሃሳብ ሲያፈልቁ የነበሩ ምሁራንን እንዲለዩ ማድረግ አሰፈላጊ ነው ። በቡድናቸው ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ መገምገም ወይም መመዘን ተገቢ ነው።ከዚህም ውጭ የክፍል ውስጥ ያደረጉትን ገለፃናዘገባ በማየት የግንዛቤ ደረጃቸውን መለየት ይቻላል። ለሙከራ የተሰጡትን ጥያቄዎች በመጠቀም መልስ እንዲሰጡ በማድረግ ወይም ምክክር እንዲያደርጉ በማድረግ ተማሪዎች ያሳዩትን እንቅስቃሴ በማየት መመዘን ይቻላል።

በንዑስ ርዕሱ መጨረሻ የተሰጡትን የማረጋገጫ ጥያቄዎች በቤት ስራ መልክ ወይም በክፍል ውስጥ በመስጠት ከዚህ ርዕስ የሚጠበቅባቸው ን ብቃት መጎናጸፋቸውን ማረጋገጥ ይቻላል። በመጨረሻም ግብረ መልስ መስጠት አስፈላጊ ነው ።

## 4.3 የኢንዱስትሪ አብዮት

**የክፍለ ጊዜ ብዛት……… 3**

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባቸው የትምህርት ብቃት፤**

- የእንዱስትሪው አብዮት በአለም ምጣኔ ሀብት ላይ ያመጣውን መሰረታዊ ለውጥ ይዘረዝራሉ
- የእንዱስትሪው አብዮት ምንነት ይገልፃሉ
- የእንዱስትሪው አብዮት መስፋፋት ጥቅምና ጉዳት በመገምገም ይገነዘባሉ

## ዋና ዋና ነጥቦች

የኢንዱስትሪው አብዮት የሰው ልጅ ከባህላዊ የማምረት ዘዴን ወደ ዘመናዊ የማምረት ዘዴ ያሸጋገረበት ሂደት ነው፡፡ ይህ አብዮት በእንግሊዝ ሀገር የተጀመረ ሲሆን ብዙ የተመቻቹ ሁኔታዎች ስለ ነበሩ ነው ።ከነዚህ ሁኔታዎ ውስጥ፤ በቂ የብረት ምርት በመኖሩ፣ መልካም አስተዳደር በመኖሩ፣ሳይንሳዊ ጥናትና ምርምር መኖሩ እና የሀገሪቱ የመሬት አቀማመጥ ለለውጡ መስረታዊ ምክንያቶች ናቸው። ከእነዚህም ለውጦች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡

- በእጅ ከማምረት ወደ በማሽን ማምረት መሻገር

- በማገዶ ከመጠቀም ወደ የከሰል ድንጋይ መጠቀም መሸጋገር
- የጭነት እንስሳትን ከመጠቀም ወደ ባቡርና መኪናን መጠቀም የተሸጋገረበት ጊዜ ነው ።

የእንዱስትሪው አብዮት የሰውን ልጅ የኑሮ ሁኔታ እንደቀየረው ሁሉ ትላልቅ ጉዳቶቸችንም አስከተሏል።እነሱም፡ የአየር ብክለት፣ የኬሚካል ጦር መሳሪያ በከፍተኛ ደረጃ መመረት፣ የኒውክለር ጦር መሳሪያ እሽቅድምድም መስፋፋት እና የመሳሰሉት ናቸው ። ስለዚህ የእንዱስትሪው አብዮት ያመጣውን ጉዳትና ያስገኘውን ጥቅም በማወዳደር ማጋናዘብ ጥሩ ነው ። የፋብሪካዎችን መስፋፋት ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት በቂ የሆነ ግንዛቤ መኖር ከዋና ዋና ነጥቦች ውስጥ አንዱ ነው ።

## ቅድመ ዝግጅት

ከሁሉም በፊት አጠቃላይ ግንዛቤና ጠለቅ ያለ እውቀት መኖር አስፈላጊ ስለሆነ ከዚህ ይዜት ጋር የተያያዙ የተለያዩ ማስረጃዎችን ማንበብ ይጠበቅብሀል/ሻል።በዚህ መሰረት ስለ እንዱስትሪው አብዮት መስፋፋት በአግባቡ መገንዘብ አስፈላጊ ነው ።በመቀጠልም ከእንግሊዝ ሀገር በመጀመር ወደ ተለያዩ አህጉራትና ሀገራት የተስፋፍውን ፋብሪካ የሚያሳይ ካርታ ማዘጋጀት ነው። የእንዱስትሪውን አብዮት ጥቅም የሚያሳዩ የአውሮፕላን፣ የትላልቅ መርከቦች፣ሳተለይቶችና የመሳስሉትን ሥዕልና ፎቶግራፎች ቢዘጋጅ በጣም ጥሩ ነው ። እንዲሁም የአየር መበከልንና ጉዳቱንም የሚያሳዩ ሥዕልና ፎቶግራፎችን ማዘጋጀትም አስፈላጊ ነው ።

በመቀጠልም ጥራቱን የጠበቀ የትምህርት ዕቅድ ማዘጋጀት ያስፈልጋል። በዚህ መሰርት ለዚህ ንዑስ ርዕስ ሶስት(3)ክፍለ ጊዜ ተመድቧል። የትምህርቱ ይዜት ከተሰጠው ክፍለ ጊዜ ጋር መመጣጠኑን አረጋግጥ/ጪ። ቢቻል ቢቻል ይህን ይዜት በደንብ ሊግልፅ የሚችን አጠር ያለ ማስታወሻ ቢዘጋጅ በጣም ጥሩ ነው ። በአጠቃላይም ቀደም ብሎ ማንበብና መዘጋጀት የመምህሩን/ሯን በራስ መተማመን ስለሚያጎለብት በክፍል ውስጥ ማብራሪያ የመስጠት ብቃትን ይጨምራል።በዚህ መሰረት መዘጋጀት ወሳኝ ነው፡፡

## የመማር መማር ዘዴ

ተማሪዎች የእንዱስትሪው አብዮትን በተመለከተ የቀረበውን ይዜት በአግባቡ እንዲረዱት ክፍሉን በሶስት/አራት ቡድን በመክፈል የእርሻ መሳሪያዎች፣ የቤት ዕቃዎች የትራንስፖርት እና የተለያዩ አልባሳት የፋብሪካ ውጤት መሆናቸውን እንዲረዱ አጠር ያለ ምክክር እንዲያደርጉ ማድረግ ጥሩ ነው ። በተጨማሪም የእንዱስትሪው አብዮት አጀማመርና የፋብሪካዎች መስፋፋት እንዲገነዘቡ ለማድረግ በይዘቱ ላይ አጭር ዘገባ አዘጋጅተው በክፍላቸው ውስጥ እንዲያብራሩ አድርግ/ጊ ። እንዲሁም ክፍሉን በሁልት ቡድን በመክፈል የእንዱስትሪዎች መስፋፋት ያስገኘውን ጥቅምና ያስከተልው ጉዳት ላይ ክርክር እንዲያደርጉ ማደራጀትና ሀሳባቸውን መረዳት አስፈላጊ ነው ።

በዚህ መስረት ሁለት ቡድኖች በማዋቀር የክርክር መርሆዎችን ላይ አጭር ማብራሪያ መስጠት አስፈላጊ ነው ። በሌላ በኩልም እንደ ምልከታ፣ድራማ፣ ገለፃ፣ የቡድን ምክክር እና የመሳሰሉትን የማስተማር ዘዴዎች ስራ ላይ ማዋል ይቻላል። የፕሮጀክት ስራ በመስጠት የፋብሪካ ውጤት የሆኑትንና በቤታቸው የሚገኙትን እቃዎች በማስመሰል ሰርተው እንዲያሳዩ ማድረግ የሙያ ክህሎታቸውን እንዲያዳብሩ ማድረግ ተገቢ ነው ።አሳታፊ የሆነና ሁሉን ያማከለ የማስተማር ዘዴ መጠቀምም በጣም አስፈላጊ ነው ።.

## ተማሪዎች የፈጠራችሎታቸውን እንዲያጎለብቱ ማድረግ

በቅድሚያ ይህ የትምህርት ይዜት ልዩ ተሰጥዖ ያላቸውን ተማሪዎች ለመርዳት ምን ያህል በቂና አስፈላጊ እንደሆነ ተረዳ/ጂ። በዚህ መሰረትም በአከባቢያቸው የሚገኙትን የፋብሪካ ውጤቶች አስመስሎ በመስራት የተሻለ ተነሳሽነት ያላቸውን ተማሪዎች ለይቶ ማበራታታት ይገባል። ካርታ በማንሳት፣ ግጥም በመፃፍና አዳዲስ ሀሳቦችን የሚያፈልቁ ተማሪዎችን አበረታታ/ቺ። ይሁን እንጂ ልዩ ተሰጥዖ ያላቸውን ተማሪዎች ለመርዳት የተሻለ አማራጭ ማዘጋጀት ያስፈልጋል።

## ተከታታይ ምዘናና ግምገማ

ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባቸው የትምህርት ብቃት መጎናጸፋቸውን ለማረጋገጥ የተለያየ ተከታታይ ምዘናና ግምገማ መጠቀም አስፈላጊ ነው። በመሆኑም ለተማሪዎች

የቡድን ስራ በመስጠትና ተሳትፎዋቸውን በማየት፣በክፍል ውስጥ ማብራሪያ እንዲሰጡ በማድረግ የተሳትፎ ደረጃቸውን መገምጋምና እንዲሁም የማስተካከያ ሐሳብ መስጠት አስፈላጊ ነው ።

## 4.4. አንደኛው ናሁለተኛው የአለምጦርነቶች

የክፍል ጊዜ ብዛት……… 6

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባቸው የትምህርት ብቃት፤**

- በሁለቱም የአለም ጦርነቶች ላይ የታዩትን ክስተቶች ይገልፃሉ
- በአንደኛውና ሁለተናው የአለም ጦርነቶች ላይ አጠር ያለ ዘገባ ያቀርባሉ።

### ዋና ዋና ነጥቦች

ከጥንት ዘመን ጀምሮ የሰው ልጅ እርስ በርስ ሲዋጋና አንዱ በአንዱ ላይ ሲዘምት እንደኖረ ይታወቃል። በመሆኑም ትላልቅ የሚባሉ ጦርነቶችን በብዙ ሀገራት መካከል ተካህሂደዋል። ይሁን እንጂ የአለም ጦርነት በሚባል ደረጃ የተካሄዱ አይደሉም። የአለም ጦርነት በመባል የሚታወቁት ሁለት ናቸው ። እነሱም አንደኛው (1914-18) እና ሁለተኛው (1939-45) የአለም ጦርነቶች ናቸው ።

አንደኛው የኣለም ጦርነት መሰረታዊና ቅጽበታዊ ምክንያቶች አሉት። ከዚህም ውጭ ጦርነቱ የራሱ የሆነ ሂደትና ውጤቶችም አሉት።መሰረታዊ የሆኑ ምክንያቶች፡ በአውሮፓ የብሔራዊ እንቅስቃሴ መጎልበት፣ የአውሮፓዊያን መካከል ቅኝ ግዛት ለማስፋፋት የተጀመሩት ውድድር፣የተለያዩ የጦር ጎራዎች መመስረት እና የፖለትካዊና ምጣኔ ሀብታዊ ውድድር ናቸው ።

**በጦርነቱ የደረሱ ዋና ዋና ጉዳቶች፡**

- ወደ 10 ሚሊዮን የሚገመቱ ህዝቦች ሞተዋል፣ 20 ሚሊዮን ደግሞ ከአከባቢያቸው በመፈናቅላቸው ለእንግልት ተጋልጠዋል
- ጀርመን ለተለያዩ ሀገራት ካሳ እንድትከፍል መገደድ

- እንደ አሜሪካና ራሽያ ያሉት ሀጋራት የፖለትካና ምጣኔ ሀብት የበላይነት አግኝተዋል
- እንደ ኦቶማን ቱርክ፣ኦስትሪያ ሃንጋሪና የጀርመን ኤምፓየርና በንጉሣን ዘውድ የሚተዳደሩ መንግስታት ፈርሰዋል።

ከዚህም ውጭ የቨርስይለስ ስምምነትና የአለም መንግስታት ሊግ መመስረት ከአንደኛው የአለም ጦርነት ጥቅሞች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ናቸው ።

እንደ አንደኛዉ የአለም ጦርነት ሁለተኛዉም የአለም ጦርነት የራሱ የሆኑ ብዙ መሰረታዊና ቅጽበታዊ ምክንያቶች አሉት።

- መሰረታዊ የሁለተኛዉ አለም ጦርንት ምክንያቶች፡
    - የአንደኛዉ አለም ጦርነት ያስከተለዉ ጉዳቶች
    - የፋሽስታዊና ናዚስታዊ አመለካከቶች መስፋፋት
    - የአለም መንግስታት ሊግድክመትና የመሳሰሉት ናቸዉ።
- የሁለተኛዉ የአለም ጦርነት ያስገኘዉ ጥቅሞች፡
    - የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መመስረት
    - የቅኝ አገዛዝ ስርዓት መፍረስ፣ የብዙ ሀገራት ነፃ መዉጣትና የእንዱስትሪዎች መስፋፋት ናቸዉ።
- ሁለተኛው የአለም ጦርነት ያስከተለው ጉዳቶች፡
- በተለያየ መለኩ በአለም ህዝቦች ላይ የተለያየ ጉዳት አድርሷል።
  ለምሳሌ፡ወደ 50 ሚሊዮን የሚሆኑ ሀዝቦች ሞተዋል፣ ከዚህ ቁጥር በላይ የሚሆኑት ደግሞ ከአከባቢያቸው ተፈናቅለዋል፣ ብዙ ቤተሰቦች ተበትነዋል፣ ልጆች ያለ አሳዳጊ ሲቀሩ አርጋዊያንም ያለጧሪ ሊቀሩ ችለዋል።
- በተጨማሪም ብዙ ከተሞችና መሰረታዊ ልማቶች ወድመዋል፣ ስራ አጥነትና ድህነት መስፋፋት እና የመሳሰሉት ክስተቶች ሁለተኛው የአለም ጦርነት ካስከተላቸው ጉዳቶች ዋናዋናዎቹ ናቸው ።

## ቅድም ዝግጅት

መምህር/ት! ከሁሉ አስቀድመህ/ሽ የአንደኛዉንና የሁለተኛዉን የአለም ጦርነቶች መነሻ ምክንያቶች፣ የጦርነቶቹ ሂደቶችን እና የጦርነቶቹን ዉጤቶች በጥልቀት መገንዘብ ይግባል። እነዚህ ጦርነቶቹም የተካሄዱባቸዉ ስፍራዎች የሚያሳይ ካርታ ማዘጋጀት ያስፈልጋል። በተጨማሪም ሁለቱን የአለም ጦርነቶች የሚያሳዩ ፖስተሮችን፣ ፎቶግራፎችን እና ቪዲዮዎችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል።

በተለይም በጦርነቶቹ ዉስጥ ወሳኝና ትልቅ ሚና የተጫወቱ ግለሰቦችን ለምሳሌም እንደ ሂትለርና ሞሶሎኒ ያሉትን ፎቶግራፋቸዉን ማፈላለግ አስፈላጊ ነዉ። ከተቻለም በድምፅና በምስል መልክ ጦርነቶቹን ሊያስረዳ የሚችል እንደ ቪድዮና የምስል መረጃዎችን ማዘጋጀት የተሻለ ነው። ለነዚህ ንዑስ ርዕሶች**ስድስት** (6) ክፍለ ጊዜዎች ተስጥተዋል። በመሆኑም ለእያንዳንዳቸዉ **ሶስት ሶስት** ክፍለ ጊዜዎች ተመድበዋል።በዚሁ መሰረትም ይዘቶችን መጥኖ መጠቀም ይገባል።

## የመማር ማስተማር ዘዴ

አንደኛውንና ሁለተኛዉን የአለም ጦርነቶች ለማስተማር የተለየዩ የማስተማር መማር ዘዴዎችን መጠቅም ይቻላል።ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባቸው የትምህርት ብቃት ሊያረጋግጥ የሚያስችል ዘዴን ለይተዉ መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡ የአንደኛውንና የሁለተኛውን የአለም ጦርነቶች መሰረታዊና ቅጽበታዊ ምክንያቶችን እንዲያወዳድሩና እንዲገመግሙ ማድረግ አንዱ ዘዴ ነዉ። በአንደኛውንና ሁለተኛውን የአለም ጦርነቶች ጊዜ የተመሰረቱና የተደራጁ የጦር ጎራዎችን በመዘርዘር አመሰራረታቸውና አላማቸውንም ጭምር ማስረዳት ተገቢ ነው።

የአለም ካርታን በመጠቀም ጦርነቶቹ የተካሄዱባቸውን ዋና ዋና አካባቢዎች እንዲያሳዩ መደገፍ ያስፈልጋል። በተቻለ መጠንም አንደኛውንና ሁለተኛዉ የአለም ጦርነቶች ያስከተሉትን ጉዳቶች ለማስገንዘብ እንዲረዳ ፖስተሮችን፣ ቪዲዮዎችንና ፎቶግራፎችን መጠቀምትምህርቱን ተቸባጭስለሚያደርገው ለመጠቀም ሞክር/ሪ። በተጨማሪም እንደ ማወዳደር፣ ክርክር፣ ድራማ፣ ዘገባ ማቅረብ እና የመሳሰሉት ዘዴዎችን

መጠቀም ይቻላል። መረሳት የሌለበት ነገርግን አካታችና አሳታፊየማስተማር ዘዴን ስራላይ ማዋልን ነው።

## ተማሪዎች የፈጠራችሎታቸውን እንዲያጎለብቱ ማድረግ

የተለየ ተሰጥዖ ያላቸው ን ተማሪዎች መርዳት ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ይረዳቸዋል። በዚህ መሰረትም ተማሪዎች ሁለቱንም የአለም ጦርነቶች ጥቅምና ጉዳት በድራማ መልክ እንዲያሳዩ ማበረታታትና የማገናዘብ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ማድረግ ጥሩ ይሆናል።

## ተከታታይ ምዘናና ግምገማ

የተሻሉ ተከታታይ ምዘናና ግምገማ ዘዴዎችን በመምረጥና በስራ ላይ በማዋል የመምህሩ/ሯ ዋናው ኃላፊነት መሆኑን መዘንጋት አይጋባም።.ተማሪዎች ትምህርቱን ካጠናቀቁ በኋላ ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባቸው የትምህርት ብቃት መጎናጸፋቸውን የምናረጋግጥበት በግምገማ ነው ።ስለዚህ በካርታ ላይ ጦርነቶቹ የተካሄዱባቸውን አካባቢዎች እንዲያሳዩ በመጠየቅ መመዘን ይቻላል፡፡ .

እንዲሁም በቡድናቸው ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ በማየት፣ የሚያቀርቡትን ዘጋባና የሚሰጡትን ማብራሪያ መዝግቦ በመያዝና በማጠናከር ችሎታቸውን መመዘን ይቻላል።በመጨረሻም የቤት ስራዎችን ወይም የክፍል ስራዎችን በመስጠት መገምገም ሌላው አማራጭ ነው ። በተለይም ለዚህ ዓላማ ተብሎ በእያንዳዱ ንዑስ ርዕስ ስር የተሰጡትን የማረጋገጫ መልመጃዎችን መጠቀም ተመራጭ ነው ።

## 4.5. ቀዝቃዛው የአለም ጦርነት

የክፍለ ጊዜ ብዛት......... 3

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባ የትምህርት ብቃት፤**

- ቀዝቃዛው የአለም ጦርነትን ባህሪይ ይገልፃሉ
- ቀዝቃዛው የአለም ጦርነት ያለፈበትን አካሄድ ይገልፃሉ

- ቀዝቃዛው  የአለም ጦርነት ጥቅምና ጉዳት ይገነዘባሉ።

## ዋና ዋና ነጥቦች

ቀዝቃዛዉ የአለምጦርነትን ምንነት፣ መነሻ ምክንያቶችን፣ የጦርነቱ ጥቅሞችና ጉዳቶችን በጥልቀት ማወቅ ከዋና ዋና ነጥቦች ዉስጥ የሚመደብ ነዉ። በዚሁ መሰረትም ቀዝቃዛዉ የአለም ጦርነት የአመለካከት፣ የፖሊሲና የፖለቲካዊና ምጣኔ ሀብታዊ የበላይነት ፍላጎት ከመታየት የመነጨ ነዉ።  በዚሁም መሰረት የአለም ታላላቅ ሀገራት እርስ በራስ መጠራጠር ጀመሩ።በመቀጠልም በካፒታሊስቶችና በኮሚኒስቶች አመለካከት መካከል በተፈጠረ የሀሳብ ልዩነት ምክንያት ግጭት ሊጀምር ችሏል።

የካፒታሊስቶች ምጣኔ ሀብታዊ ፖሊሲ የነፃ ገበያን የሚከተልና የሀብት ክምችትን የሚያበረታታ ነዉ። የኮሚኒስቶችምጣኔ ሀብታዊ ፖሊሲ ደግሞ የጋራና (ጋርዮሽ) የእዝ ስርዓትን የተከተለ ነዉ። ይህም በጋራ ሰርቶ በጋራ ማደግን የሚያበረታታ ሲሆን ገበያዉ የሚመራዉ በመንግስት የዋጋ ተመን ነዉ። መምህር/ት እንግዲህ ይህንን ይዜት ከተገነዘብህ/ሽ በኃላ የተማሪዎችን ግንዛቤ ሊገመግሙ የሚችሉ የግንዛቤ ጥያቄዎችን ማዘጋጀት ይገባል። በዚህ መሰረትም ማስተማርን እንዳትረሳ/ሺ።በተጨማሪም በአሁኑ ጊዜ የዓለም ተጨባጭ ሁኔታ ምን እንደሚመስል በጥልቀት ተገንዘቡ።

## ቅድመ ዝግጅት

የኮሚኒስትና የካፒታሊስት ሀገሮች በብዛት ይገኙ የነበሩበትን አከባቢዎችን የሚያሳይ የአለም ካርታ አዘጋጅ/ጂ። ስለቀዝቃዛዉ የዓለም ጦርነት የሚገልጹ የተለያዩ ማስረጃዎችን ማጠናከርና በጥልቀት ማንበብ ግድ ይላል። ከተቻለም በቀዝቃዛዉ የአለም ጦርነት ዉስጥ ትልቅ ተሳትፎ ያላቸዉን ሰዎች ለምሳሌም የራሽያ፣ የአሜሪካ፣ የጀርመን ፕሬዚዳንቶች እና የሌሎችንም ፎቶግራፍ የትምህርቱንይዜት በሚመጥን መልኩ ማዘጋጀት ይጠበቅብሀል/ሻል። በተጨማሪም የዘመናዊ ጦር መሳሪያዎችን(ሚሳኤሎችን) ፎቶግራፍ እና ፖስተሮች ማሰባሰብ ጥሩ ነዉ። በመቀጠልም ከትምህርቱ ይዜት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የዕለቱን የትምህርት ዕቅድ ማዘጋጀት።ይህ የትምህርት ዝግጅት ጥራቱን የጠበቀ መሆን አለበት። በዚህ መሰረት ለዚህ ይዜትሶስት(3) ክፍለጊዜ ተሰጥቷል።

## የመማር ማስተማር ዘዴ

እንደሚታወቀዉ የመማር ማስተማር ዘዴዎች ብዙ ናቸዉ።ስለዚህ ያንተ/ቺ ትልቁ ድርሻ የተሻለ ውጤት ሊያመጣ የሚችል ዘዴን መምረጥ ነዉ።ከትምህርቱ ይዜትጋር ተያያዥነት ያለው የማስተማር ዘዴ ማወቅ አስፈላጊ ነዉ።

በመሆኑም ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባቸው የትምህርት ብቃት ለማሳካት የተለያዩ የማስተማር ዘዴ መጠቀም ወሳኝ ነው። በዚህ መሰረትም እንደ ማሳየት፣ ክርክር፣ ዘገባ ማቅረብ፣ የክፍል ውስጥ ገለፃ እና ከመሳሰሉት ዘዴዎች ዉስጥ መርጦ መጠቀም ግድ ይላል። አካታችና አሳታፊ የማስተማር ዘዴንምመጠቀምይኖርባችኋል።

## ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያጎለብቱ ማድረግ

የተለየተሰጥዖ ያላቸዉን ተማሪዎች መርዳት ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸዉን እንዲያዳብሩ ስለሚረዳቸዉ ማበረታታትና ማጠናከር ያስፈልጋል። በዚሁ መሰረት ተማሪዎች የመልመጃ ጥያቄዎችን በሚሰሩበት ጊዜ ቀድመዉ የሚጨርሱና ከፍተኛ አፈፃፀም ያሳዩትን ተማሪዎች በመለየት ከትምህርቱ ይዜትጋርየሚያያዙ ተጨማሪ ስራዎችን በመስጠት ማበረታታት ይገባል።

## ተከታታይ ምዘናና ግምገማ

ተማሪዎች በቡድን ስራ ላይ ያላቸውን ተሳትፎ በማየትና በመከታተል መመዘን ይቻላል። በዚህ መሰረትም ያደረጉትን ክርክር፣ ያቀረቡትን ዘገባ እና ያቀረቡትን ገለፃ በመከታተል፣ መመዝገብ እና መረጃ በመያዝና መረጃዉን በማቀነባበር መመዘን ይቻላል። ከዚህ ውጭም የክፍል ስራ በመስጠትና የአፍ ጥያቄ በማቅረብ መገምገም ይቻላል። በሂደትም ጠንካራና ደካማ ጎኖችን በመገምገም ግብረ መልስ መስጠት በጣም አስፈላጊ ነዉ።

## የመልመጃ 4.1 መልሶች

1. ፖርቹጋልና እስፔን
2. ለመጀመሪያ ጊዜ አለም ክብ መሆኗን ያረጋገጠዉን ቡድን በመምራት ይታወቃል። ይህ ቡድንም ከ1519-1522 ዓም ጉዞዉን አጠናቋን።

3. ሰሜን አሜሪካና ደቡብ አሜሪካ ከአሰሳ ዘመን በፊት በዓለም ህዝብ አይታወቁም ነበር። ይሁን እንጂ በክርስቶፈር ኮሎምቦስ የሚመራዉ ቡድን በ1492 ዓም ባደረጉት አሰሳ ሊታወቁ ችለዋል።
4. ካርታን የመጠቅም ሞያ፣ ኮምፓስ ለጉዞ አገልግሎት መዋሉ፣ በእንፋሎትና በነዳጅ ሀይል የሚሄዱ መርከቦች መገኘት(መፈብረክ)ና የሀገሮች የባህር ኃይል መጠናከር ናቸዉ።

## የመልመጃ 4.2 መልሶች

**ክፍል I**

1. እየተረሳ የመጣውን የግሪኮ-ሮማ ጥንታዊ ስልጣኔ፣ሞያዎች፣እውቀቶች እንደገና ማጥናት፣ የሀሳብ ነፃነትና የምርምር ስራዎችን ማበረታታት.
2. የአዲሱ ፅንሰ ሀሳብ ዘመን የጥንታዊ ስልጣኔዎችን መልሶ በማጥናት የተጀመረ የምሁራን እንቅስቃሴ ሲሆን፣በተሓድሶ ደግም የካቶሊክ እምነት አሰራሮችን የማጥራትና የሀይማኖት ተሓድሶ ማድረግ ነው፣
3. ጣልያን ነች።ጣልያን ውስጥ በመጀመር ወደ ምዕራብ አውሮፓ ሀገራት ተስፋፍቷል።
4. የጥንታዊ ግሪክንናየሮማ ጽሁፎችን ማጥናት፣ በምክንያት ላይ የተሞረከዘ እውቀትን መፈለግ፣ የሀሳብ ነፃነትን መደገፍና በአፍ መፍች ቋንቋ መጠቀም ማለት ነው።
5. የዲሞክራሲ መብትና በመጻፍ ቅዱስ መርህ መሰረት በካቶሊክ ቤተክርስቲያናት ያለመከበር፣

**ከሰንጠረዥ 4.3.1. ላይ በማንበበ የማሪዎች ይህን ጥያቄ እንዲመልሱ አድርግ/ጊ**

| |
|---|
| • ማርቲን ሉተር፡ የተሓድሶ እንቅስቃሴ መሪ |
| • ሊኦናርዶ ዳቪንቺ፡ ስዕል በመሳል ሙያ ይታወቃል(ሞናሊዛ) |
| • ዊሊያም ሼክስፒር፡ በስነጽሁፍና ድራማ፣ ቲያቲር ጽሁፎች ይታወቃል |
| • ሚካኤል አንጄሎ፡ በቅርጻ ቅርጽና በስዕል ሙያ ይታወቃል። |

**የመልመጃ 4.3 ሀ መልሶች**

- መምህር/ትይፕሮጀክት ስራ በመስጠት እንዲሰሩ በማድርግ በመጨረሻም የእርምት መልስ ይሰጣቸው፡፡
- ተማሪዎች ሰርተው እንዲያቀርቡ በማድረግ የእርምት መልስ ይሰጣቸው፡፡

## የመልመጃ 4.3 (ለ)መልሶች

**ክፍል I**

1/ ሐሰት 2/ እው ነት 3/ እው ነት 4/እው ነት

**ክፍል II**

1. የድንጋይ ከሰልና የብረት ማዕድናት መኖር፣ ለዉሀ ትራንስፖርት ምቹ የሆኑ ወንዞች መኖርና በባህር መከበብ እንዲሁም የተሻሻሉ መርከቦች መፈብረክ ነዉ።
2. የሁለተኛዉ ደረጃ እንዱስትሪ አብዮት ዉጤት ነዉ
3. ጊዜን መቆጠብ፣ ምርታማነት መጀመሩና የሰዉ ልጅ እዉቀት በደንብ መጨመሩ ነዉ።
4. የአከባቢብክለት፣ስራ አጥነትና የድህነት መጨመር ፣ቤተሰብ መፍረስና የመሳሰሉት ናቸዉ።

## የመልመጃ 4.4 መልሶች

1. ብሔረተኝነት፣ ማዳላት፣የድንበር (ግዛት) ማስፋፋት (ኢምፐፔሪያሊዝም) እና የድንበር ፍላጎትነዉ
2. ፈርዲናንድ ፍራንሲስና ባለሴቱ ሶፊያ መገደል
3. ጃፓንየአሜሪካን የባህር ኃይል ማዘዣ ጣቢያ ፒርል ሀርበርን በመምታታቸዉ በ1917 የተወሰደ እርምጃ ነዉ
4. የህዝብ መፈናቀልና የቤተሰቦች መፍረስ እንዲሁ ሞትና የመሳሰሉት ናቸዉ
5. ተማሪዎች በቡድን ሆነዉ ተማክረዉ ገለፃ እንዲያደርጉ አድርግ/ጊ
6. ተማሪዎችየተለያዩ ማስረጃዎችን በማንበብ እንዲያቀርቡ አድርግ/ጊ

## የመልመጃ. 4.5. መልሶች

1. አሜሪካ(USA)እና ራሺያ (USSR)
2. የአለም ማህበረሰቦች መራራቅ፣ የጦር መሳሪያ እሽቅድምድም በጣም መጨመር፣የድህነትመስፋፋት እናየመሳሰሉትናቸዉ

3. ካፒታሊዝም(USA) እና ኮሚኒዝም(USSR)
4. አሜሪካና ራሺያ መካከል የስም ማጥፋት ዘመቻ ላይ የተመረኮዘ በመሆኑ በማደግ ላይ ባሉት ሀገራት ዉስጥ በእጃዙር ሲዋጉ ቆይተዋል።

## የምዕራፉ መጨረሻ መልሶች

### ክፍል I. የ'እውነት' ወይም 'ሐሰት' መልሶች

1/ ሐሰት 2/ እውነት 3/ሐሰት 4/ እውነት 5/ እውነት

### ክፍል II. የምርጫ ጥያቄዎች መልሶች

1/ ለ 2/ ሀ 3/ ለ 4/ መ 5/ ሐ 6/ ሀ

### ክፍል. III. ቅደም ተከትል የማስተካከል መልሶች

1. የሂሮሺማና ነጋሳኪ በመምታት(1945)
2. የፋሺስት ፓርቲ ስልጣን መያዝ (1922/3)
3. የናዚ ፓርቲ ስልጣን መያዝ (1932/33)
4. የአለም ምንግስታት ሊግ መመስረት(1920)
5. የቨርሳይለስ ስምምነት(1919)

### ክፍል IV. አጫጭር የጹሁፍ መልስ

1. ሂሮሺማና ነጋሳኪ
2. ሁለት ጎራ (ካፒታሊስትና ኮሚኒስት)
3. የአዲሱ ጽንሰ ሀስብ መፍለቅ

# ምዕራፍ 5 የአፍሪካ ታሪክ ከ15ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ

**የክፍለ ጊዜ ብዛት**......... 9

**ከዚህ ምዕራፍ የሚጠበቁ ውጤቶች**

**ይህ ምዕራፍ ከተጠናቀቀ በኋላ ተማሪዎች፣**

- በአፍሪካ ህዝቦች ላይ የባርያ ንግድ ስርዓት ያስከተለውን ጉዳት ይገልጻሉ
- የፀረ ቅኝ አገዛዝ ስርዓት አመለካከትን ያጎለብታሉ
- የአፍሪካ ህዝቦች ነፃነታቸውን ለማግኘት ያደረጉትን ትግል፣ በቅኝ ግዛት ስርዓት ዘመን የነረበውን ምጣኔ ሀብታዊና ፖሊቲካዊ ግንኙነቶችን ይገናዘባሉ

## መግቢያ

ከ1500 ዓ.ም በፊት አውሮፓውያኖች አፍሪካን እንደ ጨለማና የማይታወቅ አህጉር አድረጎ ይቆጥሩ ነበር፡፡ ከ16ኛው ክፍለ ዘመን በኋላ ግንይህ ሁኔታ መቀየር ችሏል፡፡ በዚህ መሰረት የአፍሪካ ህዝቦች የተለያዩ ምጣኔ ሀብታዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ችግሮችን አሳልፈዋል፡፡ ከእነዚህ ችግሮች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የባርያ ንግድ ስርዓትና የአውሮፓውያን ቅኝ ግዛት ስርዓት ናቸው፡፡

እነዚህ ስርዓቶች የአፍሪካ ህዝቦችን የእኩልነትና የነፃነት መብቶችን የገፈፉነበሩ፡፡የአፍሪካ ህዝቦችን ያለፍላጎታቸው ወደ ሌላ አህጉር እንዲጓዙ በማድረግ አፍሪካ በፍተኛ ቁጥር የአምራች ኃይሏን እንድታጣ ማድረግ ችሏል፡፡ በአጠቃላይ የባርያ ንግድና የቅኝ ግዛት ስርዓቶች ብዙ ቁጥር ያለው ጉልበትና የአምራች ቡደን ኃይሏን በመበዝበዝ አፍሪካ ለምጣኔ ሀብታዊ፣ ፖለቲካዊ እና ለማህበራዊ ችግሮች እንድትጋለጥ አድርጓታል፡፡

## 5.1. የባርያ ንግድ ስርዓት

**የክፍለ ጊዜ ብዛት**...... 2

ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባቸውየትምህርት ብቃት፣

- የባርያ ንግድ ስርዓት በአፍሪካውያኖች ላይ ያደረሰውን ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ጉዳቶችን ይገናዘባሉ
- የባርያ ንግድ ስርዓት ለመከላከል አፍሪካኖች ያካሄዱትን ትግል ያብራራሉ
- የባርያ ንግድ ስርዓት ሂደት በመገምገም ግንዛቤያቸውን ያሳድጋሉ

**ዋና ዋና ነጥቦች**

ለባሪያ ንግድ መጀመር የተለያዩ ምክንያቶች አሉ፡፡ እነሱም ለቤት ውስጥ ስራና ለእርሻ ስራ የሰውን ጉልበት የማግኘት ፍላጎት መፈጠሩ ነው፡፡ የባርያ ንግድ በይፋ የተጀመረው ከጂኦግራፊያዊ አሰሳ ዘመን በኋላ ነው፡፡ በዚህ መሰረት አዉሮፓውያኖች በምዕራብ አፍሪካ ድንበር አከባቢዎች ብዙ የባሪያ ንግድ ማዕከላት አቋቁመዋል፡፡ ከእነዚህ የአዉሮፓ ሀገሮች ውሰጥ ፖርቹጋል ባሮችን ወደ ሳኦቶሚናፕሪንሲፔ ደሴቶች በማጓጓዝ ባሮችን ለእርሻ ስራ ልትጠቀምባቸዉ ችላለች።እንዲሁም ባሮችን ወደ አዉሮፓ መነገድ ጀምራ ነበር።

በ15ኛዉ ክፍለ ዘመን ዉስጥ የአሜሪካ አህጉር መገኘት የባሪያ ንግድን እንዲስፋፋ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡ ምክንያቱም የፖርቹጋልና እስፔን ሰፋፊ የጥጥ፣ የሸንኮራና የትምባሆ እርሻዎች ጥሬ ምርቶችን ማምረት ስለጀመሩ ብዙ የሰዉ ጉልበት ስለሚያስፈልጋቸው ነው፡፡ የባሪያ ንግድ ስርዓት በአፍሪካውያኖች ላይ ከፍተኛ የሆነ ማህበረሰናዊ፤ ፖሊቲካዊና ስነልቦናዊ ችግሮችን እንዲያሳልፉ አድርጓል፡፡እነሱም ሕፃናትን ያለ አሳዳጊ፣አረጋዊያንን ደግሞ ያለ ጧሪ እንዲቀሩ በማድረግ፣ አፍሪካ አምራች የሰዉ ኃይሏን እንድታጣ በማድረግ የድህነትመስፋፋት፣ የፖለቲካ አለመረጋጋትና የእርስበርስ ጦርነት መስፋፋትን አስከትሏል።

በአጠቃላይ ለባሪያ ንግድ ስርዓት አጀማመርና በአፍሪካውያኖች ላይ ያመጣውን ጉዳት ለተማሪዎች ማስረዳት አስፈላጊ ነው፡፡ የባሪያ ንግድ ከአፍሪካ ማስቀረት የተቻለው በአፍሪካውያን ትግልና ከኢንዱስትሪዉ አብዮት ጋር ተያይዞ የመጡት ለዉጦች መሆናቸውን ለተማሪዎች ማስረዳት ከዋና ዋና ተግባሮች ውስጥ አንዱ ነው ።

## ቅድመ ዝግጅት

መምህራን ይህንን ርዕስ ማስተማር ከመጀመራቸው በፊት በቂ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ የመማር ማስተማር ሂደቱን የተሳካእንዲሆንያደርጋል፡፡ ስለዚህ የባርያ ንግድ ስርዓት የሚለውን ርዕስ ከማስተማርዎ በፊት

- የባርያ ንግድ መስመሮችን እንዲሁም ባርያዎች የተለያዩ ስራ ላይ ተሰማርተው ሲሰሩ የሚያሳይ ፖስተርን ማዘጋጀት፤

- ከባርያንግድ ስርዓት ጋር ተያያዥነት ያላቸው መረጃዎች እንደ ተማሪ መጽሐፍ፥ የተለያዩ ዋቢ መጽሐፍት፣ በመምህሩ መምሪያ ውስጥ የተዘረዘሩት ይዘቶችን በደንብ መገንዘብ ያስፈልጋል፤
- በአከባቢ ከሚገኙት ቁሳቁሶች በመጠቀመምከአፍሪካ ወደ አሜሪካና ከአሜሪካ ወደ አውሮፓ የሚሄድ የባርያ ንግድ መስመሮችን የሚያሳይ ካርታ ማዘጋጀት፤
- የባርያ ንግድን ሲቃወሙ የነበሩትን የታዋቂ ሰዎችን ፎቶግራፍ ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው፡፡

ይህን ርዕስ ለማስተማር የተሰጠው ክፍለ ጊዜ ብዛት **ሁለት** (2) ስለሆነ በዚህ ክፍለ ጊዜ ውስጥ የተቀመጠውንይዜት ለማጠናቀቅ ጥራት ያለው የትምህርት ዕቅድ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴ

ይህንን ርዕስ ለማስተማር የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን መጠቀም አለባችሁ፡፡ በተጨማሪም የባርያ ንግድ ስርዓት ምንነት፣ የባርያ ንግድ ስርዓትተሳታፊዎችን እነማን እንደሆኑ፣ በአብዛኛው የተሳተፉ ሀገራትን ተማሪዎች በቡድን እንዲወያዩበት ማድረግ አስገላጊ ነው፡፡ የተወያዩበትን ሃሳቦች እንዲያቀርቡ ማድረግ አለባችሁ፡፡በተማሪ መጽሐፍ ውስጥ ያሉትን ሥዕሎችና ሌሎች ለትምህርት መርጃ ያዘጋጃችሁትን ሥዕል ለተማሪዎች በማሳየት የተረዱትን ሀሳብ እንዲገልፁ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ እንዲሁም የባርያ ንግድን አስመልክቶ አጭር ዘገባ በማዘጋጀት እንዲከራከሩ ማድረግ ይቻላል፡፡ የተለያዩ አሳታፊ እና ሁሉን አቀፍ የሆኑ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡

## ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያጎለብቱ ማድረግ

ተማሪዎች በተለያየ መንገድ የፈጠራችሎታቸውን እንዲያጎለብቱ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ተማሪዎችን መልመጃዎችን እንዲሰሩና ካርታ እንዲያነሱ ማድረግ ይጠበቅባቸወኋል፡፡ያነሱት ካርታ ላይ የምስራቅ አፍሪካ ሀገሮችን በማንሳት የራሳቸውን ተሰጥዖ/ፈጠራ በመጨመር ለሌላ ተማሪዎች ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ ማድረግ፡፡ ልዩ ተሰጦ ያላቸው ተማሪዎችን በውይይትና ሰርቶ በማሳየት ላይ የሚያደርጉትን ተሳትፎ በመከታተል ማበረታታት አስፈላጊ ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ሥዕል የመሳልን ጥበብና መተንተን፣ የባርያ ንግድ ስርዓትን የሚያሳይ ካርታን በማንሳት በንግድ ስርዓቱ ላይ ያላቸውን ግንዛቤ በመገምገም ማበረታታት ተገቢ ይሆናል፡፡

## ተከታታይ ምዘና

የተለያዩ የትምህርት ይዘቶችን በተለያዩ የተከታታይ ምዘና ዘዴዎችን በመጠቀም መገምገም ይቻላል፡፡ በዚህ መሰረት ተማሪዎች የሚያደርጉትን ተሳትፎ መከታተልና ስዕልን በማየት የተረዱትን እንዲናገሩ በማድረግና ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚያሳዩትን የባህሪይ ለውጥ በተከታታይ መመዘን አስፈላጊ ነው፡፡ በመጨረሻም የተማሪዎችን ጠንካራና ደካማ ጎን በመለየት ግብረመልስ በመስጠት ተማሪዎችን ማበረታታት አስፈላጊ ነው፡፡ተማሪዎች በግልና በቡድን የሚፈጽሙትን ድርጊቶች እንደ ካርታ ማንሳት፣ የተነሳ ካርታ ላይ መረጃ መግለጽና በንቃት መሳተፋቸውን መከታተልም አስፈላጊ ነው፡፡

## 5.2 የቅኝ አገዛዝ ስርዓት በአፍሪካ

**የክፍል ጊዜ ብዛት**……… 4

ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባቸው የትምህርት ብቃት፤

- የፀረ ቅኝ አገዛዝ ስርዓትላይ ያላቸዉን ሀሳቦች ያጎለብታሉ
- የአውሮፓ ሀገሮች ቅኝ አገዛዝ ስርዓት በአፍሪካውያኖች ላይ ያደረሰውን ጉዳቶችን ይረዳሉ
- የፀረ ቅኝ አገዛዝ ስርዓትትግልና ተቃውሞ አመለካከት ያጠናክራሉ

## ዋና ዋና ነጥቦች

ቅኝ ግዛት የሚለዉ ፅንሰ ሀሳብ ሰፊ መሆኑን መረዳት አስፈላጊ ነው፡፡ በተለያዩ ምሁራን የተጠናከሩ ገለፃዎችን ማገናዘብ ከመምህራን የሚጠበቁ ዋና ዋና ነጥቦች ናቸው፡፡ በዚህ መሰረት አበዛኛዉ ምሁራን ቅኝ ግዛት ማለት አንድ ሀገር በሌላ ሀገር ላይ ያለው የምጣኔ ሀብታዊና የፖሊቲካ የበላይነት በማለት ይገልፃሉ፡፡ በተጨማሪም ቅኝ ግዛት ማለት አንድ ሀገር የሌላውን ሀገር በመቀራመት የተፈጥሮ ሀብቱን በመዝረፍ ለራሱ ጥቅም ማዋልነዉ በማለት ይገልፃሉ፡፡ ቅኝ ግዛት የሚል ፅንሰ ሀሰብ ከዚህ ሌላም ትርጉም ሊኖረው እንደሚችል ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡

አውሮፓውያን አፍሪካን በቅኝ ግዛት የያዙት መሰረታዊ ምክንያቶች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የኢንዱስትሪ አብዮት መስፋፋት፣ አውሮፓውያን የአፍሪካን የተፈጥሮ ሀብቷን ለመቆጣጠርና ግዛታቸውን ለማስፋፋት ማቀዳቸው ነው፡፡

ከ16ኛው እስከ 18ኛው ክፍለ ዘመን አሳሾች ወደ አፍሪካ በመምጣት አፍሪካን ማስሰ ችለዋል፡፡በዚህ መሰረት አፍርሪካ ውስጥ በመዞር ወንዞችን፣ ተራራዎችን እና ማዕድናትያሉበትን አካባቢዎቸ ለይተው በማወቅ ለሀገራቸው መንግስት አሳውቀዋል፡፡ የአውሮፓውያኖች አሳሾች የተጓዙበትን መንገድ መለየት ከዋና ዋና ነጥቦች ጥቅቶቹ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ የቅኝ ግዛት ስርዓት አጀማመር ምክንያት በአፍሪካ እና በአፍሪካኖች ላይ ያደረሰውን ጉዳት በአግባቡ መረዳት ዋናው ነጥብ ነው፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

የአፍሪካን ታሪክ ማስተማር ትልቅ ዝግጅትን ይጠይቃል፡፡ ምክንያቱም ሰፊና ውስብስብ የሆነ የሰው ልጅን ታሪክ ያካተተ ነው፡፡ በተጨማሪም በቂ የሆኑ የአፍሪካ ታሪክ ምንጮች ተደራጅተው አለመኖራቸው ነው፡፡ ስለዚህ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ የመጀመሪያው የመመር ማስተማር ሂደት ነው፡፡

የአፍሪካ ቅኝ አገዛዝ ዓመታት እናታሪክን የሚያሳይ ካርታ ማዘጋጀት፤ የተለያዩ ዋቢ መጽሐፍትን በማንበብ ሃሳቦችን ማደራጀት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪም እያንዳንዱ የአፍሪካ ሀገራት የት እንደሚገኙ ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ ክፍል ገብተው የመማር ማስተማር ሂደትን ከመጀመርዎ በፊት ስለ ቅኝ አገዛዝ በቂ ግንዛቤ ማግኘት አስፈላጊ ነው፡፡ በመጨረሻም ጥራት ያለውና ከትምህርቱ ይዜት ጋር የሚገናኝ የትምህርት ዕቅድ ማዘጋጀትይኖርባቸዋል፡፡

ይህንን ርዕስ ለማስተማር የተሰጠው ክፍለ ጊዜ ብዛት **ሁለት** (2) ስለሆነ በዚህ ክፍለ ጊዜ ውስጥ የተቀመጠውን ይዜት ይዜት በታቀድው መሰረት ማጠናቀቅ አስፈላጊ ነው፡፡ አጫጭር ማስታወሻዎችን ማዘጋዘትም በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴ

ቅድመ ዝግጅት ከተደረገ በኋላ የመማር ማስተማር ዘዴን መምረጥ አሰፈላጊ ነው፡፡ ስለዚህ የተደረገው ቅድመ ጅግጅት ተማሪዎች ዘንድ እንዴት መድረስ እንደሚችል ለይቶ ማወቅ

ወሳኝ ነው፡፡ ይህን ማድረግ ካልተቻለ ተማሪዎች ማግኘት የሚችሉትን የትምህርት ብቃት ከግብ ማድረስ አይቻልም፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች ከአፍሪካ ቅኝ አገዛዝ ጋር ተያያዥነት ባላቸው ጉዳች ላይ አጭር ፅሁፍ እንዲያዘጋጁ ማድረግ አንዱ የመማር ማስተማር ዘዴ ነው፡፡

ተማሪዎች የአውሮፓ ሀገሮች የቅኝ አገዛዝ ስርዓት በአፍሪካውያኖች ላይ ያደረሰውን ጥቅምና ጉዳቶች ላይ እንዲከራከሩ ማድረግና በካርታ ላይ ነፃ የሆኑ ሀጋራትና በቅኝ ግዛት ስር የነበሩትን ሀገራት እንዲያነፃፅሩ ማድረግ አንዱ የመማር ማስተማር ዘዴ ነው፡፡ ይህ ሂደት በአብዛኛው በተማሪዎች መካሄድአለበት፡፡ መምህሩ/ቷም እነዚህን ተማሪዎች መርዳትይኖርበታል/ባታል፡፡

## ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያጎለብቱ ማድረግ

ተማሪዎች በተለያየ መንገድ የፈጠራችሎታቸውን እንዲያጎለብቱ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ተማሪዎችን መልመጃዎችን እንዲሰሩ ማድረግ፣የተነሱትን ካርታዎች የምስራቅ አፍሪካን እንደ ምሳሌ በመውሰድ የራሳቸውን ተሰጥኦ/ፈጠራ በመጨመር ለሌላ ተማሪዎች ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ ማድረግን ይጨምራል፡፡ በውይይትና በሰርቶ ማሳየት ላይ የሚያደርጉትን ተሳትፎ በመከታተል ማበረታታት አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህም ሌላ ሥዕል የመሳልን ጥበብና ክዕሎት እንዲያዳብሩ ማበረታታት አስፈላጊ ነው፡፡ እንዲሁም በግጥም፣ በድራማ እና በመሳሰሉት መግለፅ የሚፈልጉ ተማሪዎችም ካሉ ማበረታታት ወሳኝ ነው፡፡

## ተከታታይ ምዘና

ከካርታ ላይ የፈረንሳይ፣ እንግሊዝ እና ፖርቱጋል ቅኝ ግዛቶችን ተማሪዎች እንዲናገሩ በማድረግ መመዘን ይቻላል፡፡ እንዲሁም በተከናወኑት ክርክር ላይ የተጫወቱትን ሚና በመመልከት፣ በቡድን ስራ ውስጥ ያደረጉትን ተሳትፎ በመመልከት ተከታታይ ምዘና ማካሄድ ይቻላል፡፡ በዚህ መሰረት መምህሩ/ሯበተገኘው ደካማና ጠንካራ ጎን ላይ መረጃዎችን በማደራጀት ግብረ መልስ በመስጠት ተማሪዎችን ማበረታታት አስፈላጊ ነው፡፡

## 5.3. የአፍሪካ ህዝቦች ከነፃነትበኋላ ያጎለበቱት ፖሊቲካዊና ምጣኔ ሀብታዊ ትስስር

**የክፍለ ጊዜ ብዛት…… 3**

ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባቸው የትምህርት ብቃት፤

- የአፍሪካ ህዝቦች ከነፃነት በኋላ ያደረጉት ማህበራዊ፣ የፖሊቲካዊና ምጣኔ ሀብታዊ ትስስር ይረዳሉ
- የአፍሪካ ህዝቦች ከነፃነት በኋላ ያደረጉትን ማህበራዊ፣የፖሊቲካዊና ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ይለያሉ
- የአፍሪካ ህዝቦች ለአፍሪካ ዕድገት ያደረጉትን አስተዋጽ*ዖ* ይገነዘባሉ

### ዋና ዋና ነጥቦች

በ1950ዎቹ ውስጥ ብዙ የአፍሪካ ሀገራት ከአውሮፓውያኖች ቅኝ አገዛዝ ስርዓት ነፃ መውጣት ጀምረዋል፡፡ ለአፍሪካ ሀገሮች ነፃ መውጣት ዋና ዋናምክንያቶች ሁለተኛው የዓለም ጦርነት፣የፓን አፍሪካኒዝም እንቅስቃሴ፣የፖሊቲካ ድርጅቶች መመስረት እና ፖለቲካዊና ምጣኔ ሀብታዊ ሚዛን ለውጦችን መረዳት ዋናዋናዎቹ ናቸው፡፡ የአፍሪካ ሀገሮች ነፃ መውጣት የቻሉት በሁለት መንገድ ነው፡፡ እነሱም መራራ ትግልን በማድረግና በመደራደር ናቸው፡፡አውሮፓውያኖች በብዛት የሚገኙበት አከባቢና መሰረተ ልማት የተሟሉበት አከባቢዎችመራር ትግል አድርገዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በአውሮፓዊያኖች ተነሳሽነት የተለያዩ ድርድሮችን በመፍጠር አፍሪካን ነፃ ለማውጣት ስምምነት ላይ ደርሷል፡፡ በዚህ ዕድል የተጠቀሙ ሀገራት የተወሰኑ ሲሆኑ ከእነሱ ውስጥ አንዷ ጊኒ ናት፡፡

ከ1960ዎች በኋላ የአፍሪካውያኖች ፖለቲካዊና ምጣኔ ሀብታዊ ሁኔታዎች በከፍተኛ ደረጃ መለወጥ ችሏል፡፡ በዚህ መሰረት የምጣኔ ሀብት ጥገኝነት፣ የማህበራዊ ችግሮች፣ መፈንቅለ መንግስት እና የእርስ በእርስ ጦርነት መስፋፋት ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ከአውሮፓውያኖች ተፅዕኖ ነፃ የሆነ ፖለቲካ ባይኖርም ብዙ የአፍሪካ ድርጅቶች ተመስርተዋል፡፡ከእነሱም ውስጥ አንዱ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ አከባቢያዊ ድርጅቶች ናቸው፡፡ ከላይ የተጠቀሱትን በመገምገም ማደራጀት በጣም አስፈላጊ ስለሆነ የተለያዩ መረጃዎችን በማሰባሰብ ማንበብ አስፈላጊ ነው፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

ይህን ንዑስ ርዕስ ለማስተማር አሰፈላጊ የሆነውን ቅድመ ዝግጅት ማድረግነው፡፡ አፍሪካን አህጉር ከነፃነት በፊትናበኋላየሚያሳይ ካርታ በማዘጋጀት ማነፃፀር አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪም ስለ አፍሪካ ከነፃነትበኋላየሚገልጹ ዋቢ መጽሐፍትን በማንበብ መረጃዎችንማደራጀት እና ጥራት ያለው የትምህርት ዕቅድ ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡ይህን ርዕስ ለማስተማር የተሰጠው ክፍለ ጊዜ ብዛት ሶስት(3) ስለሆነ በዚህ ክፍለ ጊዜ ውስጥ የተቀመጠውን የትምህርት ይዜት ማጠናቀቅ አስፈላጊ ነው፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴ

በአፍሪካ ከቅኝ ግዛት በኋላ ያለውን ምጣኔ ሀብታዊና ፖለቲካዊ ለውጦች ለማስተማር የሚረዱ የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን መጠቀም ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ መምህሩ የሚያስተምሩበትን የክፍልና የተማሪዎን ተጨባጭ ሁኔታን በመረዳት ውጤታማ የሆነውን የማስተማር ዘዴ መጠቀም ይኖርባችኋል፡፡ በዚህ መሰረት ተማሪዎችን በተለያዩ ቡድኖች በመክፈል የአፍሪካ ሀገሮች ነፃ ለመውጣት ያደረጉትንትግሎች ላይ እንዲከራከሩ ማድረግ፡፡ በድህነት እና በዕድገት ላይ ድራማ እንዲያዘጋጁ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

ፖለቲካዊና ምጣኔ ሀብታዊ የአፍሪካ ህዝቦች ትስስር ጋር ተያያዠነት ያላቸውን አጫጭር ፅሁፎች እንዲያዘጋጁ ማድረግ አንዱ የመማር ማስተማር ዘዴ ነው፡፡ እንዲሁም የአፍሪካን ካርታ በማንሳት የአፍሪካ ሀገራትን እንዲያሳዩ ማድረግ፡፡ በተጨማሪም የቅኝ ግዛት በአፍሪካኖች ላይ ያመጣውን ችግር በዘገባ መልክ እንዲያቀርቡ ማድረግ ይቻላል፡፡
ከዚህም ሌላ በውይይት፣ ክርክር፣ ገላፃ እና የመሳሰሉትን መጠቀም ይቻላል፡፡ መዘንጋት የሌለበት ነገር ግን ሁሉን ያካተተና ያሳተፈ የመማር ማስተማር ዘዴ መጠቀማችህን ማረጋገጥ ነዉ፡፡

## ተማሪዎች የፈጠራችሎታቸውን እንዲያጎለብቱ ማድረግ

ተማሪዎች በተለያዩ መንገዶች የፈጠራችሎታቸውን እንዲያጎለብቱ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ተማሪዎች መልመጃዎችን እንዲሰሩ ማድረግ፣የተነሱትን ካርታዎች በመውሰድ የራሳቸውን ተሰጥዖ/ፈጠራ በመጨመር ለሌሎች ተማሪዎች ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ ማድረግ፣ በውይይትና ሰርቶ ማሳየት ላይየሚያደርጉትን ተሳትፎ በመከታተል ማበረታታት አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህም ሌላ ሥዕል የመሳልን ጥበብ ማበረታታት፡፡ እንዲሁም በግጥም፣

በድራማ እና በመሳሰሉት መግለፅ የሚፈልጉ ተማሪዎችም ካሉማበረታታት ወሳኝ ነው

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች በቡድናቸው ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ በመመልከት መመዘን ይቻላል፡፡እንዲሁም በተከናወኑት ክርክሮች ላይ የተጫወቱትን ሚና በመመልከት፣ በቡድን ስራ ውስጥ የደረጉትን ተሳትፎ በመከታተል ተከታታይ ምዘና ማድረግ ጥሩ ነው፡፡ በዚህ መሰረት መምህሩ/ሯበተገኘው ደካማና ጠንካራ ጎኖች ላይ መረጃዎችን በማደራጀት ግብረ መልስ በመስጠት ተማሪዎችን ማበረታታት አስፈላጊ ነው፡፡

### 5.1(ሀ) የመልመጃ መልሶች

መምህራን! ተማሪዎች የሰጡትን የተግባር መልስ በመውሰድ የተማሪዎችን ሃሳብ አጎልብቱ

### የመልመጃ መልሶች 5.1(ለ)

1. ፖርቱጋል በኢንዱስትሪ አብዮት ስለምትመራ ቅኝ ተገዥዎችን ባሉበት ለመግዛት ስለፈለገች ነበር፡፡
2. የምዕራብ አፍሪካ አካከበቢ
3. አካላቸው ላይ ጉዳት ማድረስ ለምሳሌ በማቃጠል ጠባሳ መፍጥረና ከአቅም በላይ የሆነ ስራ መስራት እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡
4. ሕፃናትና አረጋዊያንን ያለ አሳዳጊና ጧሪ እንዲቀሩ አድርጓል፡፡ የሰላም አለመረጋጋትና የእርስበርስ ጦርነት፣ ድህነት እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

II. መምህራን ተማሪዎች የሰጡትን የተግባር መልስ በመውሰድ የተማሪዎችን ሃሳብ አጎልብቱ!

### የመልመጃ 5.2መልሶች

1. ፖርቱጋል፣ እስፔን፣ኢንግሊዝ፣ ፈረንሳይ፣ ቤልጅያም፣ ጀርመን እና ጣልያን ናቸው፡፡
2. መምህራን ከላይ የተዘረዘሩትን ሀገራት የቅኝ ግዛት በመለየት አረጋግጡ
3. ለድህነት፣ ለእርስ በእርስ ጦርነት፣ ስደት እና ኋላ ቀርነት ተጋልጠዋል፡፡
4. ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት እንዲከራከሩ አድረግ/ጊ

## የመልመጃ5.3 መልሶች

መምህር ተማሪዎች የሰጡትን የተግባር መልስ በመውሰድ የተማሪዎችን ሃሳብ አጎልብቱ፡፡

## የምዕራፍ አምስት ማጠቃለያ ጥያቄዎች መልሶች

I. **ከዚህ በታች ያሉትን ዓ.ነገሮች ትክክል የሆነውን እውነት ትክክል ያልሆነውን ሐሰት በማለት መልስ/ሺ**

1/ እውነት 2/ ሐሰት3/ እውነት 4/ እውነት 5/እውነት

**II-የምርጫ መልሶች**

1/ ለ 2/ ለ 3/ሀ 4/ ለ 5/ ሀ

**III-የአጭር መልስ ስጥ/ጪ ጥያቄዎች መልስ**

1. ኬንያ፣ ሱዳን፣ ኢንግሊዝ እና ሶማሊያ በኢንግሊዝ ተይዘው ነበር፡፡
2. የድንበር ግጭት፣ የመንግስት ግልበጣ፣ የእስርስ በእርስ ግጭት እና ድህነት
3. አልጄሪያ እና ሞሮኮ በፈረንሳይ ግዛት ተይዞ ነበር፡፡
4. ጅቡቲ
5. 1960ዎች የአፍሪካኖች ዘመን ሊመባል የቻለበት ምክንያት ከ16 የአፍሪካ ሀገሮች በላይ ነፃነታቸውን ያገኙበት ዘመን ስለሆነ ነው፡፡

# ምዕራፍ 6 ዘመናዊው የኢትዮጵያ ታሪክ

**የክፍል ጊዜ ብዛት**............ 12

**ከዚህ ምዕራፍ የሚጠበቁ ውጤቶች፡**

**ይህ ምዕራፍ ከተጠናቀቀ በኋላ ተማሪዎች፣**

- የኢትዮጵያ ዘመናዊዉንመንግስት አመሰራረት ሂደት ያመዛዝናሉ
- በካርታላይየ19ኛውን ክፍለ ዘመን የረጅም ርቀት የንግድ መስመሮችን ያሳያሉ
- ኢትዮጵያ ከውጭ ሀገራት ጋር ያላት የረጅም ጊዜ ግንኙነቶችን ይገልጻሉ
- የኢትዮጵያ ህዝቦች ለሀገራቸው ሉዓላዊነት እና ዳር ድንበር መከበር የተዋደቁበትን ታሪክ በማድነቅ ያከብራሉ፡፡

## 6.1. ዘመናዊዉ የኢትዮጵያመንግስት አመሰራረት

**የክፍል ጊዜ ብዛት**......... 4

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባቸው የትምህርት ብቃት፤**

- ዘመናዊዉ የኢትዮጵያ መንግስት አመሰራረት ሂደት ያመዛዝናሉ
- ዘመናዊ የኢትዮጵያ መንግስት ባህሪያትን ያብራራሉ፡፡

**ዋና ዋና ነጥቦች**

*መምህራን! በመካከለኛው ክፍለ ዘመን በዛሬው ደቡብ ምዕራብ እና በምዕራብ የሀገራችን ክፍሎች የኢትዮጵያ ህዝቦች የየራሳቸው የአስተዳደራዊ መዋቅር እንደነበራቸው መገንዘብ ይገባችኋል። በእነዚህ የሀገራችን ክፍሎች ያሉ ህዝቦች ለዘመናዊዉ መንግስት መመሰረት አስተዋጽኦ ማበርከታቸዉን መገንዘብ ይገባል፡፡ የኢትዮጵያ ዘመናዊው መንግስት ምስረታ የተጀመረው ቀደም ብሎ ቢሆንም እውን እየሆነ የመጣው ግን በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ አከባቢ ነው፡፡*

በዚህም መሰረት ዘመናዊው የኢትዮጵያ መንግስት ምስረታ ጎልቶ መታት የጀመረው ከ1900 ዓም በኋላ ነው፡፡ የኢትዮጵያ የዘመናዊው መንግስት ምስረታ ሂደት መጨረሻ ደረጃ ላይ ባይደርስም የአሁኗ ኢትዮጵያ እንድትመሰረት አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡

ዘመናዊ የኢትዮጵያ መንግስትን ለመመሰረት መንግስታዊ እንቅስቃሴዎች ከ1855 እስከ 1900 መካከል ቢደረጉም ውጤታማ አልሆኑም፡፡ ዘመናዊ የኢትዮጵያ መንግስት ምስረታ ሂደት ያስጀመረው ዳግማዊዉ ቴዋድሮስ ሲሆን የተለያዩ የፖልሲ ማሻሻያዎችና ተሓድሶዎችን አድርጓል፡፡ ይሁን እንጂ ይህንን ትልቅ ዓላማ ከግብ ሊያደርስ አልቻለም፡፡

ከ1868 በኋላ ከንጉስ ቴዎድሮስ ቀጥለው ወደ ስልጣን የመጡ የኢትዮጵያ ነገስታት ዘመናዊ የኢትዮጵያ መንግስት ምስርታ እውን ለማድረግ እንቅስቃሴዎችን ሲያካሄዱ ቆይተዋል፡፡ በዚህ መሰረት ንጉስ ዮሐንስ IVዉ ከ1872-1889 ማህበራዊ፣ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ለውጦችንና ከውጭ ሀገሮች ጋር የነበሩ ግንኙነቶችን በማሻሻል ለዘመናዊዉ መንግስት ምስርታ የበኩሉን አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

በዳግማዊዉ ምኒሊክ ዘመን (1889-1913) ዘመናዊ የኢትዮጵያ መንግስት ምስረታ እንቅስቃሴ ከበፊቱ በተሻለ መልክ ተካሂዷል፡፡ የዳግማዊዉ ምኒሊክ ዘመናዊ የመንግስት ምስረታ እንቅስቃሴ የተካሄድዉም የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ነበር፡፡ በተለይም እምቅ ሀብት ያላቸውን አከባቢዎችን በጉልበት በመቆጣጠር በኢኮኖሚ ዘርፍ አቅሙን በማደራጀት የተካሄደ ስልት ነው፡፡ሌላዉ ደግሞ በማግባባትና በማባበል ነዉ፡፡በመሆኑምዳግማዊዉ ምኒሊክ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም በ1900 አከባቢ ዘመናዊ የኢትዮጵያን መንግስት ምስረታ ቀደም ብለው ከነበሩ ነገስታት በተሻለ መልኩ እንቅስቃሴ አድርጓል፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

መምህራን! ይህንን የትምህርት ይዜት ማስተማር ከመጀመራችሁ በፊት በቂ ዝግጅት ማድረግ ይጠበቅባችኋል፡፡ በዚህም መሰረት ምስራቅ አፍሪካና ኢትዮጵያን የሚሳይ ካርታ ማዘጋጀት፣ የመካከለኛውና ዘመናዊ የኢትዮጵያ መንግስታት ባህሪያትን በአትኩሮት መለየትና ዋቢ መጽሐፍትን በማንበብ በቂ ግንዛቤ ማጎልበት አስፈላጊ ነው፡፡

የመካከለኛውና የዘመናዊዉ የኢትዮጵያ መንግስታት ልዩነታቸውን እና ተመሳሳይነታቸውን በመረጃ በማስደገፍ መለየት ይጠበቅባችኋል፡፡ በተጨማሪም የዘመናዊዉ የኢትዮጵያ መንግስት አመሰራረት ሂደት ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ በመረጃ በማስደገፍ አጭር የግል ማስታወሻ ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው፡፡

በመቀጠልም በውስጡ የመምህራንንና የተማሪዎችን ተግባር ያካተተ ዕለታዊ የትምህረት ዕቅድ ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው፡፡ እንዲሁም በተሰጠው ክፍለ ጊዜ ውስጥ ሊከናወኑ የሚችሉ የተለያዩ ተግባራትን የያዘ ዕቅድ ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው፡፡ እቅዱም ለዚህ የትምህርት ይዜት ከተሰጠው ክፍለ ጊዜ ጋር ተመጣጣኝ መሆኑን ማገናዘብ ያስፈ.ጋል፡፡ በመሆኑም ለዚህ የትምህረት ይዜት የተሰጠው ክፍለ ጊዜ **አራት**(4) መሆኑን ተገንዝባችሁ ከዕቅዳችሁ ጋር ማጣጣም ያስፈልጋችኋል፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴ

የመማር ማስተማር ሂደት የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም እንደሚከናውን አሰቀድሞ ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ ስለዚህ ለትምህረት ይዘቱ ምቹ የሆኑ የተያዩ የመማር ማስተማርዘዴዎችን መጠቀም አስፈላጊ ይሆናል፡፡

ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ በፒራሚድ የአቀማመጥ ገጽታን በመጠቀም ዘመናዊዉ የኢትዮጵያ መንግስት አመሰራረት ታሪክ ላይ ውይይት እንዲያካሂዱ በማድረግ ተማሪዎች በሚያቀረቡት ሃሳብ ላይ ገንቢ የማጠናከሪያ ሐሳብ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም የዘመናዊዉ የኢትዮጵያ መንግስታትን ባህሪያት በማስመልከት ተማሪዎችን በአራት ቡድን በማደራጀት ውይይት ካደረጉ በኋላ ለክፍል ተማሪዎች በዘገባ መልክ እንዲያቀርቡ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

እንዲሁም የአዲሱ ዘመን የኢትዮጵያ መንግስታት መመሰረት ጥቅሙንና ጉዳቱን በሚያግባባቸው አካሄድ ተማሪዎች እንዲከራከሩበት ማድረግ ያስፈላጋል፡፡ ዘመናዊ የኢትዮጵያ መንግስት አመሰራረት ላይ ድርሻ ያላቸው ሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝቦች መሆናቸዉን እንዲረዱ ማድረግ ያስፈላጋል፡፡

ስለዚህ ለተለያዩ የተማሪዎች ግንዛቤ ደረጃ እና ለትምህረት ይዘቱ ምቹ የሆኑ የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን መጠቀም አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ልዩ ትኩረትና ድጋፍ የሚሹ

ተማሪዎች፣በዝግታ የሚማሩና ልዩ ተሰጦ ያላቸውን ተማሪዎች ማዕከል ያደረገ የመማር ማስተማር ዘዴ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

**ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያጎለብቱ ማድረግ**

ልዩ ተሰጥዖላላቸዉን ተማሪዎች ልዩ ትኩረትና ድጋፍ ማድረግ ይገባል፡፡ እንዲሁም በዝግታ የሚማሩ ተማሪዎቸን ለመደገፍ በዕለታዊ ዕቅድ ውስጥ ማካተት ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ ሁሉንም ተማሪዎች ማዕከል ያደረገ የመማር ማስተማር ዘዴ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

የተሰጣቸውን የተግባርና የቡድን ስራ በፍጥነት ሰርተዉ ለሚያቀርቡ ተማሪዎች ተጨማሪ የተግባር ስራ ሰርቶ እንዲያቀርቡ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተለይ ካርታ ማንሳትና የተለያዩ መረጃዎችን ማጠናከር የሚችሉ ተማሪዎቸን መደገፍና ማበረታት አስፈላጊ ነው፡፡

**ተከታታይ ምዘና**

ተማሪዎች በቡድንና በግል ስራ የሚያሳዩትን ተሳትፎ ተከታታይ ምዘናና ግምገማ በማድረግ ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባቸውን ብቃቶችን መጎናጸፋቸዉን መለየት ያስፈልጋል፡፡ ተማሪዎችን በተከታታይ መመዘን የሚያሳዩትን የባህሪይና የግንዛቤ ለውጥና ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባቸውን ብቃቶችን መጨበጣቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም የተለያዩ ተከታታይ የግምገማ ዘዴዎችን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ለምሳሌ፣የቃል ጥያቄ፣በቡድንና በግል ስራ የሚያሳዩትን ተሳትፎ በመገምገም እና የኢትዮጵያ ጎረቤት ሀገሮች መገኛ እንዲለዩ በማድረግ መገምገም አስፈላጊ ነው፡፡ በመጨረሻም ተማሪዎች ያልተረዱትን ነጥቦችን በማቀናጀት ገንቢ ግብረ መልስ መስጠት ተግቢ ስራ ይሆናል፡፡

## 6.2. የረጅም ርቀት የንግድ መስመር

**የክፍለ ጊዜ ብዛት**...... 2

**ተማሪዎችቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባቸው የትምህርት ብቃት**:

- በኢትዮጵያ የነበሩ የረጅም ርቀት ንግድ መስመሮችን ያሳያሉ
- የረጅም ርቀት ንግድ መስመሮች ጥቅሞችን ያመዛዝናሉ

## ዋና ዋና ነጥቦች

በመጀመሪያ የረጅም ርቀት ንግድ መስመሮችን ጥቅሞችና አጀማመራቸውን በጥልቀት መርዳት አስፈላጊ ነው፡፡ በመቀጠልም በንግድ ስርዓት የግዥና ሽያጭ ስራ በተለያዩ የዓለም ሀገሮች መካከል ሲካሄድ እንደቆየ መገንዘብ ያሻል፡፡በንግድ ስርዓት ዉስጥ የግዥና ሽያጭ ስራ በተለያዩና በብዙ አካላት መካከል ሲፈጸም ቆይቷል። ለምሳሌም በአምራቾችና ተጠቃሚዎች መካከል ወይም በነጋዴዎችና በተጠቃሚዎች መካከል ሊካሄድ ይችላል።

እንዲሁም የግዥና ሽያጭ ስራ በአንድ አከባቢ በሚገኙ ሰዎች መካከል ወይም በተለያዩ አከባቢዎች መካከል ሊከናወን ይችላል። በአንድ በተወሰነ አከባቢ በሚገኙ ማህበረሰቦች መካከል የሚካሄደዉ ንግድ የአከባቢ ንግድ ሲባል በተለያዩ አከባቢዎች መካከል የሚካሄደዉ ደግሞ የረጅም ርቀት ንግድ በመባል ይታወቃል።

በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ አከባቢ የረጅም ርቀት የንግድ መስመር በጣም የተስፋፋዉ ከ19ኛዉ መቶ ክ/ዘ በኋላ መሆኑን በጥልቀት ማየት ጥሩ ነዉ ። በዚህን ጊዜም የንግድ ስራ ለመስፋፋቱ የተለያዩ ምክንያቶች አሉት። እነሱም፤

1ኛዉ በቀይ ባህር አከባቢና በሰሜን አፍሪካ ፖለቲካና ሰላም መረጋጋቱ

2ኛዉ በአረቢያ አከባቢና የአፍሪካ ቀንድ አከባቢ የንግድ እቃዎችና የባሪያ ንግድ ፍላጎት መጨመር

3ኛዉ የአዉሮፓ አገራት ቀይ ባህርና የኤደን ባህረ ሰላጤ አከባቢዎችን ለመያዝ ያላቸዉ ፍላጎት ቀስ በቀስ እየጨመረ መምጣቱ ናቸው።

## ቅድመ ዝግጅት

በቅድሚያ በመካከለኛውና በዘመናዊ ዘመን የረጅምርቀት ንግድ መስመሮች የሚያሳይ ካርታ ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው፡፡ እንዲሁም በረጅምርቀት ንግድ ዘመን በብዛት ለግብይት ይዉሉ የነበሩ የንግድ እቃዎችን መለየት ያስፈልጋል፡፡ ነጋዴዎች ከዉጭ አገር የሚያስገቡትንና ወደ ዉጭ የሚሸጡትን የንግድ እቃዎችን ለማመላለስ ባህላዊ የማጓጓዣ ዘዴዎችን ሲጠቀሙ እንደነበሩ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ እነዚህ የንግድ መስመሮችም የተለያዩ አከባቢዎችን በንግዱ ዘርፍም ሆን በማህበራዊዉ በኩል ትስስር እንዲኖራቸዉ አድርጓል።

በረዥም ርቀት ንግድየተለያዩ አከባቢ ህዝቦች እና ነጋዴዎች ግንኙነት ለባህል መወራረስም ምክያት ነበር፡፡ ስለዚህ ይህ የረጅም ርቀት ንግድ የዉጭና የአገር ዉስጥ ንግድን ያከተተ መሆኑን የሚሳይ ካርታ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡

በረዥም ርቀት ንግድ ዘመን የውጭ ሀገር የመገበያያ ገንዘቦች እና የንግድ ዕቃዎችን እንደ ቡናና ወርቅ በስዕል ወይም በቁስ መልክ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡

በመጨረሻም የመምህራንን የስራ ድርሻና በተማሪዎች የሚተገበሩ መልመጃዎችን ያቀፈና ከተሰጠው ጊዜ ጋር የሚጣጣም ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ማዘጋጀት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ውስጥየመማር ማስተማር ዘዴዎች በግልጽ መቀመጥ አለባቸዉ፡፡ ለዚህ ንዑስ ርዕስ የተሰጠው ክፍለ ጊዜም **ሁለት** (2) መሆኑን ተገንዝባችሁ የትምህርት ዕቅድ ዝግጅታችሁን ማደራጀት አስፈላጊ ይሆናል፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴ

የረዥም ርቀት ንግድ ለማስተማር የተያዩ ዘዴዎችን መጠቀም  እንደሚቻል አሰቀድሞ ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ ስለዚህ ለትምህርት ይዘቱ ምቹ የሆኑ የተያዩ የመማር ማስተማርዘዴዎችን መለየት አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ለምሣሌም ተማሪዎችን የመገበያያ ቦታዎችንና ሱቆችን ከመምህራን ጋር በመሆን በአካል በቦታው በመገኘት የግዥና ሽያጭ ስርዓትን እንዲጎበኙ ማድረግ ግንዛቤያቸውን ያዳብራል፡፡ ተማሪዎች ከጉብኝት መልስ በመገበያያ ማዕከላት የተገነዘቡትን በማቀነባበር በዘገባ መልክ ለክፍላቸዉ ማቅረብ ይኖባቸዋል፡፡በተቻለ መጠን የተለያዩ ሀገራት የመገበያያ ብሮችና ሳንቲሞችን ወደ ክፍል በማምጣት ያላቸውን የገንዘብ ዋጋ እንዲያብራሩ ዕድል መስጠት ያስፈልጋል፡፡

የተለያዩ የንግድ ዕቃዎችንና የቁም እንስሳቶችን ጭነው የሚጓዙ የመኪናዎች ስዕል ማዘጋጀትና ለተማሪዎች ማሳየት ጠቃሚ ይሆናል፡፡ በመካከለኛውና በዘመናዊዉ የታሪክ ዘመን የረጅም ርቀት ንግድ መስመሮች የሚያሳይ ካርታ በማዘጋጀት እንዲያብራሩ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በመማር ማስተማር ሂደቱ ልዩ ትኩረት እና ድጋፍ የሚሹ ተማሪዎችን፣በዝግታ የሚማሩ እና ልዩ ተሰጥዖ ያላቸው ተማሪዎቸን ማዕከል ያደረገ የመማር ማስተማር ዘዴ መጠቀም ወሳኝ አካሄድ ነዉ፡፡

## ተማሪዎች የፈጠራችሎታቸውን እንዲያጎለብቱ ማድረግ

ልዩ ተሰጦ ያላቸው ተማሪዎችንና ልዩ ትኩረትና ድጋፍ የሚሹ ተማሪዎችን ለማበረታታትና ለመደገፍ የሚረዳ ስልት በዕለታዊ ዕቅድ ውስጥ ማካተት ያስፈልጋል፡፡ ሁሉን አቀፍ የሆነ የመማር ማስተማር ዘዴ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ የተሰጣቸውን የተግባር እና የቡድን ስራ በአግባቡ ሰርቶ ለሚያቀርቡ ተማሪዎች ተጨማሪ የተግባር ስራ ሰርቶ እንዲያቀርቡ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተለይ ካርታ እና የተለያዩ መረጃዎችን በማጠናከር የረጅም ርቀት ንግድ ጥቅም እና ጉዳት ማገናዘብ  የሚችሉ ተማሪዎችን መደገፍና ማበረታት አስፈላጊ ነው፡፡

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች በቡድን እና በግል ስራ የሚያሳዩትን ተሳትፎ በተከታታይ ግምገማ ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባቸውን ብቃቶችን መጎናጸፋቸዉን መለየት ያስፈልጋል፡፡ ተማሪዎች በተከታታይ ግምገማ የሚያሳዩትን የባህሪና የግንዛቤ ለውጥ በመከታተል ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባቸውን ብቃቶችን መጨበጣቸውን  ማረጋገጥ ወሳኝ ነዉ፡፡
ስለዚህ የተለያዩ ተከታታይ ግምገማ ዘዴዎችን በመጠቀም የተማሪዎችን ምዘና ማካሄድ ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ የቃል ጥያቄ፣በቡድንና በግል  ስራ የሚያሳዩትን ተሳትፎ በመገምገምና በመጨረሻም ተማሪዎች ያልተረዱትን ነጥቦችን በማቀናጀት ገንቢ ግብረ መልስ መስጠት ተግቢ ስራ ይሆናል፡፡

# 6.3. ዘመናዊዉ የኢትዮጵያ መንግስት ከዉጭ ሀገራት ጋር ያለው ግንኙነት

**የክፍለ ጊዜ ብዛት**…………… 3

**ተማሪዎች ቢያንስ  ሊኖራቸው የሚገባቸው የትምህርት ብቃት**:

- በዘመናዊዉ የኢትዮጵያ መንግስትና በዉጭ ሀገራት መካከል  የነበረውን ግንኙነቶችን ያገናዘባሉ
- ከዉጭ ሀገራት ጋር በተለያዩ ዘርፎች  ግንኙነት መፍጠሩ ያለውን አስተዋጽኦ ይገመግማሉ፡፡

## ዋና ዋና ነጥቦች

ዘመናዊዉ የኢትዮጵያ መንግስት ከዉጭ ሀገራት ጋር በተለያዩ ዘርፎች ለዘመናትየነበረውን የግንኙነቶች ዓይነትና የግንኙነቶቹ ጥቅሞችን መረዳት አስፈላጊ ነው፡፡ በዘመናዊዉ የኢትዮጵያ መንግሥታት ታሪክ ዉስጥ ንጉሳን ከዉጭ ሀገራት ጋር ብዙ የስምምነት ዉሎችን ሲፈራረሙ ቆይተዋል። በዚህም መሰረትዳግማዊዉ ቴዎድሮስ በመጀመሪያ ከእንግሊዝ ሀገር ጋር ጥሩ የሚባል ግንኑነት ነበረዉ። በኋላ ግን በ1868 ዓ.ም ጄኔራል ናፒየር በዳግማዊዉ ቴዎድሮስ ላይ ሊዘምት ችሏል። እንደዚሁም ዮሐንስ IVዉም በመጀመሪያ ላይ እንደ ግብጽና ሱዳን ካሉት ሀገራት ጋር ጥሩ የሆነ ግንኙነት ነበረዉ። ይህ የዮሐንስ IVዉ ጥሩ ግንኙነት ግን በኋላ ላይ ወደ ጠላትነት በመቀየር ወደ ዉጊያ ሊገባ ችሏል። በዚህም የተነሳ በ1889 ዓም ዮሐንስ IVዉ ከሱዳኖች ጋር በመተማ ጦርሜዳ ሲዋጋ ህይዎቱ ሊያልፍ ችሏል።

ከ1870ዎቹ ጀምሮ ደግሞ ምኒሊክ ዳግማዊዉ ከጣሊያን፣ ፈረንሳይና እንግሊዝ ጋር የንግድ ስምምነት ግንኙነት መስርቶ ነበር።ይሁን እንጂ ኢትዮጵያና እነዚህ ስምምነት የተፈራረሙ ኃይሎች ፍላጎታቸዉ ሳይሟላ ሲቀር ወደ ግጭትና ጠላትነት ሲቀየር ቆይቷል። ለምሳሌም የዉጫሌዉ ስምምነት በ1889 ዓ.ም በጣልያንና በኢትዮጵያ መካከል የተፈረመዉ ዉል በኋላ ላይ ወደ ጠላትነት በመቀየሩ ግጭትና ጦርነት አስነስቷል።

በአጠቃላይም በዘመናዊ ታሪክ ዉስጥ ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከብዙ የዉጭ ሀገራት ጋር ጥሩ የሆነ ግንኙነት ነበራት። ለምሳሌም በ1923 እአአ የዓለም መንግሥታት ሊግ አባል በመሆን በዓለም ላይ ዕዉቅና አግኝታለች። እንዲሁም በ1945 እአአ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት (UNO) አባል በመሆን ትታወቃለች። በተጨማሪ የዓለም አቀፍ የሰዉ ልጅ መብት አዋጅ (UDHR፣1948) በመቀበል ከአለም ሀገራት ጋር ያላትን ግንኙነት ማጠናከር የቻለች ሀገርናት።

## ቅድመ ዝግጀት

በመካከለኛውና በዘመናዊ የኢትጵያ ታሪክ ዘመን በተለያዩ ዘርፎች ከውጭ ሀገራት ጋር ግንኙነቶች መኖራቸውን የሚያሳይ ካርታ ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው፡፡ እንዲሁም ከውጭ ሀገራት ጋር የተፈራረሙትን ስምምነቶችን መለየት ያስፈልጋል፡፡ በተለያዩ ስምምነቶች ላይ

የዉጭ ሀገራትና የኢትዮጵያን ፍላጎት ለይቶ ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ የተለያዩ አከባቢዎች በንግድና በፖለትካ ዘርፍ ጥሩ ግንኙነት እንደ ነበራቸዉም ማስተዋል አስፈላጊ ነዉ፡፡ በአጠቃላይም በዘመናዊዉ ኢትዮጵያ ታሪክ ዉስጥ ኢትዮጵያ በአለም አቀፍ ደረጃ ከብዙ የዉጭ ሀገራት ጋር ጥሩ የሆነ ግንኙነትእንደ ነበራት በዝርዝርመረዳት ጥሩ ነዉ።

በመጨረሻም የመምህሩን የስራ ድርሻና የተማሪዎችን ተግባር በግልጽ የሚያሳይ ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ በዕለታዊ የትምህርት ዕቅዱ ውስጥ የሚካተቱ የመማር ማስተማር ዘዴዎች ከተሰጠው ክፍለ ጊዜ ጋር መዛመድ አለባቸዉ፡፡ በመሆኑም ለዚህ ንዑስ ርዕስ የተሰጠው ክፍለ ጊዜ **ሶስት** (3) መሆኑን ተገንዝባችሁ የትምህርት ዕቅድ ዝግጅታችሁን ማቀናጀት አስፈላጊ ይሆናል፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴ

ኢትዮጵያ በዘመናዊዉ የታሪክ ጊዜያት ከተለያዩ የውጭ ሀገራት ጋር ግንኙነት መኖሯን ለማስተማር የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም እንደሚቻል አሰቀድሞ ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ ስለዚህ ለትምህረት ይዘቱ ምቹ የሆኑ የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን መለየት አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በዚህ መሰረትም ተማሪዎችን በዘመናዊ ታሪክ ዉስጥ ከኢትዮጵያ ጋር ግንኙነት የነበራቸውን የውጭ ሀገራት በመዘርዘር የግንኙነት አይነቶችንም በማቀነባበር ማቅረብ ተመራጭ ነዉ፡፡

ተማሪዎች የተለያዩ መረጃዎችን በማጠናከር ኢትዮጵያ ከውጭ ሀገራት ጋር የነበራትን ግንኙነቶች ጥቅምና ጉዳት ላይ በቡድን ተከፋፍለው ክርክር ካደረጉ በኋላ በዘገባ መልክ ለክፍላቸዉ ማቅረብ ይኖባቸዋል፡፡ ከውጭ ሀገራት ጋር የነበሩትን ጥሩ ጥሩ ግንኙነቶችን የሚያደፈርሱ ነገሮች ላይ ተማሪዎች ሁለትና ከዛ በላይ ቡድን በማደራጀት ክርክር እንዲያካሂዱ ማደረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ከክርክሩ የተገነዘቡትን ለክፍላቸዉ እንዲያቀርቡ ማድረግም የተሻለ የማስተማር ዘዴ ነዉ፡፡ በመማር ማስተማር ሂደት ዉስጥልዩ ትኩረትና ድጋፍ የሚሹ ተማሪዎችና በዝግታ የሚማሩ ተማሪዎቸን ማዕከል ያደረገ ሁሉን አቀፍ የመማር ማስተማር ዘዴ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

## ተማሪዎች የፈጠራችሎታቸውን እንዲያጎለብቱ ማድረግ

ልዩ ተሰጥዖ ያላቸው ተማሪዎችን ለመደገፍ በዕለታዊ ዕቅድ ውስጥ ማካተት ያስፈልጋል፡፡ ሁሉንም ማዕከል ያደረገ የመማር ማስተማር ዘዴ መጠቀም እንደሚስፈልግ ከላይ የተብራራ ሲሆን ልዩ ተሰጥዖ ያላቸውን ተማሪዎች ለመርዳት ለየት ያለ አካሄድ መጠቀም ያሻል፡፡ በመሆኑም በክፍል ዉስጥ የተሰጣቸውን ተግባርና የቡድን ስራ በአግባቡ ሰርቶ ለሚያቀርቡ ተማሪዎች ተጨማሪ መልመጃ በመስጠት ሰርተዉ እንዲያቀርቡ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተለይ ካርታና የተለያዩ መረጃዎችን በማጠናከር ኢትዮጵያ ከውጭ ሀገራት ጋር የነበራትን ግንኙነቶችን ለየት ባለ መልኩ ማስረዳት የቻሉትን ማበረታታት  አስፈላጊ ነው፡፡

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች በቡድን እና በግል ስራ የሚያሳዩትን ተሳትፎ በተከታታይ በመመዝገብ ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባቸውን ብቃቶችን መጎናጸፋቸዉንመለየት ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች በተከታታይ ግምገማ የሚያሳዩትን የባህሪይና የግንዛቤ ለውጥ መረዳት ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባቸውን ብቃቶችን መጨበጣቸውን  ለማወቅ የረዳል፡፡

ስለዚህ የተለያዩ የተከታታይ ምዘናና ግምገማ ዘዴዎችን በመጠቀም የተማሪዎችን የብቃት ደረጃ ለመለየት የረዳል፡፡ በመሆኑም የቃል ጥያቄን በመጠቀም፣በቡድንና በግል  ስራ ላይ የሚያሳዩትን ተሳትፎ በመገምገምና በመለየት በመጨረሻም ተማሪዎች ያልተረዱትን ነጥቦች በማቀናጀት ገንቢ ግብረ መልስ መስጠት ተግቢ ይሆናል፡፡

## *6.4. የኢትዮጵያ ህዝቦች በአንድነት ዳር ድንበርና ሉዓላዊነትን ለማስከበር ያደረጉት ትግል*

**የክፍል ጊዜ ብዛት...... 3**

**ተማሪዎችቢያንስ ሊኖራቸውየሚገባቸውየትምህርትብቃት:**

- የኢትዮጵያ ህዝቦች ሀገራቸዉን ከዉጭ ወራሪዎች ለመከላከል ያደረጉትን ተጋድሎ ያደንቃሉ
- የኢትዮጵያ ህዝቦች ኢትዮጵያን ከዉጭ ሀገራት ወረራ ለመከላከል ያደረጉትን የትግል ውጤት ያጠናክራሉ
- የሀገር ግንባታ ስራዎችን በመረዳት የበኩላቸውን ድርሻ ይወጣሉ

### ዋና ዋና ነጥቦች

የኢትዮጵያ ህዝቦች በጋራ በመሆን የሀገራቸዉን ሉዓላዊነት በማስክበር እንደሚታወቁ በጥልቀት መረዳት ያስፈልጋል። በመሆኑም በተለያዩ ጊዜያት በዉጭ ወራሪዎች ሲደረግ የነበረዉን የሀገሪቱን ሉዓላዊነት ለመድፈር የተደረጉትን ሙከራዎች ለማክሸፍ በጋራ እርምጃ እየወሰዱባቸዉ ዛሬ ደርሰዋል።

በዚሁም መሰረት ኢዮጵያኖች በዚህ በኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ ዉስጥ ትላልቅ ጦርነቶችን አካሂደዋል። እነዚህም የግብጽ ወረራ(1875-1884)፣ የመሐዲስቶች ወረራ (1882-1889)፣ የጣሊያኖች ወረራ (1885-1896 እና 1935-1941) እና የሶማሊያ መንግሥት ወረራዎች (1977-1978) እና የመሳሰሉት ናቸዉ። ይሁን እንጂ ሁሉም ወራሪዎች ተሳክቶላቸዉ ኢትዮጵያን መያዝ የቻሉ የሉም። ይህም ሊሆን የቻለበት ምክንያት የኢትዮጵያ ህዝቦች፣ ብሔሮችና ብሔረሰቦች በአንድነት በመታገላቸው ነው፡፡

እንደሚታወቀዉ የጣልያን መንግሥት በዮሐንስIV ዘመነ መንግሥት ዉስጥ በምጽዋ አከባቢ ሲስፋፋ ቆይቷል። በተለይም ከ1885 ዓ ም በኋል ከምጽዋ በመነሳት ወደ ኤሪቲራ ተስፋፍቷል። በዚሁም መሰረት ከምጽዋ ወደ አይሌት፣ ዊአ፣ ሰአቲ፣ ዶጋሊና አስመራ በቅደም ተከተል ሊስፋፋ ችሏል።በዚህን ጊዜም ከምኒሊክ IIዉ ጋር ጣልያኖች የነበራቸዉ ግንኙነት መልካም ነበር። በመሆኑም ይህ መልካም ግንኙነትም በማደጉ የዉጫሌን ስምምንት እስከ መፈራረም ደርሰዋል።

በሱዳንና በኢትዮጵያ መካከል የነበረዉ መልካም ግንኙነት መሻከር የጀመረዉ ከ19ኛዉ ክ/ዘ አጋማሽ ጀምሮ ነዉ። በ1880ዎቹ አከባቢ እስከ ነጆ( ወለጋ) በመዝለቅ ወረራ በመፈጸም በጉቴ ዲሊ ጦር ሜዳ ላይ ተሸንፈዋል። ይሁን እንጂ በሱዳንና በኢትዮጵያ መካከል ያለዉ አለመግባባት ወደ ከፍተኛ ግጭት የተሸጋገረዉ ከሒዌት(1884) ስምምነት በኋላ ነበር።

በዚሁም መሰረት ዮሐንስ IVዉ የጦር ኃይሉን ወደ ሱዳን በመላክ በኩፊት (1885) ጦርሜዳ ከሱዳኖች ጋር ተዋግቷል። በዚህም ጦር ሜዳ ኢትዮጵያኖች በማሸነፍ የእንግሊዝን ጦር ኃይል ከሱዳኖች አስለቅቀዉ በምጽዋ በኩል በሰላም ሸኝተዋቸዋል። በመሆኑም ሱዳኖች ቁጭትና ንዴት ዉስጥ እንዲገቡና ለብቀላ እንዲዘጋጁ አድርጓቸዋል።

በኢትዮጵያ መንግሥትና በሶማሊያ መንግሥት መካከል አበይት ግጭቶች የነበሩት በንጉሥ ኃይለስላሴ ቀዳማዊዉና በመንግሥቱ ኃይለማሪያም ዘመናት ነበር። ጉልህ የሆነዉ የግጭቶቹ ምክንያትም የሶማሊያ መንግሥት ግዛት የማስፋፋት ፍላጎት ማየል ነዉ። ይህ በኃይለስላሴ ቀዳማዊዉ የጀመረዉ ግጭትም እስከ ደርግ ዘመን መጨረሻ አከባቢ ሊዘልቅ ችሏል።

## ቅድመ ዝግጅት

በመካከለኛው እና በዘመናዊ ዘመን በተለያዩ ዘርፎች ከውጭ ሀገራት ጋር ግንኙነት መኖራቸውን የሚያሳይ ካርታ ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው ፡፡እንዲሁም ከውጭ ሀገራት ጋር የተፈራረሙትን ስምምነቶችን መለየት ያስፈልጋል፡፡ በተለያዩ ስምምነቶች የዉጭ አገራት እና የኢትዮጵያ ፍላጎት ለይቶ ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ የተለያዩ ጎረቤት ሀገራት ለመን ኢትዮጵያን መዉረር እንደሚፈልጉና ፖለቲካዊና ኢኮኖሚዊ ፈላጎታቸዉን በጥልቀት መመርምር ያስፈልጋል፡፡ በአጠቃላይም ዘመናዊ ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከብዙ የዉጭ ሀገራት ጋር ጥሩም ሆነ መጥፎ ግንኙነቶችን ሰታካሂድ ነበር።
እንደሚታወቀዉ የጣልያን መንግሥት በዮሐንስIV ዘመነ መንግሥት ዉስጥ በምጽዋ አከባቢ ሲስፋፋ ቆይቷል። በተለይም ከ1885 ዓ ም በኋል ከምጽዋ በመነሳት ወደ ኤሪቲራ ተስፋፍቷል።

በሱዳንና በኢትዮጵያ መካከል የነበረዉ መልካም ግንኙነት መሻከር የጀመረዉ ከ19ኛዉ ክ/ዘ አጋማሽ ጀምሮ መሆኑንና መከንቱንም ጭምር ማወቅ አስፈላጊ ነው።

በመጨረሻም ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ማዘጋጀት በጣም አስፈላጊ ተግባር ነዉ፡፡ በዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ውስጥ የሚካተቱ የመማር ማስተማር ሂደቶች ከተሰጠው ክፍለ ጊዜ ጋር መዛመድ አለባቸዉ፡፡ በዚህ መሰረትም ለዚህ ንዑስ ርዕስ የተሰጠው ክፍለ ጊዜ ሶስት (3) መሆኑን ተገንዝባችሁ የትምህርት ዕቅድ ዝግጅታችሁን ማደራጀት አስፈላጊ ይሆናል፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴ

ኢትዮጵያ በዘመናዊ መንግስት ዘመን ከተለያዩ ውጭ ሀገራት ጋር ግንኙነት መመስረቷን ሊገልጹ የሚችሉ የማስተማር ዘዴዎችን መጠቀም እንደሚቻል አሰቀድሞ ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ ስለዚህ ለትምህርት ይዘቱ ምቹ የሆኑ የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን ለምሳሌ የጦርነት ቪድዩዎችን ማሳየት፣ታሪካዊ ስዕሎችንና ፖስተሮችን መጠቀም የተሻለ ነዉ፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች የተለያዩ መረጃዎችን በማሰባሰብ ኢትዮጵያ ከውጭ ሀገራት ጋር የነበራትን አለመግባባትና ገጭቶች በዘገባ መልክ ለክፍላቸዉ እንያቀርቡ ማድረግ ይቻላል፡፡ ኢትዮጵያ ከውጭ ሀገራት ጋር ያካሄደችዉ ጦርነቶች ጥቅምና ጉዳት በተመለከተ ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት ክርክር እንዲያካሂዱ ማደረግ አስፈላጊ ነው፡፡

በመማር ማስተማር ሂደት ዉስጥ ልዩ ትኩረትና ድጋፍ የሚሹ ተማሪዎችና በዝግታ የሚማሩ ተማሪዎቸን ማዕከል ያደረገ የመማር ማስተማር ዘዴ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

## ተማሪዎች የፈጠራችሎታቸውን እንዲያጎለብቱ ማድረግ

ልዩ ተሰጠ ያላቸው ተማሪዎቸን መደገፍና ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡ ሁሉንም ማዕከል ያደረገ የመማር ማስተማር ዘዴ ከመጠቀም ጎን ለጎን እንኚህነ ተማሪዎች ለማበረታታት የሚረዳ ዘዴን መተግበር ያስፈልጋል፡፡ በዚህ መሰረት በክፍል ዉስጥ የተሰጣቸውን ተግባር ቀድመዉ ያጠናቀቁ ተማሪዎችን ተጨማሪ መልመጃ ወይም ስራ በመስጠት ሰርተዉ እንዲያቀርቡ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተለይ ሙያንና ክህሎትን ሊያዳብር የሚችል ተገባር በመስጠት ማለማመድ ያሻል ካርታ እና የተለያዩ መራጃዎ፡፡

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች በቡድንና በግል የሚያሳዩትን ተሳትፎ በተከታታይ በመመዝገብ መመዘን ይቻላል፡፡ በክፍል ዉስትና በዉጭ የሚሰጡትን መልመጃዎችና የቡድን ተግባራት

በማየትና በመከታተል ተማሪዎችን በችሎታቸዉ መለት ይቻላል፡፡ እንዲሁም የቃል ጥያቄ በመጠቀም ፣በቡድንና በግል ስራ የሚያሳዩትን ተሳትፎ በመከታተል መገምገም የቻላል፡፡ በዚህም አካሄድ በመጠቀም ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባቸውን ብቃቶችን መጎናጸፋቸዉን መመዘን የቻላል፡፡ በዚህ መሰረት ተማሪዎች በተከታታይ ግምገማ የሚያሳዩትን የባህሪና የግንዛቤ ለውጦችን በመለየት ቢያንስ ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባቸውን ብቃቶችን መጨበጣቸውን መለካት ያስፈልጋል፡፡ በመጨረሻም ተማሪዎች ያልተረዱትን ነጥቦችን በማቀናጀት ገንቢ ግብረ መልስ መስጠት ተግቢ ስራ ይሆናል፡፡

## የመልመጃ 6.1.ጥያቄዎች መልስ

1. የሚፈልገውን ጦር መሳሪዎች ማግኘት አለመቻሉና በውጭ ሀገር ዜጎች ላይ እርምጃ መውሰድ ናቸው፡፡
2. በወታደራዊ ኃይል በመታገዝና በአንዳንድ የመደለያ ዘዴዎች በመጠቀም ነበረ፡፡
3. ዳግማዊዉ ቴዎድሮስ፣ አጼ ዮሐንስIV እና ዳግማዊዉ ምኒሊክ ናቸው፡፡
4. ግብጽ፣ ጣልያን እና ሱዳን ናቸው፡፡
5. ሶስት ጊዜ ነው፡፡ ዋና ዓላማቸው የአባይ ወንዝን ለመቆጣጠር ነበረ፡፡
6. ጣልያን፣ፈረንሳይ እና እንግሊዝ ናቸው፡፡
7. የተለያዩ የማጓጓዣ ዘዴዎች መስፋፋትና በተክኖሎጂ በመታገስ የአለም ህዝቦች ግንኙነት ማደግ ፡፡

## የመልመጃ 6.2.ጥያቀዎች መልሶች

1. የዝሆን ጥርስ፣የእንስሳት ቆዳ፣ የቁም እንስሳት እና እጣን ናቸው፡፡
2. የባርያ ጉልበትና ለሎች ዕቃዎች ፍላጎት በአፍርካ ቀንድ አከባቢና በዐረቢያ በጣም ስለጨመረ የአውሮፓ ሀገሮች ቀይ ባህር እና የኤደን ባህረ ሰላጤ አከባቢን ለመቆጣጠር ከፍተኛ ፍላጎት ነበራቸው፡፡
3. የመንገደኞች ደህንነት ለመጠበቅ
4. መምህር/ት! ተማሪዎች በካርታ ስራ ዙሪያ ግንዛቤ እንዲኖራቸው በቂ ማብራሪያ ማድረግ እና ተማሪዎች የሰሩትን ማረጋገጥ አስፈላጊ ይሆናል፡፡
5. ቦንጋ፣አሳንዳቦ እና ሰቃ ናቸው፡፡

6. በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የተፈጥሮ የንግድ ዕቃዎች በከፍተኛ ክምችት ስለሚገኙ ነው፡፡

## የመልመጃ 6.3.ጥያቀዎች መልሶች

**I. የእውነት /ሐሴት ጥያቀዎች መልሶች**

1/ **እውነት** 2/**ሐሴት**3/ **እውነት** 4./ **እውነት** 5/**ሐሴት**

**II. የምርጫ ጥያቀዎች መልሶች**

1/ መ 2/ ሐ

## የምዕራፍ 6 ማጠቃለያ መልመጃ ጥያቀዎች መልሶች

**I. የእውነት /ሐሰት ጥያቀዎች መልሶች**

1/እውነት 2/እውነት3/እውነት 4/ እውነት 5.ሐሰት

**II. የምርጫ ጥያቀዎች መልሶች**

1/ ሐ 2/ ሐ 3/ ሀ 4/ ለ

**III.የቅደም ተከተል ጥያቀዎች መልሶች**

| |
|---|
| 1. ጉንደት ( ከግብጽ ጋር) |
| 2. ጉራ ( ከግብጽ ጋር) |
| 3. አድዋ (ከጣልያን ጋር) |
| 4. ካራ-ማራ( ከሶማልያ ጋር) |
| 5. ዶጋሊ (ከጣልያን ጋር)ናቸዉ፡፡ |

# ምዕራፍ ሰባት፡ ትኩረት የሚሹ ዋና ዋና የአለም ጉዳዮች

**ለዚህ ምዕራፍ የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት** ................................12

## የምዕራፉ የመማር ውጤቶች

## ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፤

- የከባቢ አየር መለወጥ በሰዉና በአከባቢ ላይ የሚያመጣዉን ተፅዕኖን ያመዛዝናሉ።
- የተፈጥሮ ሀብትን ለማንከባከብ የሚያገለግሉ አገር በቀል እዉቀት ይለያሉ።
- በተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ ላይ የሚሰሩ ተቋማትን ያደንቃሉ።
- የከባቢ አየር መበከልና የሚያመጣዉን ተፅዕኖ ይገልፃሉ።
- ለውሃ እጥረት ምክንያት የሚሆኑ ነገሮችን ይገልፃሉ።
- በደን መመንጠር ምክንያት የሚፈጠሩ ችግሮችን ይለያሉ።
- ሰዎች በግልና በጋራ ለአከባቢ ጥበቃና እንክብካቤ የሚያደርጉትን ተሳትፎ ያደንቃሉ።

## 7.1. በአሁኑ ጊዜ ትኩረት የሚሹ ዋና ዋና የአለም ጉዳዮች

### ዋና ዋና ነጥቦች

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ተማሪዎች በትኩረት ልማሩ የሚገባቸዉ በአለም ላይ ትኩረት የሚፈልጉ ጉዳዮች ምን ምን እንደሆኑ፤የአየር ንብረት መቀየር፤ ለአየር ንብረት መቀየር ምክንያት የሆኑ ነገሮችና የሚመጡ ችግሮች፤ የውሃ እጥረትና የደን መጥፋት የሚሉትን ይማራሉ።

### 7.1.1. የአየር ንብረት መቀየር

ለዚህ ርዕስ የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት.......................................... .........1

ተማሪዎች ቢያንስ ሊደርሱበት የሚገባ  የመማር ብቃት

ከዚህ  ርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡

- የአየር ንብረት መቀየርና ምንነት ይገልፃሉ።
- የአየር ንብረትና የአየር ሁኔታን ልዩነት ይዘረዝራሉ።
- የአየር ንብረትና የአየር ሁኔት ይዘቶችን ያደንቃሉ።

## ቅድመ ዝግጅት

የዚህን ርዕስ ትምህርት ማስተማር ከመጀመርዎ በፊት ይህንን ርዕስ ለማስተማር የሚያግዙ የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች እንደ የአየር ንብረትን የሚያሳይ ካርታ በማዘጋጀት ማስተማር ይቻላል። በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ያለዉን ፅሑፍና ሌሎች የተለያዩ መፅሐፎችን በማንበብ በቂ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል።

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

ይህንን ርዕስ ለማስተማር ተማሪዎችን ማዕከል ያደረጉ የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን እንደ ገለፃ፤ ጥያቄና መልስ እንዲሁም የቡድን ውይይት በመጠቀም ማስተማር ይቻላል። ተማሪዎች የአየር ንብረት መቀየር ማለት ምን እነደሆነ ከሚያዉቁት ተነስተዉ እንድናገሩ ለማድረግ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት መጠየቅ ያስፈልጋል። በተጨማሪም ሌሎች የተለያዩ ምንጮችን በማንበብና ያገኙትን እዉቀት መሰረት በማድረግ የትምህርቱን ማጠቃለያ መስጠት አስፈላጊ ነዉ።

## ልዩ ተሠጥዖ እና ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

ልዩ ችሎታ እና ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማበረታታት አስፈላጊ ነው። በውይይት ወቅት በሌሎች ተማሪዎች ላይ ተፅዕኖ እንዳያደርሱ ክትትል ማድረግ ነዉ። በክፍል ውስጥ ያሉ በትምህርት አቀባበላቸው ፈጣን ያልሆኑ እና ሴት ተማሪዎችን ደግሞ ተጨማሪ ሥራን እንዲሰሩ ማድረግና ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ።

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ ለማወቅ ተከታታይነት ያለው ክትትል ማድረግ አስፈላጊ ነው። የተማሪዎችን ችሎታ በመለየት የሚያስፈልጋቸውን እገዛ ማድረግ አስፈላጊ ነው።ለምሳሌ የተለያዩ ጥያቄዎች፤ የአየረ ንብረትና የአየር ሁኔታ ልዩነት ምንድናቸዉ? የአየረ ንብረትና የአየር ሁኔታን የሚቆታጠሩ ይዘቶች ምን ምን ናቸዉ ? የሚሉትን በመጠየቅ ግንዛቤያቸዉን መሻሻል ይገባል። ሁሉም ተማሪዎች የሚጠበቅባቸው

የመማር ብቃት ላይ መድረስ አለባቸዉ። ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ማግኘት ያልቻሉትን የተለየ እገዛ በማድረግና በእረፍት ጊዜያቸዉ የሚሰሩትን ሥራዎች በመስጠት ግንዛቤያቸዉን እንድያሻሽሉ ማድረግ ያስፈልጋል።

## የመልመጃ 7.1. ጥያቄዎች መልስ

1. የአየር ሁኔታ ማለት በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚቀያየሩ የከባቢ አየር ይዘቶች እንደ ሙቀት፤ ቅዝቃዜ፤ ንፋስ፤ ዝናብና የመሳሰሉት ናቸው። የእነዚህ ይዘቶች መቀያየር ደግሞ በቀናት፤ በሣምንታት፤ በወራትና በዓመታት ውስጥ የሚከናወን ይሆናል።

2. የአየር ንብረትና የአየር ሁኔታ ይዘቶች ተመሳሳይ ሲሆኑ እነሱም እንደ ሙቀት፤ ዝናብ፤ ትነት፤የአየር ግፊት፤ ንፋስ፤ ፀሐይና የመሳሰሉት ናቸዉ።

3. የአየር ንብረት ማለት የአየር ሁኔታ አማካይ ነው።የአየር ንብረት የሚታወቀዉ የአንድ አከባቢ አየር ሳይቀየር ለረጅም ጊዜ ቢያንስ ለ35 ዓመትና ከዚያ በላይ ጊዜ የሚቆይ ነው።

4. የአየር ንብረትና የአየር ሁኔታ ልዩነት የቆይታ ግዜያቸዉ ብቻ ነዉ። የአየር ሁኔታ እስከ አንድ ዓመት ሲሆን የአየር ንብረት ደግሞ ከ35 ዓመትና ከዚያ በላይ ነው።

## 7.1.2. የአየር ንብረት መቀየር ፅንሰ ሀሳብ

**ለዚህ ርዕስ የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት**……………………………….……… ………1

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊደርሱበት የሚገባ የመማር ብቃት**

ከዚህ ርዕስትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡

- የአየር ንብረት መቀየር ምንነት ይገልፃሉ።
- የአየር ንብረት መቀየር በአለም ወይም በአንድ አከባቢ ሊሆን እንደሚችል ይገነዘባሉ።

# ቅድመ ዝግጅት

የዚህን ርዕስ ትምህርት ማስተማር ከመጀመርዎ በፊት ይህንን ርዕስ ለማስተማር የሚያግዙ የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ፤አየር ንብረትን የሚያሳይ ካርታና የአየር ንብረት መቀየርን የሚያሣይ ስዕልን በማዘጋጀትና ለትምህርቱ ሊያግዙ የሚችሉ መፅሐፍትን በማንበብ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል።

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

ይህንን ርዕስ ለማስተማር ተማሪዎችን ማዕከል ያደረገ የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን እንደ ገለፃ፤ ጥያቄና መልስ እንድሁም የቡድን ውይይት በመጠቀም ማስተማር ይቻላል። ይሁን እንጂ ለዚህ ርዕስ ይበልጥ የሚስማማና ተማሪዎችን የሚያነቃቃ የማስተማር ዘዴን መጠቀም አስፈላጊ ነዉ። ተማሪዎች ከሚያዉቁት ተነስተዉ እንድናገሩ ለማድረግ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት መጠየቅ ያስፈልጋል። በተጨማሪም ሌሎች የተለያዩ ምንጮችን በማንበብና ያገኙትን እዉቀት መሰረት በማድረግ የትምህርቱን ማጠቃለያ መስጠት ነዉ።

## ልዩ ተሠጥዖ እና ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

ልዩ ችሎታ እና ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማበረታታት አስፈላጊ ነው። በውይይት ወቅት ቀድመዉ ሊጨርሱ ስለሚችሉ ሌላ ተጨማሪ ሥራን መስጠትና በሌሎች ተማሪዎች ላይ ተፅዕኖ እንዳያደርሱ ክትትል ማድረግ አስፈላጊ ነዉ። በክፍል ውስጥ ያሉ በትምህርት አቀባበላቸው ፈጣን ያልሆኑ እና ሴት ተማሪዎችን ደግሞ ተጨማሪ ሥራን እንዲሰሩ ማድረግና ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ ነዉ።

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ ለማወቅ ተከታታይነት ያለው ክትትል ማድረግ አስፈላጊ ነው፤፡ የተማሪዎችን ችሎታ በመለየት የሚያስፈልጋቸውን እገዛ ማድረግ አስፈላጊ ነው።ለምሳሌ የተለያዩ ጥያቄዎችን፤ የሙቀትና የዝናብ መቀየር የአየር ንብረት መቀየር ሊያመጡ ይችላሉ? በየቀኑ የአየር ሁኔታ መቀያየር የአንድ አከባቢ የአየር ንብረት መቀየር ሊሆን ይችላል? የሚሉትን በመጠየቅ ግንዛቤያቸዉን መሻሻል ይገባል።ሁሉም ተማሪዎች የሚጠበቅባቸዉ የመማር ብቃት ላይ መድረስ አለባቸዉ። ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ማግኘት ያልቻሉትን የተለየ እገዛ በማድረግና በእረፍት ጊዜያቸዉ የሚሰሩትን ሥራዎችን በመስጠት ግንዛቤያቸዉን እንድያሻሽሉ ማድረግ ያስፈልጋል።መሻሻል ያሳዩ ተማሪዎችን በማድነቅና በመሸለም ማበረታታት ያስፈልጋል።

## የመልመጃ 7.2. ጥያቄዎች መልስ

1. የአየር ንብረት መቀየር ማለት የአየር ንብረት ይዘቶች እንደ ሙቀት፤ ዝናብ፤ ዳመና፤ የፀሐይ ብርሃን፤ እርጥበትና የመሳሰሉት መጨመር ወይም መቀነስ ማለት ነዉ።

2. አይቻልም

## 7.1.3. የአየር ንብረት መቀየር ምክንያቶችና ችግሮቹ

ለዚህ ርዕስ የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት........................................ .........3

ተማሪዎች ቢያንስ ሊደርሱበት የሚገባ የመማር ብቃት

ከዚህ ርዕስትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡

- የአየር ንብረት መቀየር ተፅዕኖን ይናገራሉ።
- የአየር ንብረት መቀየር ምክንያቶችን ይዘረዝራሉ።
- የአየር ንብረት መቀየር መንስዔዎችን ይረዳሉ።
- የግሪን ሀዉስ ጋሶችና ምንጫቸዉን ይለያሉ።

# ቅድመ ዝግጅት

የዚህን ርዕስ ትምህርት ማስተማር ከመጀመርዎ በፊት ይህንን ርዕስ ለማስተማር የሚያግዙ የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን አየር ንብረትን ለውጥ ያስከተለዉ ለውጥና የግሪን ሀዉስ ጋስን የሚያሣይ ስዕልን ማዘጋጀትና ለትምህርቱ ሊያግዞት የሚችሉ መፅሐፍትን በማንበብ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል።

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

ይህንን ርዕስ ለማስተማር ተማሪዎችን ማዕከል ያደረገ የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን እንደ ገለፃ፤ ጥያቄና መልስ፤ በፕሮጄክት እንድሁም የቡድን ውይይት በመጠቀም ማስተማር ይቻላል። ይሁን እንጂ ለዚህ ርዕስ ይበልጥ የሚስማማና ተማሪዎችን የሚያነቃቃ የማስተማር ዘዴን መርጦ መጠቀም አስፈላጊ ነዉ። ተማሪዎች ከሚያዉቁት ተነስተዉ እንድናገሩ ለማድረግ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት መጠየቅ ያስፈልጋል። በተጨማሪም ሌሎች የተለያዩ ምንጮችን በማንበብና ያገኙትን እዉቀት መሰረት በማድረግ የትምህርቱን ማጠቃለያ መስጠት አስፈላጊ ነዉ።

## ልዩ ተሠጥዖ እና ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

ልዩ ችሎታ እና ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማበረታታት አስፈላጊ ነው። በውይይት ወቅት ቀድመዉ ሊጨርሱ ስለሚችሉ ርዕሱን ይበልጥ እንዲገነዘቡ የሚያደርጋቸዉ ሌላ ተጨማሪ ሥራን መስጠትና በሌሎች ተማሪዎች ላይ ተፅዕኖ እንዳያደርሱ ክትትል ማድረግ ነዉ። በክፍል ውስጥ ያሉ በትምህርት አቀባበላቸው ፈጣን ያልሆኑ እና ሴት ተማሪዎችን ደግሞ ተጨማሪ ሥራን እንዲሰሩ ማድረግና ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ።

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ ለማወቅ ተከታታይነት ያለው ክትትል ማድረግ አስፈላጊ ነው፤፡ የተማሪዎችን ችሎታ በመለየት የሚያስፈልጋቸውን እገዛ ማድረግ ነው።ለምሳሌ የተለያዩ ጥያቄዎችን፤ የአየር ንብረት መቀየር ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉት ምን ምን ናቸዉ? የአየር ንብረት በተፈጥሮአዊ አከባቢ ላይ የሚያመጣዉ ተፅዕኖ ምን ምን ናቸዉ? ለአየር ንብረት መቀየር ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ጋሶች ምን ምን ናቸዉ? የሚሉትን በመጠየቅ ግንዛቤያቸዉን መሻሻል ይገባል። ሁሉም ተማሪዎች የሚጠበቅባቸው የመማር ብቃት ላይ መድረስ አለባቸዉ። ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ማግኘት ያልቻሉትን የተለየ እገዛ በማድረግና በእረፍት ጊዜያቸዉ የሚሰሩትን ሥራዎችን በመስጠት ግንዛቤያቸዉን እንድያሻሽሉ ማድረግ ያስፈልጋል።መሻሻል ያሳዩ ተማሪዎችን በማድነቅና በመሸለም ማበረታታት ያስፈልጋል።

## የመልመጃ 7.3. ጥያቄዎች መልስ

### ክፍል አንድ፤ እዉነት ወይም ሀሰት ጥያቄዎች

1. ሀሰት 2. ሀሰት

### ክፍል ሁለት፤ አዛምድ ጥያቄዎች

1. ለ 2. ሐ 3. መ 4. ሀ B 2. C 3. D 4. A

### ክፍል ሦስት፤ ምርጫ

1. ለ 2. ለ

## ክፍል አራት፤ አጭር መልስ

1. በአየር ንብረት መቀየር ምክንያት የሚመጡ ችግሮች ብዙ ናቸዉ። ከእነዚህም ውስጥ ጥቅቶቹ የአለም ሙቀት መጨመር፤ የበረሀማነት መስፋፋት፤ የበህር ወለል መጨመር፤ የንፋስ አቅጣጫ መቀየር፤ የበረሃ በሽታች መብዛት፤ የህይወት ያላቸዉ ነገሮች ዝርያ መቀነስና የመሳሰሉት ናቸዉ።

## 7.1.4. የአየር ንብረት መቀየር ለሚቆጣጠር የሚሰሩ ሥራዎች

ለዚህ ርዕስ የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት……………………….………… ………3

ተማሪዎች ቢያንስ ሊደርሱበት የሚገባ የመማር ብቃት

ከዚህ ርዕስትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡

- የአየር ንብረት መቀየር የሚቆጣጠሩ ሥራዎችን ይናገራሉ።
- የአየር ንብረት መቀየር ለመቆጣጠር በሀገራችን የሚሰሩ ሥራዎችን ይገነዘባሉ።

### ቅድመ ዝግጅት

የዚህን ርዕስ ትምህርት ማስተማር ከመጀመርዎ በፊት ይህንን ርዕስ ለማስተማር የሚያግዙ የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን አየር ንብረትን ለመቆጣጠር የሚሰሩ ሥራዎችን የሚያሣይ ስዕል በማዘጋጀትና ለትምህርቱ ሊያግዞት የሚችሉ መፅሐፍትን በማንበብ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል።

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

ይህንን ርዕስ ለማስተማር ተማሪዎችን ማዕከል ያደረገ የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን እንደ ገለፃ፤ የቡድን ውይይት እንድሁም የመስክ ጉብኝት በመጠቀም ማስተማር ይቻላል። ይሁን እንጂ ለዚህ ርዕስ ይበልጥ የሚስማማና ተማሪዎችን የሚያነቃቃ የማስተማር ዘዴን መጠቀም አስፈላጊ ነዉ። ተማሪዎች ከሚያዉቁት ተነስተዉ እንድናገሩ ለማድረግ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት መጠየቅ ያስፈልጋል። በተጨማሪም ሌሎች የተለያዩ ምንጮችን በማንበብና ያገኙትን እዉቀት መሠረት በማድረግ የትምህርቱን ማጠቃለያ መስጠት አስፈላጊ ነዉ።

## ልዩ ተሠጥዖ እና ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

ልዩ ችሎታ እና ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማበረታታት አስፈላጊ ነው፡፡ በውይይት ወቅት ቀድመዉ ሊጨርሱ ስለሚችሉ ርዕሱን ይበልጥ እንዲገነዘቡ የሚያደርጋቸዉ ሌላ ተጨማሪ ሥራን መስጠትና በሌሎች ተማሪዎች ላይ ተፅዕኖ እንዳያደርሱ ክትትል ማድረግ አስፈላጊ ነዉ፡፡ በክፍል ውስጥ ያሉ በትምህርት አቀባበላቸው ፈጣን ያልሆኑ እና ሴት ተማሪዎችን ደግሞ ተጨማሪ ሥራን እንዲሰሩ ማድረግና ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ፡፡

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ ለማወቅ ተከታታይነት ያለው ክትትል ማድረግ አስፈላጊ ነው፤፡ የተማሪዎችን ችሎታ በመለየት የሚያስፈልጋቸውን እገዛ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ለምሳሌ የተለያዩ ጥያቄዎችን እንደ የአየር ንብረት መቀየር ለመቆጣጠር የሚሰሩሥራዎች ምን ምን ናቸዉ? የሚሉትን በመጠየቅ ግንዛቤያቸዉን መሻሻል ይገባል፡፡ ሁሉም ተማሪዎች የሚጠበቅባቸው የመማር ብቃት ላይ መድረስ አለባቸዉ፡፡ ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ማግኘት ያልቻሉትን የተለየ እገዛ በማድረግና በእረፍት ጊዜያቸዉ የሚሰሩትን ሥራዎችን በመስጠት ግንዛቤያቸዉን እንድያሻሽሉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡መሻሻል ያሳዩ ተማሪዎችን በማድነቅና በመሸለም ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡

## 7.1.5. የአየር ንብረት መቀየርን ለመቆጣጠር በአከባቢያችዉ የሚሰሩ ሥራዎች ለማወቅ የሚደረጉ ጥናታዊ

ለዚህ ርዕስ የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት………………………………… ………3

ተማሪዎች ቢያንስ ሊደርሱበት የሚገባ የመማር ብቃት

ከዚህ ርዕስትምህርት በኂላ ተማሪዎች፡

- የአየር ንብረት መቀየርን ለመቆጣጠር የሚሰሩ ሥራዎችን ይናገራሉ፡፡
- የአየር ንብረት መቀየርን ለመቆጣጠር እንደ ኦሮሚያ ክልል የተሰሩ ሥራዎችን ያመዛዝናሉ፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

የዚህን ርዕስ ትምህርት ማስተማር ከመጀመርዎ በፊት ይህንን ርዕስ ለማስተማር የሚያግዙ የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፤የአየር ንብረትን ለመቆጣጠር እንደ አገርና ክልል የተሰሩ ሥራዎችን የሚያሣይ ስዕል በማዘጋጀት እንዲሁም ትምህርቱን ለማስተላለፍ ሊያግዙት የሚችሉ መፅሐፍትን በማንበብ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል።

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

ይህንን ርዕስ ለማስተማር ተማሪዎችን ማዕከል ያደረገ የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን እንደ ገለፃ፤ የቡድን ውይይት እንዲሁም የመስክ ጉብኝት በመጠቀም ማስተማር ይቻላል። ይሁን እንጂ ለዚህ ርዕስ ይበልጥ የሚስማማና ተማሪዎችን የሚያነቃቃ የማስተማር ዘዴን መጠቀም አስፈላጊ ነዉ። ተማሪዎች ከሚያዉቁት ተነስተዉ እንድናገሩ ለማድረግ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት መጠየቅ ያስፈልጋል። በተጨማሪም ሌሎች የተለያዩ ምንጮችን በማንበብና ያገኙትን እዉቀት መሰረት በማድረግ ለትምህርቱ ማጠቃለያ መስጠት አስፈላጊ ነዉ።

## ልዩ ተሠጥዖ እና ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

ልዩ ችሎታ እና ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማበረታታት አስፈላጊ ነው። በውይይት ወቅት ቀድመዉ ሊጨርሱ ስለሚችሉ ርዕሱን ይበልጥ እንዲገነዘቡ የሚያደርጋቸዉ ሌላ ተጨማሪ ሥራን መስጠትና በሌሎች ተማሪዎች ላይ ተፅዕኖ እንዳያደርሱ ክትትል ማድረግ አስፈላጊ ነዉ። በክፍል ውስጥ ያሉ በትምህርት አቀባበላቸው ፈጣን ያልሆኑ እና ሴት ተማሪዎችን ደግሞ ተጨማሪ ሥራን እንዲሰሩ ማድረግና ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ።

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ ለማወቅ ተከታታይነት ያለው ክትትል ማድረግ አስፈላጊ ነው፤፡ የተማሪዎችን ችሎታ በመለየት የሚያስፈልጋቸውን እገዛ ማድረግ አስፈላጊ ነው። የተለያዩ ጥያቄዎችን ለምሳሌ፤ የአየር ንብረት መቀየር ለመቆጣጠር እንደ ኦሮሚያ የተሰሩ ሥራዎች ምን ምን ናቸዉ? እናንተ የምትኖሩበት አከባቢ የሚሰሩ ሥራዎችስ ምን ምን ናቸዉ? የሚሉትን በመጠየቅ ግንዛቤያቸዉን መሻሻል ይገባል። ሁሉም ተማሪዎች

የሚጠበቅባቸው የመማር ብቃት ላይ መድረስ አለባቸዉ። ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ማግኘት ያልቻሉትን የተለየ እገዛ በማድረግና በእረፍት ጊዜያቸዉ የሚሰሩትን ሥራዎችን በመስጠት ግንዛቤያቸዉን እንድያሻሽሉ ማድረግ ያስፈልጋል።መሻሻል ያሳዩ ተማሪዎችን በማድነቅና በመሸለም ማበረታታት ያስፈልጋል።

## 7.1.6. የአየር ብክለት

ለዚህ ርዕስ የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት……………………..………… ………2

ተማሪዎች ቢያንስ ሊደርሱበት የሚገባ የመማር ብቃት

ከዚህ ርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡

- የአየር ብክለት ምንነት ይገልፃሉ።
- በአየር ብክለት ምክንያት የሚመጡ ችግሮችን መናገር ይችላሉ።
- የአየር ብክለትን ለመቆጣጠር የሚረዱ ዘዴዎችን ያጤናሉ።

# ቅድመ ዝግጅት

የዚህን ርዕስ ትምህርት ማስተማር ከመጀመርዎ በፊት በአከባቢያቸዉ አየርንና አከባቢን የሚበክሉ ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ለማስተማር የሚያግዙ የተለያዩ መፅሐፍትን በማንበብ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል።

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

ይህንን ርዕስ ለማስተማር ተማሪዎችን ማዕከል ያደረገ የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን እንደ ገለፃ፤ የቡድን ውይይት እንድሁም የመስክ ጉብኝት በመጠቀም ማስተማር ይቻላል። ይሁን እንጂ ለዚህ ርዕስ ይበልጥ የሚስማማና ተማሪዎችን የሚያነቃቃ የማስተማር ዘዴን መጠቀም አስፈላጊ ነዉ። ተማሪዎች ከሚያዉቁት ተነስተዉ እንዲናገሩ ለማድረግ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት መጠየቅ ያስፈልጋል። በተጨማሪም ሌሎች የተለያዩ ምንጮችን በማንበብና ያገኙትን እዉቀት መሠረት በማድረግ የትምህርቱን ማጠቃለያ መስጠት አስፈላጊ ነዉ።

## ልዩ ተሠጥዖ እና ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

ልዩ ችሎታ እና ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማበረታታት አስፈላጊ ነው። በውይይት ወቅት ቀድመዉ ሊጨርሱ ስለሚችሉ ርዕሱን ይበልጥ እንዲገነዘቡ የሚያደርጋቸዉ ሌላ ተጨማሪ ሥራን መስጠትና በሌሎች ተማሪዎች ላይ ተፅዕኖ እንዳያደርሱ ክትትል ማድረግ አስፈላጊ ነዉ። በክፍል ውስጥ ያሉ በትምህርት አቀባበላቸው ፈጣን ያልሆኑ እና ሴት ተማሪዎችን ደግሞ ተጨማሪ ሥራን እንዲሰሩ ማድረግና ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ።

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ ለማወቅ ተከታታይነት ያለው ክትትል ማድረግ አስፈላጊ ነው፤፡ የተማሪዎችን ችሎታ በመለየት የሚያስፈልጋቸውን እገዛ ማድረግ አስፈላጊ ነው።ለምሳሌ የተለያዩ ጥያቄዎችን እንደ የአየር ብክለት ማለት ምን ማለት ነዉ? አየርን የሚበክሉ ነገሮች ምንጫቸዉ ምን ምን ናቸዉ? በአየር ብክለት ምክንያት የሚመጡ ችግሮች ምን ምን ናቸዉ? የሚሉትን በመጠየቅ ግንዛቤያቸዉን መሻሻል ይገባል። ሁሉም ተማሪዎች የሚጠበቅባቸው የመማር ብቃት ላይ መድረስ አለባቸዉ። ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ማግኘት ያልቻሉትን የተለየ እገዛ በማድረግና በእረፍት ጊዜያቸዉ የሚሰሩትን ሥራዎችን በመስጠት ግንዛቤያቸዉን እንድያሻሽሉ ማድረግ ያስፈልጋል።መሻሻል ያሳዩ ተማሪዎችን በማድነቅና በመሸለም ማበረታታት ያስፈልጋል።

## የመልመጃ 7.4 ጥያቄዎች መልስ

**ክፍል አንድ፤ እዉነት ሀሰት ጥቄዎች**

1. እዉነት 2. ሀሰት

**ክፍል ሁለት፤ አጭር መልስ ጥያቄዎች**

**1. አንደኛ ደረጃ አየር በካይ የሆኑት** ($CO_2$, $SO_2$) ሲሆኑ በሁለተኛ ደረጃ አየርን የሚበክሉት ጭጋግና ዳመና ናቸዉ።

2. በአየር ብክለት የሚመጡ ችግሮች የመተንፈሻ አካልን የሚጎዱ በሽታች፤ የአለም ሙቀት መጨመር፤ አሲድ ዝናብ፤ የኦዞን መሳሳትና የመሳሰሉት ናቸዉ።

## 7.1.7.የውሃ እጥረት

ለዚህ ርዕስ የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት…………………………….……… ………1

ተማሪዎች ቢያንስ ሊደርሱበት የሚገባ የመማር ብቃት

ከዚህ ርዕስ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች፡

- የውሃ እጥረት ማለት ምን እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡
- በውሃ እጥረት ምክንያት የሚከሰቱ ችግርን ይዘረዝራሉ፡፡
- የውሃ እጥረትን ለመቆጣጠር የሚረዱ ዘዴዎችን ያጤናሉ፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

የዚህን ርዕስ ትምህርት ማስተማር ከመጀመርዎ በፊት ትምህርቱን ለማስተማር የሚያግዙ የተለያዩ የውሃ እጥረትን የሚያስከትሉ ጉዳቶችን የሚያሳይ ስዕል ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

ይህንን ርዕስ ለማስተማር ተማሪዎችን ማዕከል ያደረገ የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን እንደ ገለፃ፤ የቡድን ውይይት እንድሁም የመስክ ጉብኝት በመጠቀም ማስተማር ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ ለዚህ ርዕስ ይበልጥ የሚስማማና ተማሪዎችን የሚያነቃቃ የማስተማር ዘዴን መጠቀም አስፈላጊ ነዉ፡፡ ተማሪዎች ከሚያዉቁት ተነስተዉ እንድናገሩ ለማድረግ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም ሌሎች የተለያዩ ምንጮችን በማንበብና ያገኙትን እዉቀት መሠረት በማድረግ የትምህርቱን ማጠቃለያ መስጠት አስፈላጊ ነዉ፡፡

## ልዩ ተሠጥዖ እና ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

ልዩ ችሎታ እና ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማበረታታት አስፈላጊ ነው፡፡ በውይይት ወቅት ቀድመዉ ሊጨርሱ ስለሚችሉ ርዕሱን ይበልጥ እንዲገነዘቡ የሚያደርጋቸዉ ሌላ ተጨማሪ ሥራን መስጠትና በሌሎች ተማሪዎች ላይ ተፅዕኖ እንዳያደርሱ ክትትል ማድረግ አስፈላጊ ነዉ፡፡ በክፍል ውስጥ ያሉ በትምህርት አቀባበላቸው ፈጣን ያልሆኑ

እና ሴት ተማሪዎችን ደግሞ ተጨማሪ ሥራን እንዲሰሩ ማድረግና ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ።

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ ለማወቅ ተከታታይነት ያለው ክትትል ማድረግ አስፈላጊ ነው፤፡ የተማሪዎችን ችሎታ በመለየት የሚያስፈልጋቸውን እገዛ ማድረግ አስፈላጊ ነው።የተለያዩ ጥያቄዎችን ለምሳሌ የውሃ እጥረት ማለት ምን ማለት ነዉ? የውሃ እጥረትን ሊያመጡ የሚችሉ ነገሮች ምን ምን ናቸዉ? የውሃ ብክለትና የውሃ እጥረት አንድነት አላቸው ወይ? የሚሉትን በመጠየቅ ግንዛቤያቸዉን መሻሻል ይገባል። ሁሉም ተማሪዎች የሚጠበቅባቸው የመማር ብቃት ላይ መድረስ አለባቸዉ። ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ማግኘት ያልቻሉትን የተለየ እገዛ በማድረግና በእረፍት ጊዜያቸዉ የሚሰሩትን ሥራዎችን በመስጠት ግንዛቤያቸዉን እንድያሻሽሉ ማድረግ ያስፈልጋል።መሻሻል ያሳዩ ተማሪዎችን በማድነቅና በመሸለም ማበረታታት ያስፈልጋል።

## የመልመጃ 7.5. ጥያቄዎች መልስ

1. ውሃ ማለት ፈሳሽ፤ ሽታ አልባ፤ ጣዕም አልባ፤ ህይወት ላላቸዉ ነገሮች በሙሉ በጣም አስፈላጊ የሆነና በሰዉነታችን ውስጥ በብዛት የሚገኝ ነገር ነዉ። ውሃ ብዙ ተቀሜታ አለዉ። ከእነዚህም ውስጥ ጥቅቶቹ ለመጠጥ፤ ለንፅህና፤ ምግብ ለማዘጋጀትና የመሳሰሉት ናቸዉ።
2. እስከ 50 ሊትር መጠቀም አለበት። የሁን እንጂ ብዙ ሀገሮች ይህንን ማሳካት አልቻሉም። የሚጠቀሙትም ለመጠጥነት፤ ለንፅህናና ምግብ ለማብሰል ነዉ።
3. የውሃ እጥረት ማለት የውሃ አቅርቦትና ፍላጎት አለመጣጣም ማለት ነዉ።
4. የውሃ እጥረትን ለመቆጣጠር ውሃን በቁጠባ መጠቀም፤ ህብረተሰብን ማስተማር፤ ውሃን በማጥራት መልሶ መጠቀም፤ በውሃ የመስኖ አጠቃቀምን መሻሻል፤ የውሃን ንፅህና መጠበቅና የመሳሰሉት ናቸዉ።

### 7.1.8. የደን መመንጠር

ለዚህ ርዕስ የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት…………………………….……… ………2

ተማሪዎች ቢያንስ ሊደርሱበት የሚገባ የመማር ብቃት

ከዚህ ርዕስትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡

- የደን መመንጠር ምንነት ይገልፃሉ፡፡
- የደን መመንጠር መንስኤዎችና የሚያደርሰዉ ጉዳት ምን እንደሆነ ይዘረዝራሉ፡፡
- የደን መመንጠርን ለመከላከል የሚረዱ ዘዴዎችን የገነዘባሉ፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

የዚህን ርዕስ ትምህርት ማስተማር ከመጀመርዎበፊትትምህርቱን ለማስተማር የሚያግዙ የተለያዩ በደን መመንጠር የሚመጡ ችግሮችን የሚያሳይ ስዕል ፤ ደን የተመነጠረና በውሃ የተጎዱ ቦታዎችን የሚያሳይ ፎቶ ማዘጋጀት፤ ከተቻለ ከኢንተርኔት መዉሰድ ያስፈልጋል፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

ይህንን ርዕስ ለማስተማር ተማሪዎችን ማዕከል ያደረጉ የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን እንደ ገለፃ፤ የቡድን ውይይት እንዲሁም የመስክ ጉብኝት በመጠቀም ማስተማር ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ ለዚህ ርዕስ ይበልጥ የሚስማማና ተማሪዎችን የሚያነቃቃ የማስተማር ዘዴዎች ከተገኙ መጠቀም አስፈላጊ ነዉ፡፡ ተማሪዎች ከሚያዉቁት ተነስተዉ እንድናገሩ ለማድረግ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም ሌሎች የተለያዩ ምንጮችን በማንበብና ያገኙትን እዉቀት መሠረት በማድረግ የትምህርቱን ማጠቃለያ መስጠት አስፈላጊ ነዉ፡፡

## ልዩ ተሠጥዖ እና ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች

ልዩ ችሎታ እና ግንዛቤ ያላቸው ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማበረታታት ነው፡፡ በውይይት ወቅት ቀድመዉ ሊጨርሱ ስለሚችሉ ርዕሱን ይበልጥ እንዲገነዘቡ የሚያደርጋቸዉ ሌላ ተጨማሪ ሥራን መስጠትና በሌሎች ተማሪዎች ላይ ተፅዕኖ እንዳያደርሱ ክትትል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በክፍል ውስጥ ያሉ በትምህርት አቀባበላቸው ፈጣን ያልሆኑ እና ሴት ተማሪዎችን ደግሞ ተጨማሪ  ሥራን እንዲሰሩ ማድረግና ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ፡፡

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ ለማወቅ ተከታታይነት ያለው ክትትል ማድረግ አስፈላጊ ነው፤፡ የተማሪዎችን ችሎታ በመለየት የሚያስፈልጋቸውን እገዛ ማድረግ

ነው፡፡የተለያዩ ጥያቄዎችን ለምሳሌ የደን መመንጠር ማለት ምን ማለት ነዉ? የደን መመንጠር ሊያመጡ የሚችሉ ነገሮች ምን ምን ናቸዉ? የደን መመንጠር የሚያስከትለዉ ጉዳት ምን ምን ናቸዉ? የሚሉትን በመጠየቅ ግንዛቤያቸዉን መሻሻል ይገባል፡፡ ሁሉም ተማሪዎች የሚጠበቅባቸው የመማር ብቃት ላይ መድረስ አለባቸዉ፡፡ ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት ማግኘት ያልቻሉትን የተለየ እገዛ በማድረግና በእረፍት ጊዜያቸዉ የሚሰሩትን ሥራዎችን በመስጠት ግንዛቤያቸዉን እንድያሻሽሉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡መሻሻል ያሳዩ ተማሪዎችን በማድነቅና በመሸለም ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡

## የመልመጃ 7.6. ጥያቄዎች መልስ

1. የደን መመንጠር የሚያመጣዉ ችግሮች ህይወት ያላቸዉ ነገሮች መጥፋት፤የስርዓተ ምህዳር መፍረስ፤የሙቀት መጨመር፤ የባህር ውሃ መጨመር፤ የአየር ንብረት መቀየርና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡
2. በቁጠባ መጠቀም፤ መልሶ መጠቀምና እንደገና መልሶ መትከል ናቸዉ፡፡

## የምዕራፍ ሰባት ጥያቄዎች መልስ

**ክፍል አንድ፤ እዉነት ሀሰት ጥያቄዎች**

1. ሀሰት 2. ሀሰት 3. እዉነት

**ክፍል ሁለት፤ ምርጫ ጥያቄዎች**

**4. ሀ 5. ለ 6. ሐ**

**ክፍል ሦስት፤ አጭር መልስ ጥያቄዎች**

6. ሰዉ ሰራሽ የሆኑት ብዙ ሲሆኑ ከእነዚህም ውስጥ የደን መጨፍጨፍ፤ (የእርሻ፤ ማዕድናት ማዉጣትና ከተሞች) መስፋፋት፤ በእንጨትና በእንጨት ውጤቶች መጠቀም ፍላጎት መጨመር፡ የግጦሽ መሬት ከአቅም በላይ ማስጋጥ፤ መሳሪታዊ የሆኑ ነገሮችን ያለ ዕቅድ ማስፋፋትና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡

8. የግሪን ሃዉስ ጋሶችና ምሳሌያቸዉ ቀጥለዉ ካለዉ ሠንጠረዥ ተመልከቱ

| ተ.ቁ | ውክል | ምንጫቸዉ | የሚያደርሰዉ ጉዳት |
|---|---|---|---|
| 1 | $CO2$ | **የመሬት አጠቃቀም መቀየር፤ ደንን ማጥፋት፤እርሻ፤ የነዳጅ መቃጠልና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡** | የከባቢ አየር ሙቀት እንድጨምር ያደርጋል |
| 2 | $CH_4$ | **የእርሻ ምርት ቅሪቶች፤ የተፈጥሮ ጋስ** | ሁለተኛ ደረጃ |
| 3 | $N_2O$ | **ፋብሪካዎች፤ለሃይል ምንጭ፤ መዳበሪያ** | $O_3$ በማፍረስ ይታወቃል |
| 4 | CFC | ተፈጥሮአዊ ምንጭ የለዉም፡፡ ሰዉ ሰራሽ የአየር በካይ | $O_3$ በማፍረስ ይታወቃል |
| 5 | ትነት $H_2O$ | ከውሃ ገፅታ ላይ በሙቀት ምክንያት ይተናል | H2O እንድተን ያደርጋል |

# ሕብረተሰብ ትምህርት ሲለበስ

# 8ኛ ክፍል

# ምዕራፍ አንድ
# የመሬት አፈጣጠር ባህሪያት

ለዚህ ምዕራፍ የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት………………………………………….. 20

## ከምዕራፉ ትምህርት የሚጠበቁ ዉጤቶች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኃላ:

- ❖ የመሬትን ገፅታ የሚቀይሩ ውስጣዊ እና ውጫዊ ሀይሎችን ትዘረዝራለህ/ሽ፡፡
- ❖ በመሬት ውስጣዊ እና ውጫዊ ሀይሎች ምክንያት የተፈጠሩ የተለያዩ የመሬት አቀማመጥን ትዘረዝራለህ/ሽ፡፡
- ❖ የአየር ንብረትን የሚቆጣጠሩ ነገሮችን ትገልጻለህ/ሽ ፡፡
- ❖ የአየር ንብረት ይዘቶችን ትዘረዝራለህ/ሽ ፡፡
- ❖ በአየር ንብረት እና በአየር ሁኔታ መካከል ያለውን ልዩነት ትለያለህ/ሽ፡፡
- ❖ በከባቢ አየር ውስጥ የሚገኙ የአየር ንብረት ንብርብሮችና ባህሪያቸውን ትገልፃለህ፡፡

| የመማር ብቃቶች | ይዘት | የመማር ማስተማር ዘዴዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • የመሬትን ገፅታ የሚቀይሩ ውስጣዊና ውጫዊ ሃይሎችን ይለያሉ፡፡<br>• በመሬት ውስጣዊና ውጫዊ ሃይሎች ምክንያት የተፈጠሩ የመሬት ገፅታን ይለያሉ፡፡<br>• የመሬት ውስጣዊና ውጫዊ ሃይሎች ሂደቶች በሰዉ ልጅ ህይወት ላይ የሚያመጡትን ተፅዕኖዎችን ይገልፃሉ፡፡<br>• የከባቢ አየር ንብርብር አይነቶች፤ የአየር ንብረትና የአየር ሁኔታን ባህሪይን የገልፃሉ ይገልፃሉ፡፡ | **1.** የመሬት አፈጣጠር ባህሪያት<br>1.1. የመሬትን ገፅታ የሚቀይሩ ሃይሎች<br>1.1.1. የመሬትን ገፅታ የሚቀይሩ ውስጣዊ ሃይሎች<br>1.1.2. የመሬትን ገፅታ የሚቀይሩ ውጫዊ ሃይሎች<br>1.2. የከባቢ አየር መዋቅሮች፤ ይዘቶችና ሥርጭታቸዉ<br>1.2.1 በከባቢ አየር ውስጥ የሚገኙ ይዘቶች<br>1.2.2. የከባቢ አየር ንብርብሮች መዋቅሮች | • የመሬትን ገፅታ የሚቀይሩ የመሬት ውስጣዊና ውጫዊ ሃይሎች መምህሩ ገለፃ ከሰጡ በኂላ ተማሪዎች የሚያውቁትን እንዲናገሩ ዕድል መስጠት ነዉ፡፡ በመቀጠል የመሬት ውስጣዊና ውጫዊ ሃይሎች የሚያሳይ ሥዕል ወይንም ቪድዮ ለተማሪዎች ማሳየት ነዉ፡፡<br>• ተማሪዎች በቡድን ሆነዉ ወደ ቤተመፃሕፍት በመሄድ በአከባቢያቸዉ የሚገኘው የመሬት አቀማመጥ በውስጣዊና ውጫዊ ሃይሎች አማካይነት እንዴት እንደተፈጠረ እንዲገልፁ ማድረግ፡፡<br>• ተማሪዎች ካርታ በማዘጋጀት በአከባቢያቸዉ የሚገኘውን የመሬት አቀማመጥ እንዲያሳዩ ማድረግ፡፡ | • ክፍል ውስጥ በመዘዋወር የተማሪዎችን ውይይት በመከታተል ግብረ መልስ መስጠት፡፡<br>• ተማሪዎች የመሬት ገፅታ መቀየር ሀደት መገንዘባቸዉን ጥያቄ በመጠየቅ ማረጋገጥ ነው፡፡<br>• የመሬትን እንቅስቃሴዎች ውጤት መግለፅ<br>• ተማሪዎች በቡድን ውይይት ላይ እንዲሳተፉና ለጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ ማበረታታት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| • የአየር ንብረትና የአየር ሁኔታን ልዩነት መለየት<br>• በአየር ንብረት ይዘቶችና አየር ንብረትን የሚቆጣጠሩ ነገሮችን መዘርዘር<br>• የዝናብና የሙቀት ልዩነት በደጋ፤ በወይና ደጋና በቆላ አከባቢዎች የመፈጠር ምክንያት ምን እንደሆነ በማነፃፀር እንድገነዘቡ ማድረግ፡፡<br>• የአከባቢያቸዉን ዕለታዊና ወረሃዊ የአየር ሁኔታ መረጃን መሰብሰብ፤ መተንተን፤ ማቅረብ በመጨረሻ ም ማጠቃለል፡፡<br>• የአየር ንብረትን የሚያሳይ ግራፍ መስራት | 1.3. የአየር ንብረትና የአየር ሁኔታ ይዘቶች ፤ የአየር ንብረትና የአየር ሁኔታ የሚቆጣጠሩ ነገሮች<br>1.3.1. የአየር ንብረትና የአየር ሁኔታን ምንነት<br>1.3.2. የአየር ንብረትና የአየር ሁኔታ ይዘቶች<br>1.3.3. የአየር ንብረትና የአየር ሁኔታን የሚቆጣጠሩ ነገሮች<br>1.3.4. የዕለታዊና ወቅታዊ የአየር ሁኔታ ልዩነቶች | • ጥያቄና መልስን በመጠቀም በከባቢ አየር ውስጥ የሚገኙ ነገሮች እንዲለዩ ማድረግ፡፡ በመቀጠል ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት የከባቢ አየር ንብርብሮችና ባህሪያቸዉ ላይ በመወያየት ግንዛቤያቸዉን እንደያዳብሩ ማድረግ፡፡ የተማሪዎችን ውይይት ተጨባጭ ለማድረግ መምህራን የከባቢ አየር ንብርብሮችን የሚያሳይ ግራፍ በማዘጋጀት ማሳየት ያስፈልጋል፡፡ .<br>• መምህራን ተማሪዎችን በማነቃቃት ያለፉትን ትምህርት እንድያስታውሱ በማድረግና ከዕለቱ ትምህርት ጋር በማያያዝ የአየር ንብረትና የአየር ሁኔታ ምንነት እንዲሁም የአየር ሁኔታን የሚቆጣጠሩ ነገሮችን እንዲገልፁ ማድረግ፡፡<br>• ተማሪዎች በቡድን ውይይት ውስጥ የአከባቢያቸዉ የዝናብ የሙቀት ልዩነት እንድረዱ ድረግ፡፡<br>• ተማሪዎችን ወደ ሜትሮሎጂ ጣቢያ በመዉሰድ መረጃዎችን ሰብስቦ በማቀናጀት በክፍል ውስጥ ሪፖርት እንድያቀርቡ ማድረግ ነዉ፡፡ | • በገለጻ ወቅት አልፎ አልፎ ተማሪዎችን ጥያቄ በመጠየቅመከታተላቸውን ማረጋገጥ፡፡<br>• ተማሪዎች የአየር ንብረትና የአየር ሁኔታ ልዩነት እንድሁም እነሱን የሚቆጣጠሩ ነገሮችን እንዲለዩ ማድረግ፡፡<br>• የተማሪዎች የቡድን ውይይት በመከታተል የሚኖረውን የዝናብና የሙቀት መጠን ልዩነት መለየታቸዉን ማረጋገጥ፡፡<br>• ተማሪዎች በመስክ ጉብኝት ላይ መረጃን መሰብሰብ ማቀናበራቸውን በተመለከተ ግብረ ማልስ መስጠት፡፡ |

**ምዕራፍ ሁለት፡ ህዝብና ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች**

**ለዚህ** ምዕራፍ የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት………………………………………….. 27

## ከምዕራፉ ትምህርት የሚጠበቁ ዉጤቶች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኃላ:

- ❖ ከጊዜ ወደ ጊዜ ያለውን የባህል ዕድገትና ለውጥ ይገልፃሉ፡፡
- ❖ የሰዎች ከቦታ ወደ ቦታ እንቅስቃሴ በህዝብ አሰፋፈር ላይ ያለውን ተፅዕኖ ይገልፃሉ፡፡
- ❖ የንግድ ምንነትና በአለም ህዝቦች ያለውን ግንኙነት ለማጠናከር የሚጫወተውን ሚና ይገልፃሉ፡፡
- ❖ የተጠቃሚዎች መብትና የምርት አቅርቦት መካከል ያለዉ ችግር ይተነትናሉ፡፡
- ❖ ግብር እና ታክስ ለመንግስት ያለዉን ጠቀሜታ ይዘረዝራሉ፡፡

| የመማር ብቃቶች | ይዘት | የመማር ማስተማር ዘዴዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • ለባህል እድገት ምክንያት የሚሆኑ ነገሮችን ይገልፃሉ፡፡<br>• ሃይማኖትና ቋንቋ የባህል መገለጫዎች መሆናቸዉን ይገልፃሉ፡፡<br>• ሃየማኖትና፣ ቋንቋ ለባህል ልዩነት መሰረት መሆናቸዉን ይገልፃሉ፡፡<br>• ግሎባላይዜሽን በማህበረሰብ በህል መቀየር ላይ ያለዉ ተፅዕኖ ይለያሉ፡፡<br>• በክፍል ውስጥ ክርክር ያክሄዳሉ፡፡<br>• ለማህበረሰብ ሀገር በቀል እዉቀት ክብር ይሰጣሉ፡፡<br>• የተለያዩ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን ይገልፃሉ፡፡ | **2. ህዝብና የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች**<br>2.1. የባህል ልዩነትና መለወጥ<br>2.1.1. የማህበረሰብ የባህል ዕድገት<br>2.1.2. ዋና ዋና የባህል መገለጫዎች (ቋንቋና ሃይማኖት )<br>2.1.3. ግሎባላይዜሽንና የበህል መለወጥ<br>2.2. ዋና ዋና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች<br>2.2.1. አንደኛ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች<br>2.2.2. ሁለተኛ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች<br>2.2.3.ሦስተኛ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች | በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት የማህበረሰብ ባህል ልዩነትና መለወጥ ላይ ውይይት እንዲያካሄዱ ማድረግና<br>ተማሪዎችን በግል፣በጥንድ፣አራት እንድሁም በስምንት በመክፈል የሚከተሉትን ጥያቄዎችን መጠየቅ፡፡<br>የኢትዮጵያ ህዝቦች ባህል ልዩነትና አንድነት ምንድነዉ?<br>የአለም ህዝብ ባህል መለወጥ ምክንያት የሆኑት ምን ምን ናቸዉ?<br>ለተማሪዎች የአለም ህዝብ ባህል ልዩነቶች የሚያሳይ ቪድዮን በማሳየት እንዲናገሩ ማድረግ | ▪የቡድን ውይይትን መከታተል፤ ባለዉ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ላይ መረጃን መሰብሰብና ተማሪዎች በትክክል መስራት አለመስራታቸዉን ግብረ መልስ መስጠት፡፡<br>▪ ተማሪዎች የባህል መገለጫዎችና ስለባህል አመጣጥ እንዲዘረዝሩ ማድረግ፡፡<br>▪ ተማሪዎች የተለያዩ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን መገንዘባቸዉን መረዳት፡፡<br>▪የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን ከተለያዩ ሀገሮች እድገት ጋር በማያያዝ ያለዉ ጠቀሜታ ምን እንደሆነ እንድገልፁ መጠየቅ፡፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| • የተለያዩ ሀገሮችን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ከእድገት ደረጃቸው ጋር በመያያዝ መግለፅ፡፡<br>• ያደጉና በማደግ ላይ ያሉትን ሀገሮች ከእርሻ እንቅስቃሴያቸው ጋር በማወዳደር ይገመግማሉ፡፡<br>• የመረጃ ፍሰት፣ የምርትና የአገልግሎት ልዩነትን መግለፅ፡፡<br>• ንግድ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ ያለዉ ድርሻ መገምገም፡፡<br>• የመጓጓዣ ዓነቶችን መግለፅ፡፡<br>• የውጪ ሀገር የንግድ ተቋማት በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ ያላቸው ድርሻ መለየት፡፡<br>• ፍላጎትና የምርት አቅርቦት በገበያ ዋጋ ላይ ያላቸውን ተፅዕኖን መግለፅ፡፡<br>• የፍላጎትና የምርት አቅርቦት መመጣጠን የሚያሳይ ግራፍ በማየት መረዳት፡፡<br>• ትክክለኛ የሆነ የገበያ ውድድር የሚፈጠርበትን ሁኔታ መረዳት፡፡<br>• የምርት ተጠቃሚዎችንና የአምራቾችን ሥርጭት መረዳት፡፡<br>• የመንግስት ግብርና ታክስ ምንነት መግለፅ፡፡<br>• የኢትዮጵያ ግብር እና ታክስ አመጣጥ ምክክር ማካሄድ፡፡ | • ያደጉና በማደግ ላይ ያሉ ሀገሮች የኢኮኖሚ መሰረታዊ እንቅስቃሴዎች<br>2.3. ንግድ፣ ገበያና የመንግስት ግብር<br>2.3.1.የንግድና የግብር አመጣጥ ፅንሰ ሀሳብ<br>➢ የንግድ ጥቅም<br>➢ የንግድ ዓይነቶች<br>➢ የአቅርቦትና ፍላጎት በገበያ ላይ ያለዉ ተፅዕኖ<br>➢ ትላልቅ የገበያ ክንውኖች<br>➢ የገበያ ውድድር ፅንሰ ሀሳብ<br>➢ የተጠቃሚዎች መብትና የአቅርቦት ችግር<br>2.4. የመንግስት ታክስና ግብር<br>➢ የታክስና የግብር ምንነትና ትርጉም<br>➢ የኢትዮጵያ ታክስና ግብር አመጣጥና እድገት<br>➢ የመንግስት ታክስና ግብር ጠቀሜታ | ▪ ተማሪዎች የቡድን ውይይት በማድረግ የሀገር የዕድገት ደረጃ ከተለያዩ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ጋር በማያያዝ እንዲገልፁ ማድረግ፡፡<br>▪ የገለፃ ዘዴን በመጠቀም ተማሪዎች የንግድ አመጣጥ፣ የምርት ሥርጭትና መሠረታዊ አገልግሎቶችን መለየትና እንዲገልፁ መምራት፡፡<br>▪ ካርታን በመጠቀም የአለም የንግድ መስመሮች ሥርጭት እንድያሳዩ ማድረግ፡፡<br>▪ ተማሪዎች የቡድን ውይይት በሚያደርጉበት ወቅት በግራፍ ፍላጎት፣ አቅርቦትና የገበያ ሁኔታ ምን እንደሚመስል እንዲገልፁ መርዳት፡፡<br>▪ ተማሪዎች በተጠቃሚዎች ባህሪና የገበያ ምንነት ላይ አሣይመንት ሠርተዉ እንድያቀርቡ መርዳት፡፡<br>▪ ተማሪዎች የተለያዩ መረጃዎችን በመፈተሽ ታክስና ግብር ለመንግስት ያላቸውን ጠቀሜታ እንዲዘረዝሩ መርዳት፡፡ | ▪የተማሪዎችን የቡድን ውይይትን በመከታተል በተማሪዎች ተሳትፎ ላይ ግብረ መልስ መስጠት፡፡<br>• ተማሪዎች የቡድን ውይይት ውስጥ መሳተፋቸውን ለማረጋገጥ አልፎ አልፎ ጥያቄዎችን መጠየቅ፡፡<br>▪የተማሪዎች ውይይት በመከታተል በተማሪዎች ተሣትፎ ላይ ግብረ መልስ መስጠት፡፡<br>▪የተማሪዎችን አሳይመንት በመሰብሰብ በትክክል መስራታቸዉን በማረጋገጥ ግብረ መልስ መስጠት |

## ምዕራፍ ሦስት፡ የተፈጥሮ ሀብት፤ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች እድገት

**ለዚህ** ምዕራፍ የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት…………………………………………….. 11

### ከምዕራፉ ትምህርት የሚጠበቁ ዉጤቶች፡

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኃላ:

- የተፈጥሮ ሀብት በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት ላይ ያለዉ ጠቀሜታ ምን እንደሆነ ያጤናሉ፡፡
- በተፈጥሮ ሀብት መጠቀም በሀገር እድገት ላይ ያለዉን ጠቀሜታ ፅንሰ ሀሳብ ይገልፃሉ፡፡
- ሰዎች በሚኖሩበት አከባቢ በተፈጥሮ ሀብት እንዴት እንደሚጠቀሙ ይናገራሉ፡፡
- በተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ላይ በማህበረሰብ ውስጥ የሚነሱ ግጭቶች እንዴት እንደሚፈቱ ይለያሉ፡፡.

| የመማር ብቃቶች | ይዘት | የመማር ማስተማር ዘዴዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • የተፈጥሮ ሀብቶች በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ላይ ያላቸዉን ጠቀሜታ ማጤን፡፡<br>• በተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ላይ ተፅዕኖ የሚያመጡ ነገሮችን መለየት፡፡<br>• በሚትኖሩበት አከባቢ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ከጊዜ ወደ ጊዜ ለምን እንደሚቀያየር መግለፅ፡፡<br>• የተፈርሮ ሀብት አጠቃቀምና እንክብካቤ ፅንሰ ሀሳብ መግለፅ፡፡ | **3. የተፈጥሮ ሀብት፤ኢኮኖሚያዊና መህበራዊ እድገት**<br><br>3.1. የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምና እንክብካቤ ቀጣይነት ላለዉ እድገት<br><br>3.1.1. የተፈጥሮ ሀብት በቀጣይነት መጠቀም በኢኮኖሚ ውስጥ ያለዉ ጠቀሜታ<br><br>3.1.2. በተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ላይ ተፅዕኖ የሚያደርሱ ነገሮች<br><br>3.1.3. የተፈጥሮ ሀብት ከጊዜ ወደ ጊዜ ያለዉ ጠቀሜታ<br><br>3.1.4. የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምና እንክብካቤ<br>➢ የተፈጥሮ ሀብት ፍቺ<br>➢ የተፈጥሮ ሀብት በቀጣይነት መጠቀም ምንነት<br>➢ የአፈር እንክብካቤና በቀጣይነት መጠቀም | ▪ ተማሪዎች በተፈጥሮ ሀብት(አፈር፤ ውሃና ደን) በቁጠባ መጠቀም በኢኮኖሚ እድገት ላይ ያለዉን ጠቀሜታ እንዲገነዘቡ መርዳት፡፡<br>▪ ተማሪዎች የኢትዮጵያ የፍዝካል ካርታን በመጠቀም የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሀብት (አፈር፤ ወንዞችን፤ ውሃንና ደኖችን) እንድያሳዩ ማገዝ፡፡<br>▪ ተማሪዎች የአከባቢያቸዉን ምልከታ በማካሄድ የአፈር፤ የውሃና የደን ሥርጭት ለይተዉ እንዲረዱ በማድረግና ሪፖርት እንድያቀርቡ መርዳት፡፡<br>▪ በክፍል ውስት ተማሪዎችን በቡድን በመክፈል የተፈጥሮ ሀብት ሥርጭትና በተፈጥሮ ሀብት ምክንያት የሚከሰቱ ግጭቶች ላይ ምክክር እንድያደርጉ ማድረግ፡፡<br>. | ▪ የተማሪዎችን የውይይት ተሣትፎን በመመልከት ጥንካሬያቸዉንና ድክመታቸዉን በመመዝገብ ግብረ መልስ መስጠት፡፡<br>▪ ተማሪዎች በውሃ፤ በአፈር፤ በደንና በዱር እንስሳት በስርዓት አጠቃቀም ላይ ህብረተሰብን እንዲያስገበዝቡ ማበረታታት፡፡<br>▪የተማሪዎችን ውይይት በመመልከት<br>➢ በተፈጥሮ ሀብት ያለቁጠባ መጠቀም ምን ዓይነት ጉዳት በአከባቢ ማህበረሰብ ላይ እንደሚያመጣ እንዲገልፁ መርዳት፡፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| • ተማሪዎች በአከባቢያቸዉ በተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ላይ የሚፈጥሩ ግጭቶችን ህብረተሰብ እንዴት እንደሚፈቱ መገምገም፡፡<br>• በተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ ላይ ተማሪዎች ከአከባቢዉ ህብረተሰብ ጋር እንዲሳተፉ ማድረግ፡፡<br>• በተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ ላይ የህብረተሰቡ የእዉቀት ደረጃን መግለፅ | ➢ የደን እንክብካቤና በቀጣይነት የመጠቀም ሁነታ፡፡<br>➢ የዱር እንስሳት እንክብካቤና በቀጣይነት የመጠቀም ሁነታ፡፡<br>3.2. ያለእንክብካቤ በተፈጥሮ ሀብት መጠቀም የሚመጡ ጉዳቶች፡፡<br>3.3. በተፈጥሮ ሀብት መጠቀም ምክንያት የሚከሰቱ ግጭቶች፡፡ የፕሮጀክት ሥራ፡ ተማሪዎች የአፈር፤ የውሃና ደን ምልከታ በማድረግ ሪፖርት እንድያቀርቡ ማድረግ | ▪ ተማሪዎች የኮንሶ ህዝብ ልምድ ማዕከል በማድረግ ህብረተሰቡ በተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ ላይ ያላቸዉን ጥናታዊ ፅሑፍ እንድያካህዱና ለክፍል ተማሪዎች ሪፖርት እንድያቀርቡ ማበረታታት፡፡ | ግጭትን በሰላማዊ መንገድ መፍታት ያለዉ ጠቀሜታ ምን እንደሆነ መግለፅ እንድችሉ ማድረግ፡፡ |

# ምዕራፍ 4፡ ዘመናዊው  የአለም ታሪክና አጀማመሩ

**የክፍለ ጊዜ ብዛት— 24**

## ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች፡

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ካጠናቀቁ ብኋላ፤**

- ጂኦግራፊያዊ የባህር ላይ አሰሳ ሂደትና አሳሾች ሲጠቀሙበት የነበርው ን የባህር ላይ መስመር ይገልፃሉ፤
- የዘመናዊው ን ዘመን ስልጣኔ ጅማሮ የአዲሱን ፅንሰ ሐሳብ (Renaissance)፣ የተሀድሶ እንቅስቃሴ (Reformation) እና የተሓድሶ እንቅስቃሴ ተቃው ሞ (Counter Reformation) ያለው ን ጥቅም ያገናዝባሉ፡
- ስለ ኢንዱሰትሪ አብዩት ጽንሰ ሀሳብ በስፋት ይግልፃሉ፡
- ሁለቱን የአለም ጦርነቶች መነሻ ምክንያትና ጉዳቶች ያገናዝባሉ፡
- ቀዝቃዛው የአለም ጦርነትን ባህርያት ይግልፃሉ።

| የመማር ብቃት | ይዜት | የመማር ዘዴ | ምዘና |
| --- | --- | --- | --- |
| • የባህር ላይ አሰሳ ሂደትና አሳሾች ሲጠቀሙበት የነበርው ን የባህር ላይ መስመር ያሳያሉ፣<br>• የዘመናዊው ን  ስልጣኔ ጅማሮ የአዲሱን ፅንሰ ሐሳብ | 4. ዘመናዊው የአለም ታሪክና አጀማመሩ<br>4.1.ጂኦግራፊያዊየባህ ር እና ውቂያኖስ ላይ አስሳ | • የባህር ላይ አሰሳ ሂደትና አሳሾች ሲጠቀሙበት የነበርው ን የባህር ላይ መስመር በፊዚካል ካርታ ላይ እንዲያሳዩ ማድረግ፣<br>• ተማሪዎች በፒራሚድ ዘዴ በመጠቀም ከዘመናዊው  ስልጣኔ ጅማሮ ጋር | • ተከታታይ የምዘና ዘዴን በመጠቀም በየምዕራፉ ሁሉ ው ስጥ ያላቸው ን |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ጅማሮ፣ የተሀድሶ እንቅስቃሴ እና የተሓድሶ እንቅስቃሴ ተቃው ሞ ያለው ን ጥቅም ይለያሉ፣<br>• የኢንዱሰትሪው አብዩት ጽንሰ ሀሳብና ምንነት ያብራራሉ፣<br>• በሁለቱ የአለም ጦርነቶች ላይ ጥናታዊ ጽሁፍ በማዘጋጀት ያቀርባሉ፣<br>• ቀዝቃዛውን የአለም ጦርነት ባህርያት ይገልፃሉ። | 4.2. የአዲሱ ፅንሰ ሐሳብ መጀመር (Renaissance), ተሓድሶ (Reformation) እና የተሓድሶ እንቅስቃሴ ተቃው ሞ(Counter-Reformation)<br>4.3. የኢንዱሰትሪው አብዩት<br>4.4. ሁለቱ የአለም ጦርነቶች<br>4.5. ቀዝቃዛው የአለም ጦርነት | ተያያዥነት ያላቸው ን (የአዲሱን ፅንሰ ሐሳብ፣ የተሓድሶን እንቅስቃሴ እና የተሓድሶእንቅስቃሴ ተቃው ሞ) ላይ በክፍል ው ስጥ እንዲወያዩ መምራት፣<br>• የክፍሉን ተማሪዎች በሁለት ቡድን በመክፈል የአዲሱን ፅንሰ ሐሳብና የተሓድሶን እንቅስቃሴ ለአለም ህዝቦች ባበረከተው አስተዋጽኦ ላይ ክርክር እንዲያደርጉ መርዳት፣.<br>• ተማሪዎች በኢንዱሰትሪው አብዩት፣በሁለቱ የአለም ጦርነቶች እና በቀዝቃዛው የአለም ጦርነት ይዘቶች ላይ አጫጭር ጥናታዊ ጽሁፎችን አዘጋጅተው በክፍል ው ስጥ እንዲያቀርቡ ማድረግ። | ተሳትፎ በመከታተል<br>• ተማሪዎችን ሊያበረታታ የሚችል ገንቢ የማስተካከያ ሐሳብ መስጠት። |

# ምዕራፍ 5፡ የአፍሪካ ታሪክ ከ15ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ

**የክፍለ ጊዜ ብዛት-9**

**ከትምህርቱየሚጠበቁውጤቶች:**

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ካጠናቀቁ ብኋላ፤**

- በአፍሪካ ህዝቦች ላይ የባርያ ንግድ ስርዓት ያስከተለውን ጉዳት ይገልፃሉ፤
- የፀረ ቅኝ አገዛዝ ስርዓት አመለካከትን ያጎለብታሉ፤
- የአፍሪካ ህዝቦች ነፃነታቸውን ለማግኘት ያደረጉትን ትግል፣ በቅኝ ግዛት ስርዓት ዘመን የነበረውን ምጥኔ ሀብታዊና ፖሊቲካዊ ግንኙነቶችን ይገነጸባሉ።

| የመማር ብቃት | ይዜት | የመማር ዘዴ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • የአፍሪካ ህዝቦች የባርያ ንግድ ስርዓትን ለመከላከል ያደረጉትን ትግል ለማሳየት ዝግጁ ይሆናሉ፣<br>• የፀረ ቅኝ አገዛዝ ስርዓት አመለካከትን ያጎለብታሉ፣<br>• የአፍሪካ ህዝቦች ነፃነታቸውን ካገኙ በኃላ ያደረጉትን ምጥኔ ሀብታዊና ፖሊቲካዊ ግንኙነቶችን በማድነቅ ያከብራሉ፣ | **5. የአፍሪካ ታሪክ ከ15ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ**<br>5.1. የባርያ ንግድ ስርዓት፣<br>5.2. የቅኝአገዛዝ ሰርዓት በአፍሪካ<br>5.1. ከነፃነት በኋላ ያለው ፖሊቲካዊና ምጣኔ ሀብታዊ የአፍሪካ ህዝቦች ትስስር | • ተማሪዎች የሚከተሉትን ጥያቄዎች፣ የባርያ ንግድ ምንነት?በባሪ ንግድ ው ሰጥ የተሳተፉ ኃይሎች እነማን እንደሆኑ ሁለት ሁለት በመሆን በክፍል ው ስጥ እንዲያቀርቡ ማድረግና መልሶም ጥያቄ በመጠየቅ ማስተማር፣<br>• ተማሪዎች ከአፍሪካ ቅኝ አገዛዝ ጋር በተያያዘ ጽሁፍ እንዲያዘጋጁ በማድረግ፣<br>• ተማሪዎችን በተለያዩ ቡድኖች በመከፋፈል በሚከተሉት ነጥቦች ላይ፣ የአፍሪካ ሀገሮች ነፃነታቸው ን ለመጎናጸፍ ያደረጉትን ትግል፣ የአፍሪካ ህዝቦች ነፃነታቸውን ካገኙ በኃላ እያደረጉ ያለው ን ምጥኔ ሀብታዊና ፖሊቲካዊ ግንኙነቶች ላይ አጠር ያለ ጽሁፍ በማዘጋጀት ለክፍላቸው እንዲያቀርቡ ማድረግ። | • ተማሪዎች ሁለት ሁለት ሆኖ ያደረጉትን ተሳትፎ መከታተል፣<br>• ባሉት ጠንካራና ደካማ ጎኖች ላይ መረጃ ማጠናቀር፣<br>• ተማሪዎችን ሊያበረታታ የሚችል ገንቢ የማስተካከያ ሐሳብ መስጠት። |

# ምዕራፍ 6፡ዘመናዊው የኢትዮጵያ ታሪክ

የክፍለ ጊዜ ብዛት-12

**ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች:**

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ካጠናቀቁ ብኋላ፤**

- ዘመናዊ የኢትዮጵያ መንግሥት አመሰራረት ሂደት ይገነዘባሉ፣
- የኢትዮጵያን ካርታ በማዘጋጀት በካረታው ላይ የረጅም ርቀት የንግድ መስመሮችን ያሳያሉ፣
- ኢትዮጵያ ከው ጭ ሀገራት ጋር ያላትን ግንኙነት ያብራራሉ።
- የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ለማስከብር የተደረጉትን የኢትዮጵያ ህዝቦች ትግል በማክበር ትልቅ ዋጋ ይሰጡታል፣

| የመማር ብቃት | ይዜት | የመማር ዘዴ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • ዘመናዊው የኢትዮጵያ መንግሥት አመሰራረት ሂደት ማገናዘብ፣<br>• በኢትዮጵያ ው ስጥ የነበረው ን የረጅም | **6. ዘመናዊው የኢትዮጵያታሪክ**<br><br>6.3. ዘመናዊው የኢትዮጵያ ታሪክ መንግሥት አመሰራረት<br>6.2. የረጅም ርቀት የንግድ መስመር | • ተማሪዎችን በፒራሚድ ዘዴ በማደራጀት ስለ ዘመናዊው የኢትዮጵያ መንግሥት አመሰራረት ሂደት ላይ ተወያይተው በማገናዘብ እንዲያብራሩ መምራት፣<br>• የኢትዮጵያን ካርታ በማዘጋጀት በካረታው ላይ በኢትዮጵያ ው ስጥ የነበረው ን የረጅም ርቀት የንግድ መስመሮችን እንዲያሳዩ ማድረግ፣ | • ተማሪዎች በቡድን ምክክር ው ስጥ ያላቸው ን ተሳትፎ በመከታተል፣<br>• የተለያዩ የተከታታይ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ርቀት የንግድ መስመሮችን ያሳያሉ፣<br>• ኢትዮጵያ ከው ጭ ሀገራት ጋር ያላትን ግንኙነት ያብራራሉ፣<br>• የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ለማስከብር የተደረጉትን የኢትዮጵያ ህዝቦች ትግል በማክበር ትልቅ ክብር ይሰጡታል።<br>. | የኢትዮጵያና የው ጭ ሀገራት ግንኙነት<br>6.4. የሀገሪቱን ሉዓላዊነትንና ዳር ድንበር ለማስከበር የተደረገው<br>የ ኢትዮጵያ ህዝቦች አንድነት(ግብጽ፣ ሱዳን፣ጣልን፣ቱርክና ሶማሊያ) | • ኢትዮጵያ ከው ጭ ሀገራት ጋር ያላትን ግንኙነት በተመለከተ ተማሪዎች አጠር ያለ ጽሁፍ አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ መምራት(መንገድ ማሳየት)<br>• የኢትዮጵያ ህዝቦች የሀገሪቱን ሉዓላዊነትና ዳር ድንበር ለማስከበር ከው ጭ ሀገራት ጋር ያደረጉትን ጦርነቶች የሚያሳይ ቪድዮዎች ለተማሪዎች ማሳየት።በመቀጠልም ተማሪዎች ይህንን ዳር ድንበር ለማስከበር አባቶቻችን የከፈሉትን መስዋእትነት ትልቅ ክብርና ግምት እንዲሰጡት ማበረታታት። | ምዘና ዘዴዎችን መጠቀም<br>• ባሉት ጠንካራና ደካማ ጎኖች ላይ መረጃ ማጠናቀር፣<br>• ተማሪዎችን ሊያበረታታ የሚችል ገንቢ የማስተካከያ ሐሳብ መስጠት። |

## ምዕራፍ ሰባት፡ ትኩረት የሚሹ የዓለም ጉዳዮች

ለዚህ ምዕራፍ የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት............................................... 12

### ከምዕራፉ ትምህርት የሚጠበቁ ዉጤቶች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኃላ:

- ❖ አየር ለውጥ በሰዉ ልጅና በአከባቢ ላይ የሚያመጣዉን ጉዳት ይገመግማሉ፡፡
- ❖ ማህበረሰቡ አከባቢያቸዉን ለመጠበቅ ያላቸዉን እዉቀት በመለየት ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡
- ❖ በአከባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ላይ የሚሠሩ ድርጅቶችን ወይንም ግለሰቦችን ያደንቃሉ፡፡

| የመማር ብቃቶች | ይዘት | የመማር ማስተማር ዘዴዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • የር ለውጥ በአከባቢና በሰዉ ላይ የሚያደርሰዉን ጉዳትና እንክብካቤያቸዉን መገምገም::<br>• አየር ለውጥ በሰዉና በአከባቢ ላይ የሚያደርሰዉን ጉዳት ለመቀነስ የማህበረሰቡን ተሳትፎ መግለፅ::<br>• የአየር መበከል የሚያመጣዉን ጉዳት መግለፅ::<br>• ከውሃ እጥረት ጋር ተያይዘዉ የሚመጡት ችግሮችን መግለፅ::<br>• በደን መጥፋት ምክንያት የሚመጡ ጉዳቶችን መለየት::<br>• ሰዎች በግልና በቡድን አከባቢያቸዉን ለመጠበቅ የሚያደርጉትን ተሳትፎ ማድነቅ:: | **7. ትኩረት የሚሹ የዓለም ጉዳዮች**<br>7.1. የአየር ንብረት መለወጥ<br>7.1.1. የአየር ንብረት መለወጥ ፅንሰ ሀሳብ<br>7.1.2. የአየር ንብረት መለወጥ ምክንያቶችና የሚያደርሰዉን ተፅዕኖዎች<br>7.1.3. የአየር ንብረት መለወጥን ለመቆጣጠር የሚሰሩ ሥራዎች<br>7.1.4. የአየር ንብረት መለወጥ ለመቆጣጠር በአከባቢያቸዉ የሚሰሩ ሥራዎችን ለመግለፅ የሚቀርብ ጥናታዊ ፅሑፍ<br>7.1.5. የአየር ብክለት<br>7.1.6. የውሃ እጥረት<br>7.1.7. የደን መጨፍጨፍ | • ጥያቄና መልስ የማስተማር ዘዴን በመጠቀም የአየር ንብረት መለወጥ ፅንሰ ሀሳብን መግለፅ:: በመቀጠል ተማሪዎችን በአምስት ቡድን በመክፈል የአየር ንብረት መለወጥና በዚህ ምክንያት በሰዉ ልጅ ላይ የሚያደርሰዉ ተፅዕኖ እንዲወያዩ ማድረግ::<br>• ተማሪዎች የአየር ንብረት መለወጥ ምክንያትና በሰዉ ልጅ ላይ የሚያደርሰዉ ተፅዕኖ ላይ አጭር ርፖርት እንዲያቀርቡ ማድረግ::<br>• ተማሪዎች መስክ ጉብኝት በማድረግ እያንዳንዱ ቤተሰብ ውሃን እንዴት እንደሚጠቀም ሪፖርት እንዲፅፉና እንዲያቀርቡ ማድረግ:: | • ተማሪዎች በቡድን ውይይት የሚያደርጉትን ተሳትፎ በመመልከት መረጃን መሰብሰብና ግብረ መልስ መስጠት::<br>• ተማሪዎች በቡድን ውይይት ውስጥ በትክክል መሳተፋቸዉን ላማረጋገጥ የከባቢ አየር መለወጥና የሚያመጣዉን ጉዳት ምን ምን እንደሆኑእንዲሁም ለመከላከል መደረግ የሚገቡ ሥራዎች ምን ምን እንደሆኑ መጠየቅ::<br>• የተማሪዎችን የቡድን ውይይት ከተከታተሉ በኋላ እያንዳንዱ ተማሪ ሪፖርት እንድያቀርቡ በማድረግ በመጨረሻም ግብረ መልስ መስጠት:: |

## ዋቢ መጽሐፍት

Adu Boahen, A.General History of Africa VII; Africa under colonial domination 1880-1935. California:Heinemann(UNESCO), 1985.

Avner, Greif. "*Cultural beliefs and Organization of society: A historical and theoretical reflections on collectivist and individualist societies*". The journal of political Economy, Volum,102, issue 5(oct.1994)912-950.*Also available*,...

Bahru Zewude. *A History of Modern Ethiopia 1855-1974*, Addis Ababa: Addis Ababa University. 1992.

_____ *A History of Modern Ethiopia 1855-1991*, Second Edition, Addis Ababa, Addis Ababa University press. 2002.

Corn, Wall. *World History in the Twentieth Century,* 1980.

Curtin, P etal .*African History: From Earlier time to Independence.*London and New York: Longman,1995.

Easton, Steward. *Brief History of the Western world*. Barnes & Noble Inc. New York, 1962.

Gamachu Magarsa. *The Oromo and the Ethiopian state ideology in a historical perspective,* in Ethiopia in broader perspective. Edited by kasuyoshifuki et al, vol. 2, 1997.

Girma Alemayehu &Tadsse Delessa .*World ,African &Ethiopian History.,*commercial Printing Press___